፶፮፡ ከመምህሩ ፡ ከአባ ፡ ጳኵሚስ ፡ ዘንድ ፡ እንደተማረ፡ለልጆቹ፡መነኰሳት፡ሥርዓተ ፡ ማኅበርን ፡ ሠራላቸው። ከዚህም፡ በኋላ፡ በእግዚአብሔር፡ቸርነት፡እንደ፡ ኄኖክና፡ እንደ፡ ኤልያስ ፡ ከሞት ፡ ገጽ ፡ ተሠወረ።

፶፯፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡ በዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለዘሚካኤል ፡ ዘተሰምየ ፡ አረጋዌ። እስመ ፡ ሑረቱ ፡ በጥበብ ፡ ወፍናዊሁ ፡ ልባዌ ። ምስሌሁ ፡ ኀቡረ ፡ ዘበአሐዱ ፡ ህላዌ። ሰላም ፡ ለቅዱሳን ፡ ዘተሰነዓዉ፡ ስንዓዌ። ከመ ፡ በጸሎት ፡ ይሥዓሩ፡ሥርዓቶ፡ለአርዌ።

፶፰፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለመራክዋ ፡ ወእለ ፡ ምስሌሁ ፡ ሰማዕታት፡ ወዱማቴዎስ፡ ወእምራይስ፡ ወ፬፻ ወ፴ ወ፩ዱ ፡ ሰማዕታት ፡ ወእግዚአብሔር፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቶሙ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።

***

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ ወ፫ ለጥቅምት ፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ኮነ፡ ሰማዕተ፡ ቅዱስ ፡ ቢላሞን ፡ ዘእምሀገረ ፡ ኒቆምድያ።

፪፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አቡሁ ፡ መምለኬ ፡ ጣዖት ፡ ወእሙሰ ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ወመሀርዎ ፡ ጥበበ፡ ወእምዝ፡ ተራከበ፡ ምስለ፡ አሐዱ፡ ቀሲስ፡ ዘስሙ፡ አርማላስ፡ ወውእቱ፡ መሀሮ፡ ሃይማኖተ፡ ርትዕተ፡ ዘእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወአጥመቆ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወተጋደለ ፡ ገድለ ፡ ዐቢየ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ እስከ ፡ ወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ዐበይት።

፫፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ መጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ ፩ ዕውር፡ ብእሲ ፡ ይግበር ፡ ሎቱ ፡ መድኃኒተ ፡ ለአዕይንቲሁ ፡ በጥበቡ ፡ ወገብረ፡

፶፰፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የመራክዋና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ያሉ ፡ ሰማዕታት ፡ የዱማቴዎስና ፡ የእምራይስ ፡ የአራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ሰማዕታት ፡ መታሰቢያቸው ፡ ሆነ ። እግዚአብሔርም ፡ በጸሎታቸው ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

***

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥቅምት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ በዚች ፡ ቀን፡ ከኒቆምድያ ፡ አገር ፡ ቅዱስ ፡ ቢላሞን ፡ በሰማዕትነት፡አረፈ።

፪፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ አባቱ ፡ ጣዖት ፡ አምላኪ ፡ ነው ፡ እናቱ ፡ ግን ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ፡ ጥበብንም ፡ አስተማሩት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ፡ ስሙ ፡ አርማላስ ፡ ከሚባል ፡ ቄስ ፡ ጋር ፡ ተገናኘ ። እርሱም ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የቀናች፡ ሃይማኖት ፡ አስተማረው፡ የክርስትና፡ ጥቅምቀትንም ፡ አጠመቀው ፡ ታላቅ ፡ የሆኑ ፡ ድንቆች ፡ ታምራትን ፡ የማድረግ ፡ ሀብትን ፡ እግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ሰጠው ፡ ድረስ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ታላቅ ፡ ገድልን ፡ ተጋደለ።

፫፡ በአንዲት ፡ ቀንም ፡ ለዓይኖቹ ፡ መድኃኒትን ፡ እንዲአደርግለት ፡ አንድ ፡ ዕውር ፡ ሰው ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ፡ ቅዱስ ፡ ቢላ

www.ethiopianorthodox.org

ቢላሞን ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አስተዳለውኩ ፡
ለከ፡መንግሥተ፡ሰማያዊ፡፡

፰፡ ወሰምዐ፡ሐራሁ፡ለንጉሥ፡ዘንተ፡ቃለ፡
ትፍሥሕት ፡ ወአምኑ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡፡ ወተ
አመኑ ፡ በቅድመ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ እሙ
ንቱ ፡ አምኑ ፡ በክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ሕያው ፡ ወሶቤሃ ፡ አዘዘ ፡
ንጉሥ፡ከመ፡ይምትሩ፡አርእስቲሆሙ፡
በሰይፍ ፡ ወለቅዱስኒ ፡ ቢላሞን ፡ ምስሌ
ሆሙ ፡ ይምትርዎ ፡ ወከመዝ ፡ ፈጸመ ፡
ስምዖ፡ምስሌሆሙ፡ለእለ፡ሐራ፡ወኍ
ልቆሙ ፡ ፫ወ፬ወ፰ቱ ፡ ወነሥኡ ፡ አክ
ሊለ፡ስምዕ፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡፡

፱፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡
ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ሰማዕት ፡
ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡
ዓለም፡አሜን፡፡

፲፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለ፫
ወ፬ ፡ ወ፰ቱ ፡ ሰማዕታት ፡ ማኅበረ ፡ ቢላ
ሞን ፡ ወተዝካረ ፡ ዕረፍቶሙ ፡ ለሰላት
ዮን፡ ወአጥራኪስ፡ ወኢናፍር፡ ወአድራ
ኒቆስ፡ወአርሞሊስ፡ወአርሞክስ፡ወአድ
ማንያ፡ ወአርሚስ ፡ ወቅድስት፡ ጾመታ ፡
ወኢሳይያስ፡አብ፡ወሲላስ፡ረድእ፡ጳው
ሎስ፡ወተዝካሮሙ፡ለሐዋርያት፡፡

፲፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡
ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ወበረከቶሙ ፡
ተሀሉ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን፡፡

የደስታ ፡ ቃል ፡ አሰማው፡፡ የመረጥኩህ ፡
ቢላሞን ፡ ሆይ ፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡ እኔ፡
ሰማያዊ ፡ መንግሥትን ፡ አዘጋጅቼልሃ
ለሁና

፰፡ የንጉሡ ፡ ጭፍሮችም ፡ ይህን ፡ የደስታ ፡
ቃል ፡ ሰሙ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌ
ታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አምነው ፡
እነርሱ፡በሕያው፡እግዚአብሔር፡ልጅ፡
ክርስቶስ ፡ የአመኑ ፡ መሆናቸውን ፡ በን
ጉሡ ፡ ፊት ፡ ገለጡ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡
ራሳቸውን ፡ በሰይፍ ፡ እንዲቆርጡ ፡
ንጉሡ ፡ አዘዘ ፡፡ ቅዱስ ፡ ቢላሞንንም ፡ እን
ዲቆርጡት ፡ አዘዘ ፡ ከእሊህ ፡ ጭፍሮች ፡
ጋርም፡እንዲህ፡ገድሉን፡ፈጸመ፡ቍጥራ
ቸውም ፡ መቶ ፡ ኀምሣ ፡ ስምንት ፡ ነው ፡
የሰማዕትነት ፡ አክሊልንም ፡ በመን
ግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ፡፡

፱፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡
እኛንም ፡ በዚህ ፡ ሰማዕት ፡ ጸሎት ፡ ይማ
ረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡
ለዘላለሙ፡አሜን፡፡

፲፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የቢላሞን ፡ ማኅበር ፡ የሆኑ
የመቶ ፡ ሃምሣ ፡ ስምንት ፡ ሰማዕታት ፡
መታሰቢያቸው፡ ነው ፡ ደግሞ ፡ የሰላ
ትዮን ፡ የአጥራኪስ ፡ የኢናፍር ፡ የአድራ
ኒቆስ ፡ የአርሞሊስ ፡ የአርሞቅስ ፡ የአድ
ማንያ ፡ የአርሚስ ፡ የቅድስት ፡ ጾመታ ፡
የአባት፡ኢሳይያስ፡የጳውሎስ፡ረድ፡የሲ
ላስና ፡ የሐዋርያትም ፡ የዕረፍታቸው ፡
መታሰቢያ ፡ ነው፡፡

፲፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡
እኛንም፡ በጸሎታቸው ፡ ይማረን ፡ በረከ
ታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡
አሜን፡፡

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ እብል ፡ ለርክበተ ፡ ዐፅምክሙ ፡ ወርቅ፡፡ አዝቂር ፡ ወኪርያቅ፡፡ ወሰላም ፡ ለሲላስ ፡ ረድእ ፡ ጳውሎስ ፡ ማዕነቅ፡፡ ዘጸለለ ፡ በጌጋይ ፡ እምነጽሮታ ፡ ለጽድቅ ፡፡ ዐይነ ፡ ሐሊናየ ፡ ፈውሱ ፡ በምራቅ፡፡

ሰላም፡ሰላም፡ሐዋርያቲሁ፡ለአብ፨ዘአኀዙ፡ዮም፡በቃለ፡ጥበብ፡፡ በቤተ፡ክርስቲያን፡አሐቲ፡ እንተ፡አሕዛብ፡፡ ያስተጋብኡ፡መጻሕፍተ፡እምባሕረ፡መለኮት፡ርኂብ፡፡ ከመ፡ጽጌያተ፡ያስተ ጋብእ፡ንህብ፡፡

፩፤ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ አመ፡ ፲ወ፮ ለጥቅምት፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አብ፡ ቅዱስ፡ አባ፡ ያቃቱ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ዘሀገረ፡ እስክንድርያ፡ እምኍልቆሙ፡ ለአበው፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ፴ወ፱ቱ።

፪፤ ወሶበ፡ አዕረፈ፡ አባ፡ ብንያሚን፡ ዘእምቅድሜሁ፡ ኀረይዎ፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ ወሤምዎ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ላዕለ፡ ሀገረ፡ እስክንድርያ፡ ወበመዋዕሊሁ፡ በጽሐ፡ ብዙኅ፡ ምንደቤ፡ እስመ፡ ሀሎ፡ ፩ መለካዊ፡ ዘስሙ፡ ቴዎዶስዮስ፡ ወውእቱ፡ ሖረ፡ ኀበ፡ ዘይድ፡ ንጉሠ፡ ደማስቆ፡ ወወሀቦ፡ ለንጉሥ፡ ብዙኀ፡ አምኃ፡ ወተሠይመ፡ መኰንነ፡ ላዕለ፡ ሀገረ፡ እስክንድርያ፡ ወአኀዘ፡ ያመንድቦ፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ ያቃቱ፡ እስከ፡ ነሥአ፡ እምኔሁ፡ ጸባሕተ፡ ለለዓመት፡ ፫፻፷ተ፡ ዲናረ፡ ወርቅ፡ ወከመዝ፡ አጽሐቦ፡ እስከ፡ አመ፡ አጥፍአ፡ እግዚአብሔር፡ ለውእቱ፡ ዐላዊ።

፫፤ ወበመዋዕሊሁ፡ ተፈጸመ፡ ሕንፀታ፡ ለቤተ፡ ክርስቲያን፡ ዘአባ፡ መቃርስ፡ አበ፡ ብዙኃን፡ አበው፡ ቅዱሳን።

፬፤ ወበአሐቲ፡ ሌሊት፡ አስተርአዮ፡ መልአከ፡ እግዚአብሔር፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ ወአይድዖ፡ ከመ፡ በሀገረ፡ ፍዩም፡ ሀሎ፡ ብእሲ፡ መነኰስ፡ ጻድቅ፡ ዘስሙ፡ ዮሐንስ፡ ዘይትቀነይ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ዘአባ፡ መቃርስ፡ ወአዘዘ፡ ከመ፡ ይፌኑ፡ ላእካነ፡ ወያብጽሑ፡ ኀቤሁ፡ ወከመ፡ ይትራድኡ፡ በእንተ፡ ተግሣጸ፡ ሕዝብ፡ ወትምህርት፡ ወከሠተ፡ ሎቱ፡ ካዕበ፡ ከመ፡ ውእቱ፡ ይከውን፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ እምድኅሬሁ።

፭፤ ወሶቤሃ፡ ፈነወ፡ ላእካነ፡ ወአምጽኡ፡ ኀቤሁ፡ ወመጠዎ፡ ኵሎ፡ ግብረ፡ ወውእቱ፡ ኮነ፡ ያዓርፎ፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ እምብዙኅ፡ ፃማ፡ ወነበረ፡ ዲበ፡ መንበረ፡ ሢመቱ፡ ፲ ወ፱ተ፡ ዓመተ፡ ወእምዝ፡ አዕረፈ፡ በሰላም።

፮፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቱ፡ ለዝንቱ፡ አብ፡ ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን፡

፩፤ አንድ፡ አምላክ፡ በሆነ፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ ጥቅምት፡ ዐሥራ፡ ስድስት፡ በዚች፡ ቀን፡ ለአባቶች፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ አርባ፡ ዘጠነኛ፡ የሆነ፡ ቅዱስ፡ አባት፡ የእስክንርድያ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ አባ፡ ያቃቱ፡ አረፈ።

፪፤ ከርሱ፡ በፊት፡ የነበረ፡ አባ፡ ብንያሚን፡ በአረፈ፡ ጊዜ፡ ይህን፡ አባት፡ መርጠው፡ በእስክንድርያ፡ አገር፡ ላይ፡ ሊቀ፡ ጵጵስና፡ ሾሙት፡ በዘመኑም፡ ብዙ፡ ችግር፡ ደርሶበታል፡ ስሙ፡ ቴዎዶስዮስ፡ የሚባል፡ አንድ፡ መለካዊ፡ ሰው፡ ነበረ፡ እርሱም፡ ወደ፡ ደማስቆ፡ ንጉሥ፡ ወደ፡ ዘይድ፡ ሒዶ፡ ብዙ፡ እጅ፡ መንሻ፡ ሰጥቶ፡ ለእስክንድርያ፡ አገረ፡ ገዥ፡ ሁኖ፡ ተሾመ። ይህንንም፡ አባት፡ አባ፡ ያቃቱን፡ ሊአስጨንቀው፡ ጀመረ፡ በየዓመቱ፡ ግብር፡ ሰባት፡ ሺህ፡ የወርቅ፡ ዲናር፡ ከእርሱ፡ እስከተቀበለ፡ ድረስ፡ እግዚአብሔርም፡ እስከ፡ አጠፋው፡ ድረስ፡ ይህን፡ አባት፡ እንዲህ፡ አሠቃየው።

፫፤ በዘመኑም፡ የብዙዎች፡ ቅዱሳን፡ አባቶች፡ አባት፡ የሆነ፡ የአባ፡ መቃርስ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሕንፃዋ፡ ተፈጸመ።

፬፤ በአንዲት፡ ሌሊትም፡ ከእግዚአብሔር፡ የታዘዘ፡ መልአክ፡ ለዚህ፡ አባት፡ ተገለጸለት፡ ፍዩም፡ በሚባል፡ አገር፡ በአባ፡ መቃርስ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ውስጥ፡ የሚያገለግል፡ ዮሐንስ፡ የሚባል፡ ጻድቅ፡ ሰው፡ መነኰስ፡ እንዳለ፡ ነገረው። ሕዝብን፡ በማስተማርና፡ በመምከርም፡ ይራዳው፡ ዘንድ፡ መልእክተኞችን፡ ልኮ፡ እንዲአስመጣውም፡ አዘዘው፡ ሁለተኛም፡ ከእርሱ፡ በኋላ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ እንደሚሆን፡ ገለጠለት።

፭፤ በዚያንም፡ ጊዜ፡ መልእክተኞችን፡ ልኮ፡ ወደርሱ፡ አስመጣው፡ ሥራውንም፡ ሁሉ፡ አስረከበው፡ ይህንንም፡ አባት፡ ከብዙ፡ ድካም፡ የሚያሳርፈው፡ ሆነ፡ በሹመቱ፡ ወንበር፡ ዐሥራ፡ ዘጠኝ፡ ዓመት፡ ኑሮ፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ በሰላም፡ አረፈ።

፮፤ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ እኛንም፡ በዚህ፡ አባት፡ ጸሎት፡ ይማረን፡ በረከቱም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም፡ለአባ፡ያ.ቃ.ቱ፡ምሉእ፡ስብሐት፡ወውዳሴ።እንተ፡ነሥአ፡ክብረ፡ዘየዓቢ፡እምክብረ፡ሙሴ። ፈለሰ፡ዮም፡በከመ፡አመሮ፡መልአከ፡ቅዳሴ።ዮሐንስሃ፡ጻድቀ፡ብእሴ።እምድኅረ፡ረሰየ፡መንበሮ፡ወራሴ።

፳፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካረ፡ዕረፍቶሙ፡ለቅዱሳን፡ መቀሮፍዮን፡ ወዕብሎ፡ ወጴጥሮስ፡ ረድኡ፡ለአባ፡ኢሳይያስ፡ባሕታዊ፡ወተዝካሮሙ፡ለፋሩ፡ወ፯ወ፫ቱ፡ጻድቃን፡እለ፡ድርቂ፡ወአሮን፡መስተጋድል፡ወቃርቡ፡ወአናልዩ፡ወአባ፡ጳውሊ፡ወማርቆስ፡መስተጋድል።ወእግዚአብሔር፡ይምሐረነ፡በጸሎቶሙ፡ወበረከቶሙ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፡ በዚችም፡ቀን፡የቅዱሳን፡መቀሮፍዮን፡የእብሎ፡የባሕታዊ፡ኢሳይያስ፡ረድእ፡የጴጥሮስ፡ደግሞ፡የፋሩ፡የድርቄ፡አገር፡የሆኑ፡የአርባ፡አምስት፡ጻድቃን፡የመስተጋድል፡አሮን፡የቃርቡ፡የአናልዩ፡የአባ፡ጳውሊ፡የመስተጋድል፡ማርቆስ፡የዕረፍታቸው፡መታሰቢያ፡ነው።እግዚአብሔርም፡በጸሎታቸው፡ይማረን፡በረከታቸውም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለክሙ፡መቀሮፍዮን፡ወእብሎ፡ብፁዓዊ።ወጴጥሮስ፡ረድኡ፡ለኢሳይያስ፡ባሕታዊ። ደናግል፡ዕደው፡እምነ፡ፍትወት፡ምድራዊ።ሀቡኒ፡እምቅብዕክሙ፡ፈትለ፡ማኅቶትየ፡አርዊ።አመ፡በውውዓ፡ሌሊተ፡ይመጽእ፡መርዓዊ።

***

፩፡ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩አምላክ፡አመ፡፲ወ፳ ለጥቅምት፡በዛቲ፡ዕለት፡ኮነ፡ሰማዕተ፡ቅዱስ፡ፊልያስ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘሀገረ፡ቀምስ።

፪፡ ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡በመዋዕሊሁ፡ለቍልቍልያኖስ፡መኰንን፡አቅረብዎ፡ኀበ፡ዓውደ፡ምኵናን፡ወይቤሎ፡ቍልቍልያኖስ፡ሡዕ፡ለአማልክት፡ወይቤ፡ፊልያስ፡አንሰ፡ኢይሠውዕ፡ለአማልክት፡ዘእንበለ፡ለእግዚአብሔር፡ባሕቲቱ፡ወይቤ፡ቍልቍልያኖስ፡አይኑ፡መሥዋት፡ዘይፈቅድ፡እግዚአብሔር፡ወይቤሎ፡ፊልያስ፡ልበ፡ንጹሐ፡ወመንፈሰ፡የዋሀ፡ወትሑተ፡ወኵነኔ፡ጽድቅ፡ወነገረ፡ህልወ፡ዘከመዝ፡መሥዋዕተ፡ይሠምር፡እግዚአብሔር።

፫፡ ወይቤ፡ቍልቍልያኖስ፡በእንተ፡ነፍስኑ፡ትትጋደል፡አው፡በእንተ፡ሥጋ፡ወይቤ፡ፊልያስ፡በእንተ፡ነፍስ፡ወሥጋ፡እስመ፡እሙንቱ፡ይትነሥኡ፡ኅቡረ።

፬፡ ወይቤ፡ቍልቍልያኖስ፡ብከኑ፡ብእሲት፡ፍቅርት፡ወውሉድ፡ፍቁራን፡ወእኀው፡ወአዝማድ፡ወይቤ፡ፊልያስ፡ እምኵሉ፡ፍቅረ፡እግዚአብሔር፡ያዐቢ።

***

፩፡ አንድ፡አምላክ፡በሚሆን፡በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥቅምት፡ዐሥራ፡ሰባት፡በዚች፡ቀን፡የሀገረ፡ቀምስ፡ኤጲስቆጶስ፡ቅዱስ፡ፊልያስ፡በሰማዕትነት፡አረፈ።

፪፡ ይህንንም፡ቅዱስ፡በመኰንኑ፡ቍልቍልያኖስ፡ዘመን፡ወደ፡ፍርድ፡አደባባይ፡አቀረቡት፡ቍልቍልያኖስም፡ለአማልክት፡ሠዋ፡አለው።ፊልያስም፡እኔ፡ከብቻው፡እግዚአብሔር፡በቀር፡ለአማልክት፡አልሠዋም፡አለ።ቍልቍልያኖስም፡እግዚአብሔር፡ምን፡አይነት፡መሥዋዕት፡ይሻል፡አለ፡ፊልያስም፡ቅን፡ትሑት፡የሆነ፡ንጹሕ፡ልቡናን፡ዕውነተኛ፡ፍርድን፡ቁም፡ነገርን፡እንዲህ፡ያለ፡መሥዋዕትን፡እግዚአብሔር፡ይወዳል፡አለው።

፫፡ ቍልቍልያኖስም፡የምትጋደል፡ስለ፡ነፍስ፡ነው፡ወይስ፡ስለ፡ሥጋ፡አለ፡ፊልያስም፡ስለ፡ነፍስና፡ስለ፡ሥጋ፡ነው፡እነርሱ፡በአንድነት፡ይነሣሉና፡አለ።

፬፡ ቍልቍልያኖስም፡የምትወዳት፡ሚስት፡የምትወዳቸው፡ልጆች፡ወይም፡ወንድምና፡ዘመድ፡አለህን፡አለው፡ፊልያስም፡ከሁሉም፡የእግዚአብሔር፡ፍቅር፡ይበልጣል፡አለ።

www.ethiopianorthodox.org

፫፡ ወይቤ፡ቍልቍልያኖስ፡አይኑ፡ዘገብረ፡እግዚ
አብሔር፡ እምሥናይ፡ወይቤ፡ፊልያስ፡ገብረ፡
ለነ፡እግዚአብሔር፡ ሰማየ፡ወምድረ፡ወኵሎ፡
ዘውስቴቶሙ፡ ወዓዲ ፡ ከመ ፡ ያድኅነነ ፡ እም
እደ ፡ ሰይጣን ፡ ጸላኢነ ፡ ወረደ ፡ እምሰማያት ፡
ወተሰብአ፡ወተወልደ፡እምቅድስት፡ድንግል፡
ማርያም። ወአንሶሰወ፡ውስተ፡ዓለም፡ወመሀ
ረነ ፡ ፍኖተ ፡ ሕይወት ። ወእምዝ ፡ ተወክፈ ፡
ሕማማተ ፡ በሥጋሁ ፡ ወተሰቅለ ፡ ወሞተ ፡
ወተንሥአ፡በሣልስት፡ዕለት፡ወዐርገ፡በ፵፡
ዕለት ፡ ወካዕበ ፡ ይመጽእ ፡ ለኰንኔ ፡ ወዘንተ ፡
ኵሎ፡ገብረ፡በእንቲአነ።

፬፡ ወይቤ ፡ ቍልቍልያኖስ ፡ ቦኑ ፡ አምላክ ፡
ይሰቀል ፡ ወይመውት ፡ ወይቤሎ ፡ ፊልያስ ፡
እወ ፡ ሞተ ፡ በእንተ ፡ ፍቅረ ፡ ዚአነ ፡ ወየሀበነ ፡
ሕይወተ፡ዘለዓለም።

፭፡ ወይቤሎ፡ቍልቍያኖስ፡ኢያእመርከሁ፡ከመ፡
አነ ፡ አክበርኩከ ፡ ወኢፈቀድኩ ፡ እጸባእከ ፡
እስመ፡አአምር፡ከመ፡ክቡረ፡ዘመድ፡አንተ፡
ወይእዜኒ ፡ ሡዕ ፡ ለአማልክት ፡ ከመ ፡ ኢት
ሙት ፡ በእኩይ ፡ ሞት ፡ ወይቤሎ ፡ ፊልያስ፡
እመሰ፡ፈቀድከ፡አሥምሮትየ፡አዝዝ፡ኰንኖ
ትየ ፡ ወቀቲሎትየ ፡ ወሶቤሃ፡ አዘዘ ፡ ቍልቍ
ያኖስ፡ከመ፡ይከልልዎ፡በሰይፍ።

፰፡ ወእንዘ ፡ ይወስድዎ ፡ ይቅትልዎ ፡ መጽኡ ፡
ኀቤሁ ፡ አዝማዲሁ ፡ ወዐበይተ ፡ ሀገር ፡ ወሰአ
ልዎ ፡ እንዘ ፡ ይስዕሙ ፡ እደዊሁ፡ ወእገሪሁ ፡
ከመ ፡ ይትአዘዝ፡ ለመኰንን ፡ ወይሡዕ ፡ ለአማ
ልክት። ውእቱሰ ፡ ገሠጾሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ አ፡
መስሕታን ፡ሰስሉ ፡ እምኔየ ፡ እስመ ፡ አነ ፡
አሐውር ፡ እፁር ፡ መስቀሎ ፡ ለእግዚእየ ፡
ክርስቶስ።

፱፡ ወበጺሐ ፡ ኀበ ፡ ይቀትልዎ ፡ ወሜጠ ፡ ገጾ ፡
መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ ወሰፍሐ ፡ እደዊሁ ፡ ወጸ
ለየ ፡ ኀበ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ፡
ስብሐት ፡ወአማሕፀነ ፡ ሕዝቦ ፡ ኀቤሁ ፡ ወተሰ
ነዓለ ፡ ወእምዝ ፡ ከለልዎ ፡ ወነሥአ ፡ አክ
ሊለ፡ስምዕ።

፲፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡አብ፡መስተጋድል፡
ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ዓለመ፡ለዓለም፡
አሜን።

፫፡ ቍልቍልያኖስም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከበጎ ፡
ሥራ ፡ የሠራው ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አለ ፡
ፊልያስም ፡እግዚአብሔር፡ ያደረገልን፡ይህ፡
ነው ፡ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ በውስጣቸው ፡
ያሉትን፡ሁሉ፡ፈጠረልን።ዳግመኛም፡ከጠላ
ታችን ፡ ከሰይጣን ፡ እጅ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡
ከሰማያት ፡ ወርዶ ፡ ከቅድስት፡ ድንግል ፡
ማርያም፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ተወለደ ፡ የሕይወት ፡
መንገድንም ፡ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ ተመላልሶ ፡
አስተማረ፡መከራንም፡በሥጋው፡ተቀብሎ፡
ተሰቅሎ ፡ ሞተ ፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡
ተነሥቶ ፡ በአርባ ፡ ቀን ፡ ዐረገ ፡ ዳግመኛም ፡
ለፍርድ፡ ይመጣል ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡
አደረገ።

፬፡ ቍልቍልያኖስም ፡ አምላክ ፡ ይሰቀላልን ፡
ይሞታልን፡አለ፡ፊልያስም፡አዎን፡የዘላለም፡
ሕይወትን፡ይሰጠን፡ዘንድ፡ስለ፡እኛ፡ፍቅር፡
ሞተ፡አለው።

፭፡ቍልቍልያኖስም፡እንዲህ፡አለው፡እኔ፡እንዳ
ከበርኩህ፡ልጣላህም፡እንዳልፈለግሁ፡አላወ
ቅህምን ፡ አንተ ፡ በወገን ፡ የከበርከ ፡ እንደሆ
ንክ ፡ አውቃለሁና ፡ አሁንም ፡ ለአማልክት ፡
ሠዋ፡በክፉ፡አሟሟት፡እንዳትሞት፡አለው።
ፊልያስም ፡ እኔን፡ ደስ ፡ ማሰኘት ፡ ከወደድክ ፡
እንዲሠቃዩኝና፡እንዲገድሉኝ፡እዘዝ፡አለው፡
በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ በሰይፍ ፡ ራሱን ፡ እንዲቆ
ርጡት፡አዘዘ።

፰፡ ሊገድሉት፡ሲወስዱትም፡ዘመዶቹና፡የሀገር፡
ታላላቆች ፡ ወደርሱ ፡ መጡ ፡ ለመኰንኑም ፡
በመታዘዝ፡ለአማልክት፡እንዲሠዋ፡እጆቹን፡
እግሮቹን ፡ እየሳሙ ፡ ለመኑት ። እርሱ ፡ ግን ፡
የጌታዬ ፡ ክርስቶስን ፡ መከራ ፡ መስቀልን ፡
ልሸከም ፡ እሔዳለሁና፡ እናንተ ፡ አሳሳቾች ፡
ከእኔ፡ወግዱ፡ብሎ፡ገሠጻቸው።

፱፡ ከሚገድሉበትም ፡ ሲደርስ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡
ምሥራቅ ፡ መልሶ ፡ እጆቹን ፡ ዘርግቶ ፡ ክብር ፡
ይግባውና፡ወደ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ጸለየ ፡ ሕዝቡን ፡ አደራ ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ አስጠበ
ቀና ፡ ተሰናበተ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡
ቆረጡት፡የሰማዕትነት፡አክሊልንም፡ተቀበለ።

፲፡ለእግዚአብሔርም።ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በዚህ ፡ መስተጋድል ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማ
ረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላ
ለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

፲፮፡ ወእምዝ ፡ ጸሐፈ ፡ አባ ፡ ሳዊሮስ ፡ ስጣዌ ፡ መልእክቱ ፡ ለአባ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ እንዘ ፡ ይብል፡አአኵቶ፡ለእግዚአብሔር፡ዘኀረየከ፡ ለዛቲ ፡ ሢመት ፡ ክብርተ ፡ ለቤተ ፡ ክርስ ቲያን፡ከመ፡ትዕቀባ፡በርትዕት፡ሃይማኖት፡ ዘአጽንዕዋ፡ወሠርዕዋ፡አበዊነ፡ቅዱሳን፡፫፻ ፲ወ፰ቱ፡ርቱዐነ፡ሃይማኖት፡በሀገረ፡ኒቅያ። ወአለበዎ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይጽናዕ ፡ በዝንቱ ፡ ወኢይትገኃሥ፡ኢ፡ለየማን፡ወኢ፡ለፀጋም፡ ወዓዲ ፡ ይቤሎ ፡ መሀሮሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ ወትረ፡ከመ፡ይጽንዑ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ ርትዕት።

፲፯፡ ወሶበ፡በጽሐት፡መልእክቱ፡ለአባ፡ሳዊሮስ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ተፈሥሐ ፡ ባቲ ፡ ወአዘዘ፡ያንብብዋ፡በውስተ፡ኵሉ፡መካን፡ ወኮነ፡ዝንቱ፡አብ፡ዘይሜህሮሙ፡ለሕዝብ፡ ኵሎ፡አሚረ፡ወያነብብ፡ሎሙ፡መጻሕፍተ፡ ቅዱሳተ፡ወይኤዝዞሙ፡ለኵሎሙ፡ኤጲስቆ ጶሳት፡ወካህናት፡በእንተ፡ዐቂበ፡መርዔቶሙ፡ ወፈጺሞ፡ሑረቶ፡ሠናየ፡ወአሥመሮ ለእግ ዚአብሔር፡ወአዕረፈ፡በሰላም።

፲፰፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ትብጽሐነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፮፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ሳዊሮስ ፡ ለአባ ፡ ዲዮስ ቆሮስ፡የመልእክቱን፡መልስ፡እንዲህ፡ብሎ፡ ጻፈ። በኒቅያ፡ከተማ፡ተሰብስበው፡ሃይማኖ ታቸው፡የቀና፡ሦስት፡መቶ፡ዐሥራ፡ስም ንቱ፡ቅዱሳን፡አባቶቻችን፡በቀናች፡ሃይማ ኖት፡አጽንተው፡የሠሩዋትን፡ቤተ፡ክርስቲ ያኑን፡እንድትጠብቅ፡ለዚች፡ለከበረች፡አገ ልግሎት፡የመረጠህ፡እግዚአብሔርን፡አመ ሰግናዋለሁ። ዳግመኛም፡በዚሁ፡እንዲጸና፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ፈቀቅ ፡ እንዳ ይል፡አስገነዘበው፡ደግሞም፡በቀናች፡ሃይማ ኖት፡እንዲጸኑ፡ሕዝቡን፡ሁል፡ጊዜ፡አስተ ምራቸው፡አለው።

፲፯፡ የአባ፡ሳዊሮስም፡መልእክት፡ወደ፡አባ፡ዲዮ ስቆሮስ ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ተሰኘባት ፡ በሁሉ፡ቦታም፡እንዲአስተምሩባት፡አዘዘ፡ ይህም፡አባት፡ሕዝቡን፡ሁል፡ጊዜ፡የሚያስ ተምራቸው፡ሆነ። ሁል፡ጊዜም፡ቅዱሳት፡ መጻሕፍትን፡በማንበብ፡ያስተምራቸዋል፡ ኤጲስ ቆጶሳቱንና፡ካህናቱንም፡መንጋዎቻ ቸውን፡ስለ፡መጠበቅ፡ያዛቸዋል፡መልካም፡ አገልግሎቱንም ፡ አድርሶ ፡ እግዚአብሔ ርንም፡ደስ፡አሰኝቶ፡አረፈ።

፲፰፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከ ቱም፡ትድረሰን፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡ዲዮስቆሮስ፡ክሣደ፡ዐለውት፡ሰያፌ። ወበኀፀ፡ቃል፡ነዳፌ። ሃይማኖተ፡ሥሉስ፡ቅዱስ፡ ለመሐይምናን፡ታውፊ። ለነፍስየ፡አመ፡ጸአታ፡እምዓለም፡ኃላፊ። በመንግሥተ፡ሰማይ፡በላ፡ምስሌየ፡ አዕርፊ።

፲፱፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካረ፡ሢመቱ፡ለቅዱስ፡ እስጢፋኖስ ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ወቀዳሚ ፡ ሰማዕት፡በረከተ፡ጸሎቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፱፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የዲያቆናት ፡ አለቃ ፡ የሰማ ዕታት ፡ መጀመሪያ ፡ የሆነ ፡ ቅዱስ ፡ እስጢ ፋኖስ፡ለተሾመባት፡ቀን፡መታሰቢያ፡ናት፡ በጸሎቱም፡የምትገኝ፡በረከቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለእስጢፋኖስ፡እንተ፡ነጸረ፡በዐይኑ። እንዘ፡ወልድ፡ይነብር፡ለአብ፡ውስተ፡የማኑ። ከመ፡ ኖትያዊ፡ጠቢብ፡ኃዳፌ፡ሐመር፡በኪኑ። ባሕረ፡መጻሕፍት፡አመ፡ጸበተት፡ልሳኑ። ተቃውሞቶ፡ መዋግድ፡ስእኑ።

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ፲ወ፰ ለጥቅምት ።
በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡
ቴዎፍሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገረ ፡ እስክን
ድርያ ፡ እምኍልቆሙ ፡ ለአበው ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳ
ሳት ፡ ፳ወ፫ቱ ።

፪፡ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ተሠይመ ፡ በሳድስ ፡ ዓመተ ፡
መንግሥቱ ፡ ለቴዎዶስዮስ ፡ ንጉሥ ፡ ወነበረ ፡
በመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ፳ወ፰ተ ፡ ዓመተ ።

፫፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ኮነ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡
ዘተርጐመ ፡ መጻሕፍተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወእም
ኔሆሙ ፡ ራእየ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወመል
እክተ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወዓዲ ፡ ኮነ ፡ ኤጲፋ
ንዮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ላዕለ ፡ ደሴተ ፡ ቆጵሮስ ።

፬፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ተንሥኡ ፡ ፯ቱ ፡ ደቂቅ ፡ እም
ድኅረ ፡ ኖሙ ፡ ፫፻ተ ፡ ፸ወ፪ተ ፡ ዓመተ ።

፭፡ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ረድኡ ፡ ለአባ ፡ አትናቴዎስ ፡
ሐዋርያዊ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወተሐፅነ ፡ በኀቤሁ ፡
እንዘ ፡ ይትሜሀር ፡ መጻሕፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ወኵሎ ፡ ሥርዓታተ ። ወሶበ ፡ አዕረፈ ፡
አባ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእምቅ
ድሜሁ ፡ ተሠይመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላዕለ ፡ ሀገረ ፡
እስክንድርያ ፡ ወኮነ ፡ ማእምረ ፡ ወለባዌ ፡
ወደረሰ ፡ ድርሳናተ ፡ ብዙኃተ ፡ ወተግሣጻተ ፡
በእንተ ፡ ፍቅር ፡ ወበእንተ ፡ ምሕረት ፡ ወበ
እንተ ፡ ተዓቅቦ ፡ እምነሢአ ፡ ምሥጢራት ፡
ቅድሳት ፡ እምቅድመ ፡ ንስሐ ፡ ወበእንተ ፡
ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ወኵነኔ ፡ ዘለዓለም ፡ ዘተ
ደለወ ፡ ለኃጥአን ፡ ወካልአተ ፡ ድርሳናተ ፡
ዘይከውና ፡ በቍዔተ ።

፮፡ ወኮነ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ወልደ ፡ እኁቱ ፡ ለዝንቱ ፡
አብ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ወውእቱ ፡ ሐፀኖ ፡ ሠናየ ፡
ሕፅነተ ፡ ወመሀሮ ፡ ትምህርተ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ወእምዝ ፡ ፈነዎ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ ሰራብዮን ፡
ውእቱኒ ፡ መሀሮ ፡ ኵሎ ፡ ምግባረ ፡ መንፈሳዌ ።

፯፡ ወኮነ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለአባ ፡ አትናቴዎስ ፡
ቀዲሙ ፡ ሰምዖ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ቴዎፍሎስ ፡
ለአባ ፡ አትናቴዎስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ለእመ ፡
ረከብኩ ፡ መዋዕለ ፡ ሠናየ ፡ እምኮስተርኩ ፡
ዘንተ ፡ ወግረ ፡ ወእምሐነፅኩ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ለቅዱሳን ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ ወኤ
ልሳዕ ፡ ነቢይ ።

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥቅምት ፡ ዐሥራ ፡
ስምንት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ለአባቶች ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት ፡ ሃያ ፡ ሦስተኛ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡
ጳጳሳት ፡ የከበረ ፡ አባት ፡ ቴዎፍሎስ ፡ አረፈ ።

፪፡ ይህም ፡ አባት ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ በነገሠ ፡
በስድስተኛ ፡ ዓመት ፡ ተሾመ ፡ በወንጌላዊ ፡ ማር
ቆስም ፡ ወንበር ፡ ሃያ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ።

፫፡ በዘመኑ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍትን ፡ የተረጐመ ፡ ከእሳ
ቸውም ፡ የወንጌላዊ ፡ ዮሐንስን ፡ ራእይና ፡
የሐዋርያ ፡ ጳውሎስን ፡ መልእክት ፡ የተረጐመ ፡
ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ተነሣ ፡ ዳግመኛም ፡
ለደሴተ ፡ ቆጵሮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የሆነ ፡ ኤጲፋ
ንዮስ ፡ ነበረ ።

፬፡ በዘመኑም ፡ ሰባቱ ፡ ደቂቅ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡
ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከአንቀላፉ ፡ በኋላ ፡ ተነሡ ።

፭፡ ይህም ፡ አባት ፡ የሐዋርያዊ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
አባት ፡ አትናቴዎስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነው ፡
የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ መጻሕፍትና ፡ ሥር
ዓቱን ፡ ሁሉ ፡ እየተማረ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡
አደገ ። ከእርሱ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
አባ ፡ ጢሞቴዎስም ፡ በአረፈ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡
አባት ፡ በእስክንድርያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵ
ስና ፡ ተሾመ ፡ አዋቂና ፡ አስተዋይም ፡ ስለሆነ ፡
ስለ ፡ ፍቅር ፡ ስለ ፡ ርኅራኄ ፡ ከንስሐ ፡ በፊት ፡
ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ከመቀበል ፡ መጠበቅ ፡
ስለ ፡ ሚገባ ፡ ስለ ፡ ሙታን ፡ መነሣትና ፡ ለኃ
ጥአን ፡ ስለ ፡ ተዘጋጀ ፡ ስለዘላለማዊ ፡ ሥቃይ ፡
ሌሎችም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ድርሳናትንና ፡ ተግ
ሣጻትን ፡ ደረሰ ።

፮፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስም ፡ ለዚህ ፡ አባት ፡ ቴዎፍሎስ ፡
የእኅቱ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ በበጎ ፡ አስተ
ዳደግ ፡ አሳደገው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡
ትምህርት ፡ አስተማረው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡
ወደ ፡ አባ ፡ ሰራብዮን ፡ ላከው ፡ አባ ፡ ሰራብ
ዮንም ፡ መንፈሳዊ ፡ ተግባርን ፡ ሁሉ ፡ አስተ
ማረው ።

፯፡ በአትናቴዎስም ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲህ ፡
ሆነ ፡ በጎ ፡ ዘመን ፡ ባገኝ ፡ ይህን ፡ ኮረብታ ፡ ባስጠ
ረግሁት ፡ ነበር ። ለከበሩ ፡ ለመጥምቁ ፡ ዮሐ
ንስና ፡ ለነቢይ ፡ ኤልሳዕም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በሠራሁም ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ ይህ ፡ አባት ፡ ቴዎ
ፍሎስ ፡ አባ ፡ አትናቴዎስን ፡ ይሰማው ፡ ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ዴማስ ። ወካዕበ ፡ ሐነፀ ፡ በስመ ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በምሥራቀ ፡ ሀገር ፡ ወእምዝ ፡ ሐነፀ ፡ በስመ ፡ ሩፋኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ በውስተ ፡ ደሴት ፡ ወካልእተ ፡ ብዙኀተ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ።

፲፫ ፡ ወርእዮ ፡ ንጉሥ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ፍቅሮ ፡ ኀበ ፡ ሐኒፀ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጠዎ ፡ ኵሎ ፡ አብያተ ፡ ጣዖታት ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ ፡ ወተመጢዎ ፡ ውእቱ ፡ አንሀሎሙ ፡ ወሐነፀ ፡ ዲበ ፡ መካኖሙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአብያተ ፡ ነግድ ፡ ወወሀበ ፡ ካዕበ ፡ ምድሮሙኒ ።

፲፬ ፡ ወኮነ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ሶበ ፡ ያጠምቅ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ይሬኢ ፡ በቅድሜሁ ፡ በትረ ፡ መስቀል ፡ ዘብርሃን ፡ እንዘ ፡ የአትብ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ላዕለ ፡ እለ ፡ ይጠመቁ ።

፲፭ ፡ ወዝንቱ ፡ አብ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ወቴዎዶስዮስ ፡ ንጉሥ ፡ አመ ፡ ደቂቅ ፡ እሙንቱ ፡ ርእዩ ፡ ራእየ ፡ አሐደ ፡ በአሐቲ ፡ ሌሊት ፡ ክልኤሆሙ ፡ እንዘ ፡ የሐጥቡ ፡ ዕፀወ ፡ ወፈከርዋ ፡ ለይእቲ ፡ ራእይ ፡ ከመ ፡ ፩ እምኔሆሙ ፡ ይከውን ፡ ንጉሠ ፡ ወካልዑ ፡ ይከውን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወኮነ ፡ ከማሁ ።

፲፮ ፡ ወበቀዳሚት ፡ ዓመት ፡ ዘተሠይመ ፡ ባቲ ፡ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ንሜህር ፡ ሃይማኖተ ፡ ከመ ፡ ይጽሐፉ ፡ በመጽሐፍ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ወያምጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ወገብሩ ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ ።

፲፯ ፡ ወእምዝ ፡ ተንሥኡ ፡ ንጉሥ ፡ ወሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወአንበርዎሙ ፡ ለእሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ዲበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወጸለዩ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወከሠተ ፡ ሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ዘእንበለ ፡ እለ ፡ ይብሉ ፡ ወይትአመኑ ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ዕሩይ ፡ በመለኮት ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወሶቤሃ ፡ አዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ያውዕይዎሙ ፡ ለእሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ኑፉቃን ፡ ወለእለሂ ፡ ኑፉቃን ፡ ይሰድድዎሙ ፡ እምሀገረ ፡ መንግሥቱ ።

በቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ በሀገሩ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ሠራ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሊቀ ፡ መላእክት ፡ ሩፋኤል ፡ ስም ፡ በደሴት ፡ ውስጥ ፡ ሠራ ፡ ሌሎችንም ፡ ብዙዎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሳነፀ ።

፲፫ ፡ ንጉሡም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ለመሥራት ፡ ያለውን ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳቱን ፡ ፍቅር ፡ አይቶ ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ የጣዖታት ፡ ቤቶችን ፡ ሁሉንም ፡ ሰጠው ፡ እርሱም ፡ ተቀብሎ ፡ አፈረሳቸውና ፡ በቦታቸው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንና ፡ የእንግዶች ፡ ቤቶችን ፡ ሠራ ፡ ሁለተኛም ፡ ምድራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሰጠው ።

፲፬ ፡ ይህም ፡ አባት ፡ ቴዎፍሎስ ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀትን ፡ በሚያጠምቅ ፡ ጊዜ ፡ የብርሃን በትረ ፡ መስቀል ፡ በሚጠመቁት ፡ ላይ ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ ሲያማትብ ፡ ያይ ፡ ነበር ።

፲፭ ፡ ይህ ፡ አባት ፡ ቴዎፍሎስና ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ልጆች ፡ በሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለቱም ፡ በአንዲት ፡ ሌሊት ፡ አንዲት ፡ የሆነች ፡ ራእይን ፡ እነርሱ ፡ እንጨቶችን ፡ እንደሚለቅሙ ፡ አዩ ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ንጉሥ ፡ እንደሚሆን ፡ ሁለተኛውም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንደሚሆን ፡ ያቺን ፡ ራእይ ፡ ተረጐሟት ፡ እንዲሁም ፡ ሆነ ።

፲፮ ፡ ይህም ፡ አባት ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ በተሾመባት ፡ በመጀመሪያዪቱ ፡ ዓመት ፡ ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ሃይማኖትን ፡ እናስተምራለን ፡ የሚሉ ፡ ሁሉ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ በመጽሐፍ ፡ ጽፈው ፡ ወደርሱ ፡ እንዲአቀርቡ ፡ አዘዛቸው ፡ እንዳዘዛቸውም ፡ አደረጉ ።

፲፯ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ተነሥተው ፡ እነዚያን ፡ ጽሑፎች ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለዩ ፡ ጌታም ፡ ወልድ ፡ በመለኮቱ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከሚታመን ፡ በቀር ፡ ከውስጣቸው ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ የጸና ፡ እንደሌለ ፡ ገለጠላቸው ። በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ እሊህን ፡ የመናፍቃን ፡ መጻሕፍትን ፡ እንዲአቃጥሏቸው ፡ እነዚያንም ፡ መናፍቃን ፡ ከሚገዛው ፡ አገር ፡ እንዲአሳድዷቸው ፡ ንጉሥ ፡ አዘዘ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፡ ወዮሐንስኒ፡አፈ፡ወርቅ፡ያበዝኅ፡አንብቦ፡
መጻሕፍት፡ወሐቲተ፡ወበእንተዝ፡አውገዘ፡
መጻሕፍተ፡አውጋርዮስ፡ወፈነወ፡ኀበ፡
ዝንቱ፡አብ፡ቴዎፍሎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእ
ስክንድርያ፡ወኀበ፡ኤጲፋንዮስ፡ኤጲስ
ቆጶስ፡ዘቆጵሮስ፡ወኀበ፡ኵሎሙ፡ኤጲስቆ
ጶሳት፡ከመ፡ያውግዙ፡መጻሕፍተ፡አውጋ
ርዮስ።
፲፱፡ ወእምዝ፡ሶበ፡ፈጸመ፡ሑረቶ፡ሠናየ፡ወአ
ሥመሮ፡ለእግዚአብሔር፡ወአዕረፈ፡
በሰላም።
፳፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይም
ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡አብ፡ወበረከቱ፡
ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፰፡ ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅም፡መጻሕፍትን፡ማን
በብና፡መመርመር፡ያበዛ፡ነበር፡ስለዚህም፡
የአውጋርዮስን፡መጻሕፍት፡አወገዘ፡ያወ
ግዙ፡ዘንድም፡ወደ፡እስክንድርያ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ወደዚህ፡አባት፡ወደ፡ቴዎፍሎስ፡
ወደ፡ቆጵሮስ፡ኤጲስቆጶስ፡ወደ፡ኤጲፋ
ንዮስ፡ወደ፡ኤጲስቆጶሳት፡ሁሉ፡በየ
ሀገሩ፡ላከ።
፲፱፡ ከዚህም፡በኋላ፡መልካም፡ጉዞውን፡በፈጸመ፡
ጊዜ፡እግዚአብሔርንም፡አገልግሎ፡በሰላም፡
አረፈ።
፳፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በዚህ፡አባት፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከቱም፡
ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለቴዎፍሎስ፡ድልወ፡ዘተረክበ። በመንበረ፡ማርቆስ፡ይንበር፡ድኅረ፡አትናቴዎስ፡ሰከበ። በመንፈስ፡ቅዱስ፡ሎቱ፡ከመ፡አእምሮ፡ተውህበ። ይሬኢ፡ለለአሐዱ፡ጊዜ፡ያጠምቅ፡ሕዝበ። እንዘ፡በትረ፡ብርሃን፡የኀትም፡ከዊኖ፡ማዕተበ።

፳፩፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ኮነ፡ሰማዕተ፡ቅዱስ፡ሮማ
ኖስ፡መነኮስ፡በመዋዕለ፡አስቅልጵያኖስ፡
መኰንን፡ዘሰደዶሙ፡ለክርስቲያን።
፳፪፡ ወዝንቱ፡ቅዱስ፡ሶበ፡ሰምዐ፡ከመ፡መኰንን፡
ሰደዶሙ፡ለሕዝበ፡ክርስቲያን፡አስተጋብ
አሙ፡አሐተኔ፡ለኵሎሙ፡ሕዝበ፡ክርስ
ቲያን፡ምስለ፡ቀሳውስት፡ወዲያቆናት፡
ወመዓዶሙ፡በእንተ፡ሃይማኖተ፡ክርስቶስ፡
ወአጽንዖሙ።
፳፫፡ ወሰሚዖ፡አስቅልጵያኖስ፡ዘንተ፡አዘዘ፡ያምጽእዎ፡ወሶበ፡ቆመ፡ቅድሜሁ፡ይቤሎ፡አስቅ
ልጵያኖስ፡አንተኑ፡ሮማኖስ፡ክቡረ፡ዘመድ።
አውሥአ፡ቅዱስ፡ወይቤሎ፡ምንት፡ይበ
ቍዓኒ፡ክብረ፡ዘመድ፡ክብርየሰ፡ክርስቶስ፡
ውእቱ፡ወሰሚዖ፡መኰንን፡አዘዘ፡ይስ
ቅልዎ፡ወይስትርዎ፡መላትሒሁ። ወርእዮ፡
መኰንን፡ትዕግሥቶ፡አንከረ፡እስመ፡ኢነ
በበ፡ምንተኒ፡እንዘ፡ይሰትርዎ፡መላትሒሁ።
፳፬፡ ወሶቤሃ፡ይቤሎ፡ሮማኖስ፡ለመኰንን፡ናሁ፡
አምላኪየ፡ከሠተ፡አፉየ፡ከመ፡እዝልፍ፡
ዕበደከ፡እመ፡ተአምር፡ጽድቀ፡ነገረ፡
አዝዝ፡ያምጽኡ፡ሕፃነ፡ወይንግረነ፡ለእመ፡

፳፩፡ በዚችም፡ቀን፡ክርስቲያኖችን፡በአሳደደ፡
በመኰንን፡አስቅልጵያኖስ፡ዘመን፡የከበረ፡
መነኮስ፡ሮማኖስ፡በሰማዕትነት፡አረፈ።
፳፪፡ ይህም፡ቅዱስ፡የክርስቲያን፡ወገኖችን፡
መኰንኑ፡እንዳሳደዳቸው፡በሰማ፡ጊዜ፡ከቀ
ሳውስትና፡ከዲያቆናት፡ጋር፡የክርስቲያን፡
ወገኖችን፡ሁሉ፡በአንድነት፡ሰበሰባቸው፡
ስለ፡ክርስቶስ፡ሃይማኖትም፡መክሮ፡አጸ
ናቸው።
፳፫፡ አስቅልጵያኖስም፡ይህን፡ሰምቶ፡እንዲአ
መጡት፡አዘዘ፡በፊቱም፡በቆመ፡ጊዜ፡አስቅ
ልጵያኖስ፡በወገን፡የከበርክ፡ሮማኖስ፡አንተ፡
ነህን፡አለው፡ቅዱሱም፡የወገን፡ክብር፡ምን፡
ይጠቅመኛል፡ክብሬ፡ግን፡ክርስቶስ፡ነው፡
ብሎ፡መለሰለት። መኰንኑም፡ሰምቶ፡እንዲ
ሰቅሉትና፡ጉንጮቹን፡ይሰነጣጥቁ፡ዘንድ፡
አዘዘ፡ጉንጮቹንም፡ሲሰነጣጥቁት፡ምንም፡
አልተናገረምና፡መኰንኑ፡ትዕግሥቱን፡
አደነቀ።
፳፬፡ በዚያንም፡ጊዜ፡ሮማኖስ፡መኰንኑን፡
እንዲህ፡አለው፡እነሆ፡ስንፍናህን፡እዘልፍ፡
ዘንድ፡ፈጣሪዬ፡አፌን፡ከፈተ፡እውነት፡
ነገርን፡ብታውቅ፡ለእግዚአብሔር፡እንሰ

www.ethiopianorthodox.org

፳፱፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ተዝካሮሙ፡ ለዮሐንስ፡ ሰማዕት፡ ወአድራኒ፡ ወአርቴማዎስ፡ ወአርስጦስ፡ ወሉዲኖስ፡ ወአስማኒት፡ ወ፯ቱ፡ ደቂቃ፡ ወበረከቶሙ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

* * *

፩፡ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ፩ አምላክ፡ አመ፡ ፲ወ፱፡ ለጥቅምት፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ኮኑ፡ ቅዱስ፡ በርተሎሜዎስ፡ ወብእሲቱ፡ በመዋዕለ፡ ዲዮቅልጥያኖስ፡ ንጉሥ፡ ዐላዊ።

፪፡ ወእሉ፡ ቅዱሳን፡ እምሀገረ፡ ፍዩም፡ ዘእምዕራበ፡ ግብፅ፡ ወአስተዋደይዎሙ፡ ኀበ፡ መኰንን፡ ከመ፡ ክርስቲያን፡ እሙንቱ፡ ወለአከ፡ መኰንን፡ ወአብጽሖሙ፡ ወተሰአሎሙ፡ በእንተ፡ ሃይማኖት፡ ወእሙንቱ፡ በቅድሜሁ፡ ተአመኑ፡ በእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት።

፫፡ ወአዘዘ፡ መኰንን፡ ይክርዩ፡ ሎሙ፡ ዐዘቅተ፡ ዕሙቀ፡ ወይደይዎሙ፡ በህየ፡ ወይድፍንዎሙ፡ ሕያዋኒሆሙ፡ ወገብሩ፡ ቦሙ፡ በከመ፡ አዘዘ፡ መኰንን፡ ወፈጸሙ፡ ስምዖሙ፡ በዝንቱ፡ ወነሥኡ፡ አክሊለ፡ ስምዕ፡ በመንግሥተ፡ ሰማያት።

፬፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ ይምሐረነ፡ በጸሎቶሙ፡ ለሰማዕት፡ ወበረከቶሙ፡ ተሀሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡ አሜን።

፳፱፡ በዚችም፡ ቀን የሰማዕት፡ ዮሐንስ፡ የአድራኒ፡ የአርቴማዎስ፡ የአርስጦስ፡ የሉዲኖስ፡ የአስማኒትና፡ የሰባቱ፡ ልጆቿ፡ መታሰቢያቸው፡ ነው፡ በረከታቸውም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

* * *

፩፡ አንድ፡ አምላክ፡ በሚሆን፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ ጥቅምት፡ ዐሥራ ዘጠኝ፡ በዚች፡ ቀን፡ በከሀዲው፡ ዲዮቅልጥያኖስ፡ ዘመን፡ ቅዱስ፡ በርተሎሜዎስና፡ ሚስቱ፡ በሰማዕትነት፡ አረፉ።

፪፡ እሊህ፡ ቅዱሳንም፡ የግብጽ፡ ምዕራብ፡ ከሆነ፡ ፍዩም፡ ከሚባል፡ አገር፡ ናቸው፡ ክርስቲያኖችም፡ እንደሆኑ፡ በመኰንኑ፡ ዘንድ፡ ወነጇቿቸው፡ መኰንኑም፡ ልኮ፡ አስቀረባቸውና፡ ስለ፡ ሃይማኖት፡ ጠየቃቸው፡ እነርሱም፡ ክብር፡ ይግባውና፡ በጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በፊቱ፡ ታመኑ።

፫፡ መኰንኑም፡ ጥልቅ፡ ጉድጓድ፡ እንዲቆፍሩላቸው፡ በዚያም፡ እንዲጨምሩአቸውና፡ በሕይወታቸው፡ እንዲደፍኑባቸው፡ አዘዘ። መኰንኑም፡ እንዳዘዘ፡ አደረጉባቸው፡ በዚህም፡ ምስክርነታቸውን፡ ፈጽመው፡ የሰማዕትነት፡ አክሊልን፡ በመንግሥተ፡ ሰማያት፡ ተቀበሉ።

፬፡ ለእግዚአብሔርም፡ ምስጋና፡ ይሁን፡ እኛንም፡ በሰማዕታቱ፡ ጸሎት፡ ይማረን፡ በረከታቸውም፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ትኑር፡ ለዘላለሙ፡ አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ ለበርተሎሜዎስ፡ ወለብእሲቱ፡ ዘሕፅኑ። እለ፡ በክርስቶስ፡ ተአመኑ። መኰንን፡ ዐላዊ፡ በዘአክረየ፡ ወዓልያኑ። በውስተ፡ ዐዘቅት ፡ ዕሙቅ፡ እስከ፡ ኀቡረ፡ ተደፍኑ። እንዘ፡ ሕያዋን፡ እሮ፡ ምውታነ፡ ኮኑ።

፩፡ ወበዛቲ፡ ዕለት፡ ኮነ፡ ማኅበረ፡ ጉባዔ፡ ዘቤተ፡ ክርስቲያን፡ በሀገረ፡ አንጾኪያ፡ በእንተ፡ ጳውሎስ፡ ሳምሳጢ።

፪፡ ወዝንቱ፡ ጳውሎስ፡ ሶበ፡ ተሠይመ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ላዕለ፡ አሐቲ፡ ሀገር፡ እምአህጉረ፡ አንጾኪያ፡ ዘርዐ፡ ሰይጣን፡ ውስተ፡ ልቡ፡ ዘርዐ፡ እኩየ፡ ወኮነ፡ ዘየአምን፡ ከመ፡ ቃል፡ ዘአልቦ፡ አካል፡ ወጥንቱ፡ ለክርስቶስ፡ እማርያም፡ ወውእቱ፡ ዘፈጠሮ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ያድኅን፡ ቦቱ፡ ዓለመ፡ ወኢተዋሐደ፡ ምስለ፡ መለኮት፡ አላ፡ ወረደ፡ ላዕ

፩፡ በዚችም፡ ቀን፡ ስለ፡ ጳውሎስ፡ ሳምሳጢ፡ በአንጾኪያ፡ አገር፡ የቤተ፡ ክርስቲያን፡ የአንድነት፡ ስብሰባ፡ ተደረገ።

፪፡ ይህ፡ ጳውሎስም፡ ከአንጾኪያ፡ አገሮች፡ በአንዲቱ፡ አገር፡ ኤጲስቆጶስነት፡ በተሾመ፡ ጊዜ፡ ክፉ፡ ዘርን፡ ሰይጣን፡ በልቡ፡ ውስጥ፡ ዘራበት፡ አካላዊ፡ ቃልን፡ አካል፡ እንደሌለ፡ የክርስቶስም፡ ጥንት፡ መገኛው፡ ከማርያም፡ እንደሆነ፡ እርሱም፡ ዓለምን፡ ያድንበት፡ ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ የፈጠረው፡ እንደሆነ፡ ከመለኮትም፡ ጋር፡ ያልተዋሐደ፡ በላዩ፡ ወርዶ፡ በእ

www.ethiopianorthodox.org

ሌሁ፡ ወኀደረ ፡ ውስቴቱ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወኢኮነ ፡ ዘየአምን ፡ ኢ ፡ በወልድ ፡
ወኢ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፯፡ ወበእንተዝ ፡ ተጋብኡ ፡ ማኅበረ ፡ ኤጲስቆ
ጶሳት ፡ ወሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ዲዮናስ ፡ ዘእስ
ክንድርያ ፡ ወአባ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ዘሮሜ ፡ ኢክ
ህሉ ፡ ከመ ፡ ይብጽሑ ፡ ወይትጋብኡ ፡ ምስ
ሌሆሙ ፡ በእንተ ፡ ርሥአኖሙ ፡ ባሕቱ ፡
ጸሐፉ ፡ መልእክተ ።

፰፡ ወአባ ፡ ዲዮናስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ፡
ጸሐፈ ፡ መልእክተ ፡ ዘይብል ፡ እስመ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ወልዱ ፡ ወቃሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ዘዕሩይ ፡ ምስሌሁ ፡ በመለኮቱ ፡ ወውእቱ ፡ እም
ሠለስቱ ፡ ፩ወልድ ፡ ተሠገወ ፡ በእንቲአነ ፡ እም
እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡
ዘእንበለ ፡ ዘርዐ ፡ ብእሲ ፡ ወኮነ ፡ ሰብአ ፡
ፍጹመ ፡ ከማነ ፡ እንዘ ፡ ዕሩይ ፡ በመለኮቱ ፡
ምስለ ፡ አብ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወእም
ድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ኮኑ ፡ አሐደ ፡ ፪ቱ ፡ ጠባይዓት ፡
ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወኢትድምርት ። ወእንዘ ፡
ያጤይቅ ፡ ሰማዕተ ፡ እምነ ፡ መጻሕፍት ፡ ዘብ
ሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ ወፈነዋ ፡ ለይእቲ ፡ ምስለ ፡ ፪ቱ ፡
ቀሳውስት ፡ ማእምራን ።

፱፡ ወሶቤሃ ፡ ተጋብኡ ፡ ፲ወ፫ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡
ወእሉ ፡ ፪ ቀሳውስት ፡ ወተዋሥእዎ ፡ ለው
እቱ፡ ጳውሊ ፡ ሳምሳጢ ፡ ወአንበቡ ፡ በቅድ
ሜሁ ፡ መልእክቶ ፡ ለአባ ፡ ዲዮናስ ፡ ወተዋ
ሥእዎ ፡ ዓዲ ፡ በቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡
ዘይቤ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልዱ ፡ ወቃሉ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ ወፀዳለ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ከመ ፡
ውእቱ ፡ ህልው ፡ ወዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡
ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱሰ ፡ ኢተወክፈ ፡
ቃሎሙ ።

፲፡ ወእምዝ ፡ አውገዝዎ ፡ ወመተርዎ ፡ ወሰደድዎ ፡
ወለዙሎሙ ፡ እለ ፡ የአምኑ ፡ በትምህርቱ ።

፲፩፡ ወሠርዑ ፡ ለምእመናን ፡ ቀኖና ።

፲፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይዕ
ቀበነ ፡ እምስሒት ፡ በጸሎቶሙ ፡ ወበረከቶሙ ፡
ትብጽሐነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ አደረበት ፡ እንጂ ፡ ብሎ
የሚያምን ፡ ሆነ ፡ በወልድም ፡ ቢሆን ፡ በመን
ፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ቢሆን ፡ የሚያምን ፡ አልሆነም ።

፯፡ ስለዚህም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አንድነት ፡ ተሰ
በሰቡ ፡ የእስክንድርያ ፡ አባ ፡ ዲዮናስ ፡ የሮሜ ፡
አባ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ እሊህ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ስለ ፡
እርጅናቸው ፡ ከዚያ ፡ ደርሰው ፡ ከእርሳቸው ፡
ጋር ፡ ሊሰበሰቡ ፡ አልቻሉም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መል
እክትን ፡ ጻፉ ።

፰፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አበ ፡ ዲዮናስም ፡
እንዲህ ፡ የሚል ፡ መልእክትን ፡ ጻፈ ። የእግዚ
አብሔር ፡ ልጁም ፡ ቃሉም ፡ የሆነ ፡ ክርስቶስ ፡
በመለኮቱም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡
እርሱም ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ ወልድ ፡
ስለእኛ ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድን
ግል ፡ ማርያም ፡ ያለ ፡ ዘር ፡ ሥጋንና ፡ ነፍስን ፡
ነሥቶ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የሆነ፡ በመለኮቱ ፡
ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ትክክል ፡
ሲሆን ፡ እንደእኛ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሁኗል ፡ ከተ
ዋሕዶውም ፡ በኋላ ፡ ያለ ፡ መለያየትና ፡ ያለ ፡
መቀላቀል ፡ ሁለቱ ፡ ባሕርያት ፡ አንድ ፡ ሁነ
ዋል ፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ መጻሕፍት ፡ ምስክ
ሮችን ፡ ጠቅሶ ፡ እያስረዳ ፡ ጽፎ ፡ ይቺንም ፡
መልእክት ፡ ከሁለት ፡ ምሁራን ፡ ቀሳውስት ፡
ጋር ፡ ላካት ።

፱፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስቱ ፡ ኤጲስቆጶ
ሳትና ፡ እሊህ ፡ ሁለቱ ፡ ቀሳውስት ፡ ጉባኤ ፡
አድርገው ፡ ይህን ፡ ጳውሊ ፡ ሳምሳጢን ፡ አቅር
በው ፡ የአባ ፡ ዲዮናስን ፡ መልእክት ፡ በፊቱ ፡
አነበቡ ። ዳግመኛም ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ልጁም ፡ ቃሉም ፡ የሆነ ፡ የጌትነቱ፡
ነጸብራቅ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ የሐዋርያ ፡
ጳውሎስን ፡ ቃል ፡ በመጥቀስ ፡ እርሱ ፡ ከአብ ፡
ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ በትክክልነት ፡ እንደ
ሚኖር ፡ አስረዱት ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ቃላቸውን ፡
አልተቀበለም ።

፲፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በእርሱ ፡ ትምርት ፡ የሚያምኑ
ትን ፡ ሁሉ ፡ አውግዘው ፡ ከምእመናን ፡ ለይ
ተው ፡ አሳደዱት ።

፲፩፡ ለምእመናንም ፡ ሥርዓትን ፡ ሠሩ ።

፲፪፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡
በጸሎታቸው ፡ ከስሕተት ፡ ይጠብቀን ፡ በረከ
ታቸውም ፡ ትድረሰን ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

ለእሎንቱ፡መነኮሳት፡ዘአበይዎ፡ነሢኦቶ።

፲፰፡ ወነሥአ፡፩እምኔሆሙ፡ዘስሙ፡አባ፡ስምዖን፡ ለዮሐንስ፡ወረሰዮ፡ረድአ፡ወደመሮ፡ምስለ፡ ፪ቱ፡አርድእቱ።

፲፱፡ ወሶበ፡አእመረ፡አባ፡ስምዖን፡ከመ፡ቀርበ፡ ጊዜ፡ፍልሰቱ፡ጸውዖሙ፡ለደቂቁ፡ወይቤሎሙ፡ ንዑ፡ደቂቅየ፡እንግርክሙ፡ዘአርአየኒ፡እግ ዚአብሔር፡ ዘይከውን፡ላዕሌክሙ፡እምድ ኅረ፡ፍልሰትየ፡ለ፩እምኔክሙ፡ይመሥጦ፡ ዝዕብ፡ወካልኡኒ፡ይዘሮ፡ውስተ፡ዓለም፡ወለ ሣልሳይ፡ይወጽእ፡ስሙዓተ፡ዜናሁ፡ውስተ፡ ኵሉ፡ዓለም።

፳፡ ወእምዝ፡ነጸረ፡አረጋዊ፡ኀበ፡ገጸ፡ዮሐንስ፡ ወይቤሎ፡ጽናዕ፡አ፡ወልድየ፡በፍቅረ፡ክር ስቶስ፡ እስመ፡ውእቱ፡ኀረየከ፡ከመ፡ትኩን፡ አበ፡ለብዙኃን።

፳፩፡ ወእምድኅረ፡ዕረፍቱ፡ለአባ፡ስምዖን፡በሣ ልስት፡ዕለት፡ወጽአ፡አሐዱ፡ረድእ፡ውስተ፡ ዓለም፡ ወአውሰበ፡ብእሲተ፡ ወካልኡኒ፡ ኢተዐውቀ፡ኀበ፡በጽሐ፡ወቅዱስ፡ዮሐንስ፡ ተርፈ፡ ባሕቲቶ፡ ኀዘነ፡ ወተከዘ፡ ወይቤ፡ በልቡ፡እረድ፡እምዝንቱ፡ደብር፡እስአል፡ ዜና፡ አብያጽየ፡ ወዘንተ፡ ብሂሎ፡ ወጽአ፡ እምደብሩ፡ ወእንዘ፡ ይወርድ፡ እምውእቱ፡ ደብር፡ተቀበልዎ፡ጸባኢተ፡ጸይለም፡ወአሠ ርዎ፡ ምስለ፡ ፪ቱ፡ አንስት፡ ልሑያት፡ ወወ ሰድዎ፡ ወእንዘ፡ ሀለዉ፡ በፍኖት፡ ኃጥኡ፡ ማየ፡ ዘይሰትዩ፡ ሎሙኒ፡ ወለእንስሳሆሙ። ወይቤሎሙ፡አባ፡ዮሐንስ፡አምላኪየ፡ለእመ፡ አውጽአ፡ ለክሙ፡ ማየ፡ እምዝንቱ፡ ገዳም፡ ተሀድጉኒኑ፡ወይቤልዎ፡እወ። ወሶቤሃ፡ባረከ፡ አባ፡ ዮሐንስ፡ ዲበ፡ ምድር፡ እንዘ፡ ይብል፡ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ወነቅዐ፡ሎሙ፡ማይ፡ወሰትዩ፡ወረወዩ።

፳፪፡ ወይቤሎሙ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ፈንዉኒ፡በከመ፡ ኪዳንክሙ፡ወይቤልዎ፡ኢንኅድገከ፡ግሙራ፡ እስመ፡ ኢንረክብ፡ ዘከማከ፡ ወዘንተ፡ ብሂ ሎሙ፡አብጽሕዎ፡ኀበ፡ጸይለም፡ሀገሮሙ።

ገዳማቸው፡በእግዚአብሔር፡ ፈቃድ፡ደረሰ።

፲፰፡ ከእርሳቸውም፡ አንዱ፡ አባ፡ ስምዖን፡ የሚባ ለው፡ ዮሐንስን፡ ወስዶ፡ ደቀ፡ መዝሙሩ፡ አድርጎ፡ ከሁለቱ፡ ደቀ፡ መዛሙርቱ፡ ጋር፡ አኖረው።

፲፱፡ አባ፡ ስምዖን፡ የሚሞትበት፡ ጊዜ፡ እንደ፡ ቀረበ፡ በአወቀ፡ ጊዜ፡ ልጆቹን፡ ጠርቶ፡ ከሞትኩ፡በኋላ፡በእናንተ፡ላይ፡የሚሆነውን፡ እግዚአብሔር፡ ያሳየኝን፡እንግራችሁ፡ዘንድ፡ ልጆቼ፡ ኑ፡ አላቸውና፡ ከእናንተ፡ አንዱን፡ ጅብ፡ነጥቆ፡ይወስደዋል። ሁለተኛው፡ወደ፡ ዓለም፡ ተመልሶ፡ ይባክናል። የሦስተኛው፡ ግን፡ ዜናው፡ በዓለሙ፡ ሁሉ፡ ይሰማል፡ አላቸው።

፳፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ አረጋዊው፡ ስምዖን፡ ወደ፡ ዮሐንስ፡ ተመልክቶ፡ ልጄ፡ ሆይ፡ በክር ስቶስ፡ ፍቅር፡ ጽና፡ ለብዙዎች፡ አባት፡ ልትሆን፡እርሱ፡መርጦሃልና፡አለው።

፳፩፡ አባ፡ስምዖንም፡ከአረፈ፡በኋላ፡በሦስተኛው ቀን፡አንዱ፡ረድዕ፡ወደ፡ዓለም፡ተመልሶ፡ ሚስት፡ አገባ፡ ሁለተኛው፡ ወዴት፡ እንደ ደረሰ፡ አልታወቀም። አባ፡ ዮሐንስም፡ ብቻውን፡ ቀረ፡ ፈጽሞ፡ አዘነ፡ በልቡ፡ እንዲህ፡ አለ፡ የጓደኞቼን፡ ወሬ፡ እጠይቅ፡ ዘንድ፡ ከገዳም፡ ወጥቼ፡ ልውረድ፡ ይህንንም፡ ብሎ፡ ከገዳሙ ወጥቶ፡ ሲወርድ፡ የጸይለም፡ ጠረኞች፡ ተቀበሉት፡ ደም፡ ግባታቸው፡ ከሚአምር፡ ከሁለት፡ ሴቶች፡ ጋር፡ አሥረው፡ ወሰዱት፡ በጕዞም፡ ላይ፡ እያሉ፡ ለእንስሶቻቸውና፡ ለራሳቸው፡ የሚጠጡት፡ ውኃ፡ አጡ። አባ፡ ዮሐንስም፡ ከዚህ፡ በረሀ፡ ውስጥ፡ ፈጣሪዬ፡ ውኃን፡ ቢአ ወጣላችሁ፡ ትለቁኛላችሁን፡ አላቸው፡ አዎን፡ አሉት። በዚያንም፡ ጊዜ፡ አባ፡ ዮሐንስ፡በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ብሎ፡ በምድር፡ ላይ፡ አማተበ፡ ውኃም፡ፈልቆላቸው፡ጠጥተው፡ረኩ።

፳፪፡ የከበረ፡ዮሐንስም፡ቃል፡ኪዳን፡እንደ፡ገባች ሁልኝ፡ አሰናብቱኝ፡ አላቸው፡ እነርሱም፡ እንዳንተ፡ ያለ፡ አናገኝምና፡ ከቶ፡ አንለ ቅህም፡ አሉት። ይህንንም፡ ብለው፡ ወደ፡ አገራቸው፡ወደ፡ጸይለም፡አደረሱት።

www.ethiopianorthodox.org

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለዮሐንስ ፡ በሥልጣነ ፡ ቃሉ ፡ ዘአዘዛ ። ይኩን ፡ ደመ ፡ ለፈለገ ፡ ጸይለም ፡ ውኂዛ ። ወሰላም ፡ ለረድኡ ፡ ጽጉየ ፡ ሠናይ ፡ መዓዛ ። እንተ ፡ ተውህበ ፡ ለሞት ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ወሬዛ ። ለነፍስ ፡ አእላፍ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቤዛ ።

፳፯፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ካዕበ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለጻድቃን ፡ እለ ፡ መጥራ ፡ እለ ፡ ተጠብሑ ፡ በመጥባሕት ፡ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ወተዝካሩ ፡ ዓዲ ፡ ለይምርሐነ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወለእሉኒ ፡ ጻድቃን ፡ እለ ፡ መጥራ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ማዕሰ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ኢተሌለየ ፡ ወመግነዞሙ ፡ ኢበልየ ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፳፯፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ዳግመኛ ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ለታረዱ ለመጥራ ፡ ጻድቃን ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ። ደግሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ይምርሐነ ፡ ክርስቶስ ፡ መታሰቢያው ፡ ነው ፡ እሊህም ፡ የመጥራ ፡ ጻድቃን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ቆዳቸው ፡ ከሥጋቸው ፡ አልተለያየም ፡ መግነዛቸውም ፡ አላረጀም ። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ቸኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

<u>አርኬ</u>

ሰላም ፡ ለይምርሐ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ዓሙ ። በቅብዓ ፡ ክህነት ፡ ወንግሥ ፡ ዘአባላቲሁ ፡ ተኀትሙ ። እስከ ፡ ብዙኃን ፡ ሕዝብ ፡ እመንክራቲሁ ፡ ተደሙ ። መንገለ ፡ ተክዕወ ፡ ወነጥበ ፡ ደሙ ። በቈለ ፡ ወይን ፡ ዘመንክር ፡ ጣዕሙ ።

ሰላም ፡ ለስምዖን ፡ መንፈስ ፡ ትንቢት ፡ ዘተዓጽፈ ። ዜና ፡ እርዳኢሁ ፡ ሠለስቱ ፡ በከመ ፡ ተጽሕፈ ። አሐዱ ፡ በተዘርዎ ፡ ውስተ ፡ ዓውደ ፡ ዓለም ፡ ኀለፈ ። ወካልኡኒ ፡ ልብሰ ፡ ምንኵስና ፡ ገደፈ ። በገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዮሐንስ ፡ ተርፈ ።

*  *  *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ሁ ፡ ለጥቅምት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡ ወዐቢይ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐፂር ።

፪፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አበዊሁ ፡ ዘእምላዕላይ ፡ ግብጽ ፡ ወእሙንቱ ፡ ፈራህያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢኮነ ፡ ሎሙ ፡ ወልድ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ወኢ ፡ ብዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ዳዕሙ ፡ ብዑላን ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ወሐፀንዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ይሜህርዎ ፡ ሠናየ ፡ ሕፅነተ ።

፫፡ ወሶበ ፡ ኮኖ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ፲ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ሆከቶ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ከመ ፡ ይልበስ ፡ አስኬማ ፡ መላእክት ፡ ዘውእቱ ፡ ልብሰ ፡ ምንኵስና ።

፬፡ ወበጺሖ ፡ ህየ ፡ ተራከቦ ፡ ለአሐዱ ፡ አረጋዊ ፡ አብ ፡ ዘስሙ ፡ ባይሞይ ፡ ወሰገደ ፡ ሎቱ ፡ ዮሐንስ ፡ ወሰአሎ ፡ ከመ ፡ ይትወከፎ ፡ ኀቤሁ ፡ አረጋዊኒ ፡ ይቤሎ ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ ኢርቱዕ ፡ ለከ ፡ ከመ ፡ ትንበር ፡ ዝየ ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ገዳም ፡

*  *  *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥቅምት ፡ ሃያ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ክቡርና ፡ ገናና ፡ የሆነ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐፂር ፡ አረፈ ።

፪፡ የዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ወላጆቹ ፡ ከላይኛው ፡ ግብጽ ፡ ናቸው ፡ እነርሱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩ ፡ ናቸው ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ በቀር ፡ ልጅ ፡ የላቸውም ፡ የዚህ ፡ ዓለምም ፡ ብልጽግና ፡ ቢሆን ፡ የላቸውም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ባለጸጎች ፡ ናቸው ፡ ይህንንም ፡ ቅዱስ ፡ እያስተማሩ ፡ በበጎ ፡ አስተዳደግ ፡ አሳደጉት ።

፫፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ዕድሜው ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ አነሣሥታው ፡ የመላእክት ፡ የሆነ ፡ አስኬማን ፡ ይለብስ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ሔደ ፡ ይኸውም ፡ የምንኵስና ፡ ልብስ ፡ ነው ።

፬፡ ከዚያም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ የሚባለውን ፡ አንዱን ፡ አረጋዊ ፡ አባት ፡ ተገናኘው ፡ ዮሐንስም ፡ ሰገደለትና ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ እንዲቀበለው ፡ ለመነው ፡ ሽማግሌውም ፡ አባት ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ያንተ ፡ በዚህ ፡ መኖር ፡ ልክ ፡ አይደለም ፡

ዕፅብት ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይትጌበሩ ፡ በእደዊሆሙ ፡ ይጸውሙ ፡ ወይጼልዩ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ። ወሶበሂ ፡ ይሰክቡ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ዘእንበለ ፡ መንጸፍ ፡ ይሰክቡ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ወሬዛ ፡ ኢትክል ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ዐፀባ ፡ አላ ፡ ባሕቱ ፡ ይኄይሰከ ፡ ትትመየጥ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወትሕየው ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ሠናየ ፡ ሕይወተ ።

፭፤ ወይቤሎ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ኦ ፡ አቡየ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተወከፈኒ ፡ ወኢትሚጠኒ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ መጻእኩ ፡ ከመ ፡ እኩን ፡ ታሕተ ፡ ጽላሎትከ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ ኢይገብር ፡ ምንተኒ ፡ ግብረ ፡ ዘእንበለ ፡ ይሰአል ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሶቤሃ ፡ ሰአሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዊር ፡ ይኰሥት ፡ ሎቱ ፡ ግብሮ ፡ ወአስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይቤሎ ፡ ይቤለከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተወከፎ ፡ ለዝንቱ ፡ እኁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይከውን ፡ ንዋየ ፡ ኅሩየ ።

፮፤ ወእምዝ ፡ ነሥኦ ፡ ለዮሐንስ ፡ ሐዊር ፡ ወአብኦ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአምጽአ ፡ አልባሳተ ፡ ምንኵስና ፡ ወጸለየ ፡ ላዕሌሆን ፡ ሠለስተ ፡ መዓልተ ፡ ወሠለስተ ፡ ሌሊተ ። ወእምዝ ፡ አስተርአዮ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአተበ ፡ ላዕለ ፡ አልባስ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ወአረጋዊ ፡ አልበሶ ፡ ለአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ኪያሆን ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ።

፯፤ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ወጠነ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ተጸምዶተ ፡ ወተጋድሎተ ፡ አረጋዊሰ ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ ፈቀደ ፡ ያመክሮ ፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ዘበጦ ፡ ወሰደዶ ፡ እምበዓቱ ፡ ወይቤሎ ፡ ኢይፈቅድ ፡ እኅድር ፡ ምስሌከ ፡ ወቀዱስኒ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ቆመ ፡ በአፍአ ፡ ማዕከለ ፡ መርሕብ ፡ ወለለጽባሑ ፡ ይወጽእ ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ ወይዘብጦ ፡ ወይብሎ ፡ ኢይፈቅድ ፡ እርአይከ ፡ ውእቱሰ ፡ ይቤሎ ፡ ስረይ ፡ ሊተ ፡ ኦ ፡ አቡየ ፡ ወይሰግድ ፡ ታሕተ ፡ እገሪሁ ።

፰፤ ወአመ ፡ ሳብዕት ፡ ዕለት ፡ ወጽአ ፡ አረጋዊ ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርእዮሙ ፡ ለሰብዓቱ ፡ መላእክት ፡ እንዘ ፡ የዓውድዎ ፡ ለዮሐንስ ፡ ወያስተቄጽልዎ ፡ በአክሊላት ፡ ወእምአሜሃ ፡ ኀደገ ፡ አመክሮቶ ፡ ወአብኦ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ።

በዚች ፡ ገዳም ፡ የሚኖሩ ፡ በእጆቻቸው ፡ ይሠራሉ ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ይጾማሉ ፡ ይጸልያሉ ፡ በሚተኙም ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ምንጣፍ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይተኛሉ ፡ አንተ ፡ ወጣት ፡ ጐልማሳ ፡ ስለሆንክ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ችግር ፡ አትችልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ተመልሰህ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በጎ ፡ አኗኗርን ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ ይሻልሃል ፡ የዚች ፡ ገዳም ፡ ኑሮ ፡ ጭንቅ ፡ ነውና ፡ አለው ።

፭፤ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ እኔ ፡ በጥላህ ፡ ሥር ፡ ልኖር ፡ መጥቼአለሁና ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ተቀበለኝ ፡ እንጂ ፡ አትመልሰኝ ፡ ይህም ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ እግዚአብርሔርን ፡ ሳይጠይቅ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ አይሠራምና ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ ይገልጥለት ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዊር ፡ እግዚብሔርን ፡ ለመነው ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ተገልጦለት ፡ እርሱ ፡ የተመረጠ ፡ መሳሪያ ፡ ይሆናልና ፡ ተቀበለው ፡ ብሎሃል ፡ አለው ።

፮፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዊርን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስገባው ፡ የምንኵስና ፡ ልብሶችንም አምጥቶ ፡ በላያቸው ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ ጸለየ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ተገልጾ ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ በልብሶቹ ፡ ላይ ፡ አማተበ ፡ ሽማግሌውም ፡ እነዚያን ፡ ልብሶች ፡ ለአባ ፡ ዮሐንስ ፡ አለበሰው ።

፯፤ ከዚያቺም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ተጋድሎንና ፡ አገልግሎትን ፡ ጀመረ ፡ አባ ፡ ባይሞይም ፡ ሊፈትነው ፡ ወደደ ፡ በአንዲትም ፡ ቀን ፡ ደብድቦ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ መኖር ፡ አልሻም ፡ ብሎ ፡ ከበዓቱ ፡ አስወጥቶ ፡ አባረረው ፡ የከበረ ፡ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ ከሜዳ ፡ መካከል ፡ በውጭ ፡ ቆመ ፡ በየቀኑም ፡ በጥዋት ፡ እየወጣ ፡ ከእዚህ ፡ ላይህ ፡ አልሻም ፡ እያለ ፡ ይመታዋል ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ብሎ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ይሰግዳል ፡

፰፤ በሰባተኛዪቱም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊሔድ ፡ ሽማግሌው ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ ወጣ ፡ አባ ፡ ዮሐንስንም ፡ ሰባት ፡ መላእክት ፡ ከበው ፡ አክሊላትን ፡ ሲያቀዳጁት ፡ አያቸው ፡ ከዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ መፈተኑን ፡ ተወው ፡ ወደ ፡ መኖሪያውም ፡ አስገባው ።

www.ethiopianorthodox.org

፱፡ ወእምዝ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ፡ ረከበ ፡ አባ ፡
ባይሞይ፡ዕፀ ፡ይቡሰ፡ነሥአ፡ወወሀቦ፡ለአባ፡
ዮሐንስ ፡ ወይቤሎ ፡ ትክሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ዕፅ ፡
ወስቅዮ ፡ ማየ ፡ እስከ ፡ ይሠርፅ ፡ ወይፈሪ ፡
ወተአዘዘ፡አባ፡ዮሐንስ፡ለአቡሁ፡ወነሢኦ፡
ውእተ፡ዕፀ፡ተከሎ፡ወሰቀዮ፡ማየ፡ለለዕለቱ፡
፪ተ፡ጊዜ፡ወማዩኒ፡ርኁቅ፡መጠነ፡፲ወ፪ቱ፡
ምዕራፍ።

፲፡ወእምድኅረ፡ሠለስቱ፡ዓመት፡ሠረፀ፡ውእቱ፡
ዕፅ፡ወኮነ፡ዕፀ፡ዐቢየ፡ወጸገየ፡ወፈረየ፡ፍሬ፡
ጥዑመ ፡ ወእምነ ፡ ፍሬሁ፡ ነሥአ ፡ አባ ፡
ባይሞይ ፡ ወወሰደ ፡ሎሙ ፡ ለአረጋውያን ፡
ቅዱሳን ፡ መነኰሳት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ ፡
ወብልዑ ፡ እምፍሬ ፡ ተአዛዚ ፡ ወትሑት ፡
ወእሙንቱ ፡ ርእዮሙ ፡ ዘንተ ፡ መንክረ ፡ አን
ከሩ ፡ ወሰብሕዎ ፡ለእግዚአብሔር ፡ ዘይሁብ ፡
ዘከመዝ ፡ ጸጋ ፡ ለእለ ፡ ይትኤዘዙ ፡ ለመምህራ
ኒሆሙ።

፲፩፡ወተእኀዘ፡አባ፡ባይሞይ፡ውስተ፡ጽኑዕ፡ደዌ፡
መጠነ ፲ወ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ ወይትለአኮ ፡ አባ ፡
ዮሐንስ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ ሠምረ፡ ያመ
ክሮ ፡ በዝንቱ ፡ ደዌ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቊርባነ ፡
ኅሩየ፡ በከመ ፡ ውእቱ ፡ አመክሮ ፡ ለአባ ፡
ዮሐንስ፡

፲፪፡ ወበጊዜ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለአባ ፡ ባይሞይ ፡ አስተጋ
ብአሙ ፡ ለአረጋውያን ፡ ቅዱሳን ፡ መነኰሳት ፡
ወአኀዞ ፡ ለአባ ፡ ዮሐንስ ፡ ወመጠዎ ፡ ሎሙ ፡
እንዘ ፡ ይብል ፡ ንሥእዎ ፡ ወዕቀብዎ ፡ እስመ ፡
ውእቱ ፡ መልአክ ፡ ወአኮ ፡ ሰብእ ። ወለው
እቱኒ፡ ይቤሎ ፡ ካዕበ ፡ እምድኅረ ፡ ዕረፍትየ ፡
ኅድር፡ውስተ፡መካን፡ኀበ፡ተከልከ፡ውእተ፡
ዕፀ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ ዘአስተዳለወ ፡
ለከ፡እግዚአብሔር ፡ ወብዙ ኃን ፡ ይድኅኑ ፡
በእዴከ ፡ ወይቀውም ፡ ዝክርከ ፡ በህየ ፡ ወይ
ወጽእ፡ዜናከ፡ውስተ፡ኵሉ፡ዓለም፡ወዘንተ፡
ብሂሎ፡አዕረፈ፡ወቀበርዎ፡በክብር።

፲፫፡ወእምዝ፡ሖረ፡ቅዱስ፡አባ፡ዮሐንስ፡ወኀደረ፡
ኀበ፡ውእቱ፡መካን፡በከመ፡ይቤሎ፡አረጋዊ፡
አቡሁ ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ ወተጋደለ ፡ ገድለ ፡
ዐቢየ ፡ እስከ ፡ ተሰምዐ ፡ ዜናሁ ፡ ፈድፋደ ፡
ውስተ፡ኵሉ፡ዓለም።

፱፡ከዚህም፡በኋላ፡በአንዲት፡ቀን፡አባ፡ባይሞይ፡
የደረቀ ፡ ዕንጨት ፡ አግኝቶ ፡ ወስዶ ፡ ለአባ ፡
ዮሐንስ ፡ ሰጠውና ፡ ይህን ፡ ዕንጨት ፡ ትተከ
ለው፡እስከሚበቅልና፡እስከሚአፈራ፡ድረስ፡
ውኃን፡አጠጣው፡አለው ። አባ፡ዮሐንስም፡
ለአባቱ፡ታዛዥ፡በመሆን፡ተቀብሎ፡ወስዶ፡
ተከለው ፡ በየቀኑም ፡ሁለት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡
ያጠጣዋል ፡ ውኃውም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ምዕ
ራፍ፡ያህል፡የራቀ፡ነው።

፲፡ ከሦስት ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ ያ ፡ ዕንጨት ፡
አቈጥቍጦ ፡ በቀለ ፡ ታላቅም ፡ ዛፍ ፡ ሁኖ ፡
አብቦ ፡ ጣፋጭ ፡ ፍሬን ፡ አፈራ ። አባ ፡ ባይሞ
ይም፡ከፍሬው፡ለቅዱሳን፡አረጋውያን፡ወሰደ
ላቸውና፡የታዛዥንና፡የትሑቱን፡ፍሬ፡እነሆ፡
ብሉ ፡ አላቸው ፡ እነርሱም ፡ ይህን ፡ ድንቅ ፡
ተአምር ፡ አይተው ፡ አደነቁ ፡ ለመምህሮ
ቻቸው ፡ ለሚታዘዙ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጸጋ ፡
የሚሰጥ፡እግዚአብሔርንም፡አመሰገኑት።

፲፩፡ አባ ፡ ባይሞይም ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡
ያህል ፡ በጽኑዕ ፡ ደዌ ፡ ውስጥ ፡ ተይዞ ፡ ኖረ ፡
አባ፡ ዮሐንስም ፡ ያገለግለው ፡ ነበር ፡ አባ፡
ዮሐንስን፡እንደፈተነው፡የተመረጠ፡መሥ
ዋዕትን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ደዌ ፡ እንዲ
ፈትን፡እግዚአብሔር፡ፈቅዷልና፡

፲፪፡ በሚሞትበትም ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ ቅዱ
ሳን፡ አረጋውያን ፡ መነኰሳትን ፡ ሰበሰባ
ቸውና ፡ አባ ፡ ዮሐንስንም ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡
እርሱ፡ሰው፡ያይደለ፡መልአክ፡ነውና፡ተቀ
ብላችሁ ፡ ጠብቁት ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ። እርሱ
ንም ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ከእረፍቴ ፡
በኋላ፡ያን፡ዕንጨት፡ወደ፡ተከልክበት፡ቦታ
በዚያ ፡ ኑር ፡ እግዚአብሔር ፡ ላንተ ፡ ያዘጋ
ጀልህ ፡ ነውና ፡ ብዙዎችም ፡ በአንተ ፡ እጅ ፡
ይድናሉ ፡ መታሰቢያህም ፡ በዚያ ፡ ጸንቶ ፡
ይኖራል፡ዜናህም፡በዓለም፡ሁሉ፡ይወጣል፡
ይህንንም ፡ ተናግሮ ፡ አረፈ ፡ አክብረውም ፡
ቀበሩት።

፲፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ አረ
ጋዊ ፡ አባቱ ፡ አባ ፡ ባይሞይ ፡ እንደነገረው ፡
ወደዚያ፡ቦታ፡ሒዶ፡ኖረ፡ዜናውም፡በዓለም፡
ሁሉ፡እጅግ፡እስከ፡ተሰማ፡ድረስ፡ታላቅ፡
ተጋድሎን፡ተጋደለ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፡ ወተሠይመ፡ አበ፡ ምኔት፡ ላዕለ፡ቤተ፡ክርስ
ቲያን፡ ዘዚአሁ፡ ወእንዘ፡ ያነብር፡ ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ አባ፡ ቴዎፍሎስ፡ እደዊሁ፡ ላዕለ፡
ርእሱ፡ በጊዜ፡ ሢመቱ፡ ተሰምዐ፡ ቃል፡
እምሰማይ፡ ዘይብል፡ አክዮስ፡ አክዮስ፡
አክዮስ፡ዝ፡ብሂል፡ይደልዎ፡ይደልዎ፡ይደ
ልዎ።
፲፭፡ ወሶበ፡ ይቄድስ፡ ቍርባነ፡ ለእለ፡ ኢይደ
ልዎሙ፡ነሢአ፡ቅዱስ፡ቍርባን፡ይፈልጦሙ፡
ወይብሎሙ፡ ይእዜኒ፡ ሑሩ፡ ወነስሑ፡ ወእ
ምዝ፡ ተመየጡ፡ ወንሥኡ፡ መሠጢረ፡ ቅድ
ሳት።
፲፮፡ ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡አባ፡ዮሐንስ፡ፈነዎ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ አባ፡ ቴዎፍሎስ፡ ውስተ፡ ሀገረ፡
ባቢሎን፡ያምጽእ፡ሎቱ፡ሥጋሆሙ፡ለቅዱሳን፡
ሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ ወዝንቱኒ፡ ሀሎ፡ ጽሑፈ፡
አመ፡፲ለወርኀ፡ግንቦት።
፲፯፡ ወበአሐቲ፡ ዕለት፡ መጽአ፡ ፩ዱ፡ መነኮስ፡
ኀበ፡ በዓቱ፡ ለአባ፡ ዮሐንስ፡ ወረከቦ፡ እንዘ፡
ይነውም፡ ወመላእክተ፡ እግዚአብሔር፡ይት
ጋፍዑ፡ ላዕሌሁ፡ ወያንዘፈዝፉ፡ ክነፊሆሙ፡
ወይብሎ፡ ፩ዱ፡ ለካልኡ፡ ኅድገኒ፡ አንብር፡
ክንፍየ፡ ላዕሌሁ፡ ወዘንተ፡ ርእዮ፡ አእኰቶ፡
ለእግዚአብሔር።

፲፰፡ ወእምድኅረዝ፡ ሶበ፡ መጽኡ፡ በርበር፡ አረማ
ውያን፡ ኀበ፡ ገዳመ፡ አስቄጥስ፡ ከመ፡ ያመዝ
ብሩ፡ አብያተ፡ መንኮሳት፡ ወሖረ፡ አባ፡
ዮሐንስ ኀበ፡ ቍልዝም፡ ኀበ፡ ደብረ፡ አባ፡
እንጦንስ፡ ውኀደረ፡ በህየ፡ በገቦሁ፡ ለዐፀድ፡
ዘደብረ፡ አባ፡ እንጦንስ፡ ወአምጽአ፡ ሎቱ፡
እግዚአብሔር፡ ብእሴ፡ ምእመነ፡ ወኮነ፡
ዘይትለአኮ፡ እስከ፡ ዕለተ፡ ዕረፍቱ።

፲፱፡ ወእምዝ፡ ሶበ፡ ፈቀደ፡ እግዚአብሔር፡ከመ፡
ያዕርፎ፡ እምፃማ፡ ዝንቱ፡ ዓለም፡ ፈነዎሙ፡
ኀቤሁ፡ ለቅዱሳኒሁ፡ ጻድቃን፡ አባ፡ እንጦንስ፡
ወአባ፡ መቃርስ፡ ወአባ፡ ጳኵሚስ፡ ወምስ
ሌሆሙ፡ አባ፡ ባይሞይ፡ አቡሁ፡ መንፈሳዊ፡
ከመ፡ ይናዝዝዎ፡ ወያጠይቅዎ፡ ፍልሰቶ፡ እም
ዓለም፡ ኀላፊ። ወእሙንቱ፡ ናዘዝዎ፡ ወይ
ቤልዎ፡ ተፈሣሕ፡ እስመ፡ አስተዳለወ፡ ለከ፡
እግዚአብሔር፡ ትፍሥሕተ፡ ዘኢየሐልቅ፡ ወን

፲፬፡ በራሱ፡ ቤተ፡ ክርስቲያንም፡ አበ፡ ምኔት፡
ሁኖ፡ ተሾመ፡ በሹመቱም፡ ጊዜ፡ ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ አባ፡ ቴዎፍሎስ፡ እጆቹን፡ በራሱ፡
ላይ፡ ሲጭን፡ አክዮስ፡ አክዮስ፡ አክዮስ፡
የሚል፡ ቃል፡ ከሰማይ፡ ተሰማ፡ ይህም፡
ይገባዋል፡ ይገባዋል፡ ይገባዋል፡ ማለት፡
ነው።
፲፭፡ የቍርባን፡ቅዳሴን፡በሚቀድስ፡ጊዜ፡ቅዱስ፡
ቍርባንን፡መቀበል፡የማይገባቸውን፡ይለያ
ቸዋል፡ ዛሬስ፡ ሒዳችሁ፡ንስሐ፡ ግቡ፡
ከዚያም፡ በኋላ፡ ተመልሳችሁ፡ ሥጋውን፡
ደሙን፡ተቀበሉ፡ይላቸዋል።
፲፮፡ ይህን፡ አባ፡ዮሐንስንም፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡
ቴዎፍሎስ፡ የቅዱሳን፡ የሠለስቱ፡ ደቂቅን፡
ሥጋቸውን፡ እንዲአመጣለት፡ ወደ፡ ባቢ
ሎን፡ ልኮታል፡ ይህም፡ በግንቦት፡ ወር፡ በዐ
ሥረኛው፡ቀን፡ተጽፎአል።
፲፯፡ በአንዲትም፡ ዕለት፡ አንድ፡ መነኰስ፡ ሊጐበ
ኘው፡ ወደ፡ በዓቱ፡ ቢመጣ፡ ኣባ፡ ዮሐንስን፡
ተኝቶ፡ አገኘው፡ የእግዚአብሔርም፡መላእ
ክት፡ በላዩ፡ ይጋፉ፡ ክንፎቻቸውንም፡ ያርገ
በግቡ፡ ነበር፡ አንዱም፡ ሌላውን፡ ተወኝ፡
ክንፌን፡ በላዩ፡ ላኑር፡ ይለዋል፡ ይህንንም፡
አይቶ፡ እግዚአብሔርን፡አመሰገነው።
፲፰፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ የመነኰሳቱን፡ መንደር፡
ሊበረብሩ፡ የበርበር፡ አረማውያን፡ ወደ፡
አስቄጥስ፡ ገዳም፡ በመጡ፡ ጊዜ፡ አባ፡
ዮሐንስም፡ወደ፡አባ፡እንጦንስ፡ገዳም፡ወደ፡
ቍልዝም፡ ሔደ፡ በዚያም፡ በአባ፡ እንጦንስ፡
ገዳም፡ በጐኑ፡ በአለ፡ቦታ፡ ተቀመጠ፡ እስከ
ሚያርፍባትም፡ ቀን፡ ድረስ፡ የሚያገለ
ግለው፡ አንድ፡ የታመነ፡ ሰውን፡ እግዚ
አብሔር፡ አመጣለት።
፲፱፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ ከዚህ፡ ዓለም፡ ድካም፡ ሊአሳ
ርፈው፡ በወደደ፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ቅዱ
ሳን፡ ጻድቃኖቹን፡ አባ፡ እንጦስን፡ አባ፡
መቃርስን፡ አባ፡ ጳኵሚስን፡ ከእርሳቸውም፡
ጋር፡ መንፈሳዊ፡ አባቱ፡ አባ፡ ባይሞይንን፡
ያረጋጉትና፡ ከዚህ፡ ከኃላፊው፡ ዓለም፡ መለ
የቱን፡ ይነግሩት፡ ዘንድ፡ ወደርሱ፡ ላካቸው።
እነርሱም፡ እንዲህ፡ ብለው፡ አረጋጉት፡ ደስ፡
ይበልህ፡ እግዚአብሔር፡የማያልቅ፡ ተድላ፡
ደስታን፡ አዘጋጅቶልሃልና፡ ክብር፡ ይግባ

www.ethiopianorthodox.org

ሕነ፡ንመጽእ፡ኀቤከ፡ካዕበ፡በዕለተ፡እሑድ፡ ወንነሥእከ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሎቱ ፡ ስብ ሐት፡ወባረክዎ፡ወተሰውጡ፡እምኀቤሁ።

፳፡ ወበዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ፈነዎ ፡ ለወዓሊሁ ፡ ኀበ ፡ አሐዱ፡ዐፀድ፡ወእምዝ፡ደወየ፡ደዌ፡ንስቲተ፡ ወበሌሊተ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ጊዜ ፡ ይነቁ ፡ ዶርሆ፡ መጽኡ ፡ እሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ፡ማኅበረ፡ቅዱሳን፡ወሠራዊተ፡መላ እክትኒ፡በጽሑ፡ኀቤሁ፡ወርእዮ፡ተፈሥሐ፡ ወመጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለእግ ዚአብሔር፡ወአዕረግዋ፡ለነፍሱ፡መላእክት፡ በዐቢይ፡ክብር፡እንዘ፡ይሴብሑ፡ወይዜምሩ፡ ወውእተ፡ጊዜ፡መጽአ፡ረድኡ፡ወርእዮሙ፡ ለቅዱሳን ፡ ማኅበረ ፡ ጻድቃን ፡ ወማኅበረ ፡ መላእክት ፡ እንዘ ፡ የዐውድዋ ፡ ወያዐርግዋ ፡ ለነፍሱ ፡ እንዘ ፡ ይዜምሩ ፡ ወቆመ ፡ መጠነ ፡ አሐቲ፡ ሰዓት ፡ እንዘ ፡ ያነክር ። ወመጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ አሐዱ ፡ እመላእክት ፡ ወአጠየቆ ፡ ስሞሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ለለአሐዱ ፡ እንዘ ፡ ይኤ ምሮ፡በአጽባዕቱ፡ወይብሎ፡ዝ፡አባ፡ዕገሌ፡ ወተሰአሎ ፡ ረድእ ፡ ለመልአክ ፡ ወይቤሎ ፡ መኑ ፡ ዘእምቅድሜሆሙ ፡ ዘይበርህ፡ ገጹ ፡ ከመ፡ፀሐይ፡አውሥአ፡ወይቤሎ፡ዝንቱሰ፡ አባ፡እንጦንስ፡አበ፡ኵሎሙ፡መንከሳት።

፳፩፡ ወሶበ፡ቦአ፡ውስተ፡በዓት፡ውእቱ፡ረድእ፡ ረከቦ፡ለአባ፡ዮሐንስ፡ስጉዶ፡ዲበ፡ምድር፡ ወአዕረፈ፡ወበከየ፡ላዕሌሁ፡ብካየ፡ዐቢየ። ወእምዝ ፡ አፍጠነ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ዐፀደ ፡ መነከሳት ፡ ወነገሮሙ ፡ ዘከመ ፡ አዕረፈ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐፂር ፡ ወመጽኡ ፡ እሙንቱ፡አኃው፡ወገነዝዎ፡ወፆሩ፡ሥጋሁ፡ በክብር ፡ ወወሰድዎ ፡ ወአንበርዎ ፡ ውስተ ፡ ዐፀዶሙ።

፳፪፡ወነበረ፡በህየ፡እስከ፡አፍለስዎ፡ውሉዱ፡ወአ ንበርዎ፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ዘዚአሁ፡ ኀበ፡ተከለ፡ዕፀ፡ይቡሰ፡ወአሥረፀ።

፳፫፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡አብ፡ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ውና ፡ ጌታችንም ፡ እንዳዘዘ ፡ በእሑድ ፡ ቀን ፡ ሁለተኛ ፡ ወዳንተ ፡ መጥተን ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ሕይወት፡እንወስድኻለን፡ባርከውትም፡ከእ ርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሱ ።

፳፡ በዐርብ ፡ ቀንም ፡ አገልጋዩን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ቦታ፡ላከው፡ከዚህም፡በኋላ፡ጥቂት፡ታመመ፡ በእሑድም ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡ ዶሮ ፡ ሲጮህ ፡ እሊያ፡ቅዱሳን፡ከሁሉም፡ቅዱሳን፡ማኅበር፡ ጋር ፡ መጡ፡ የመላእክትም ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ ወደርሱ ፡ መጡ ፡ በአያቸውም ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሎት፡በእግዚአብሔር፡እጅ፡ነፍሱን፡ሰጠ፡ መላእክትም፡እያመሰገኑና፡እየዘመሩ፡በታ ላቅ ፡ ክብር ፡ ነፍሱን ፡ አሳረጓት ፡ በዚያንም፡ ጊዜ ፡ ረድኡ ፡ መጣ ፡ ነፍሱንም ፡ ከበው ፡ እያ መሰገኑ ፡ ሲያሳርጓት ፡ የጻድቃንና ፡ የመላእ ክትን ፡ ማኅበር ፡ አይቶ ፡ እያደነቀ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ቆመ ። ከመላእክትም ፡ አንዱ ፡ ወደርሱ ፡ መጥቶ ፡ የቅዱሳንን ፡ ስማቸውን ፡ በመጥራት ፡ በጣቱ ፡ እያመለከተ ፡ ይህ ፡ አባ ፡ ዕገሌ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አስረዳው ፡ ረድኡም ፡ መልአኩን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው፡ ይህ ፡ በፊታቸው ፡ ያለ ፡ ፊቱ ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ የሚ በራ ፡ ማን ፡ ነው ፡ መልአኩም ፡ የመነኰሳቱ ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ አባ ፡ እንጦንስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት።

፳፩፡ ወደ ፡ በዓቱም ፡ ያ ፡ ረድእ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰግዶ ፡ እንዳረፈ ፡ አባ ፡ ዮሐንስን፡አገኘውና፡ታላቅ፡ልቅሶን፡በላዩ፡ አለቀሰ፡ከዚያም፡በኋላ፡ወደ፡መነኰሳቱ፡ መንደር፡ፈጥኖ፡በመሔድ፡ቅዱስ፡አባ፡ ዮሐንስ፡ሐፂር፡እንደ፡አረፈ፡ነገራቸው። እነዚያም፡መነኰሳት፡አክብረው፡ገንዘው፡ ሥጋውን ፡ ተሸክመው ፡ ወስደው ፡ በቦታ ቸው፡አኖሩት።

፳፪፡ የደረቀ ፡ ዕንጨት ፡ ተክሎ ፡ በአበቀለበት ፡ ላይ፡ በሠራት ፡ የራሱ ፡ በሆነች ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ውስጥ ፡ ልጆቹ ፡ ከዚህ ፡ አፍልሰው ፡ ወስደው ፡ እስከ ፡ አኖሩት ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ኖረ።

፳፫፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከ ቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ሰላም፡እብሎ፡በሕቁ።ለዮሐንስ፡ሐዊር፡ዘነዊኅ፡ኂሩተ፡ጽድቁ።እምትርሲተ፡ዓለም፡ማሳኒ፡በዘይርኅቁ።ከመ፡ያለብዎሙ፡ለእለ፡ኃሠሡ፡ወጽሕቁ።ግብረ፡ምንዅስና፡ርእየ፡ቀዊሞ፡ዕራቁ።

፳፬፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተዝካረ፡ዕረፍቱ፡ለዐቢይ፡ነቢይ፡ኤልሳዕ፡ዘትርጓሜ፡ስሙ፡መድኅን፡ወዐቃቢ።

፳፭፡ ወውእቱ፡እምሀገረ፡አሜሁላ፡ዘእምነገደ፡ይሳኮር፡ወተነበየ፡ብዙኀ፡ወገብረ፡መንክራተ፡ወይቤልዎ፡ለኤልሳዕ፡ሰብአ፡ይእቲ፡ሀገር፡ናሁ፡ንብረታ፡ለዛቲ፡ሀገር፡ሠናይ፡በከመ፡ትሬኢ፡እግዚእነ፡ወማየ፡ብሔራሰ፡እኩይ፡ውእቱ፡አንስትኒ፡ይመክና፡በሰትዮቱ፡

፳፮፡ ወይቤሎሙ፡ኤልሳዕ፡አምጽኡ፡ሊተ፡መስብክተ፡ሐዲሰ፡ወደዩ፡ውስቴቱ፡ፄወ፡ወአምጽኡ፡ሎቱ።

፳፯፡ ወሖረ፡ኤልሳዕ፡ኀበ፡ነቅዐ፡ማይ፡ወሠጠ፡ውስቴቱ፡ዝኩ፡ፄወ፡ወይቤ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ፈወስክዎ፡ለዝንቱ፡ማይ፡ከመ፡አልቦ፡ዘይመውት፡ወአልቦ፡ዘይመክን፡እምኔሁ።

፳፰፡ ወእምይእቲ፡አሚር፡ተፈወሰ፡ውእቱ፡ማይ፡እስከ፡ዮም፡በከመ፡ነበበ፡ኤልሳዕ።

፳፱፡ ወብዙኅ፡ተአምሪሁ፡ለዝንቱ፡ነቢይ፡ኤልሳዕ፡ውእቱኒ፡አንጽሖ፡ለንዕማን፡ሶርያዊ፡እምለምጹ፡ወአንሥአ፡ሙታነ፡አሐደ፡በሕይወቱ፡ወካልአ፡እምድኅረ፡ሞቱ፡ወፈጺሞ፡መዋዕለ፡ትንቢቱ፡አዕረፈ፡በሰላም።

፴፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ለነቢይ፡ኤልሳዕ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፳፬፡ በዚችም፡ቀን፡የስሙ፡ትርጓሜ፡ጠባቂና፡አዳኝ፡የሆነ፡የታላቅ፡ነቢይ፡የኤልሳዕ፡የዕረፍቱ፡መታሰቢያ፡ነው።

፳፭፡ እርሱም፡አሜሁላ፡ከሚባል፡አገር፡ከይሳኮር፡ነገድ፡ነው፡ብዙ፡ትንቢትን፡ተናግሮአል፡ብዙ፡ተአምራትንም፡አደርጓል።የኢያሪኮም፡ሰዎች፡ኤልሳዕን፡ጌታችን፡እንደምታያት፡የዚች፡አገር፡ኑሮዋ፡ያማረ፡የተወደደ፡ነው፡የአገሩ፡ውኃ፡ግን፡ክፉ፡ነው፡ሴቶች፡ሲጠጡት፡ይመክናሉ፡አሉት፡

፳፮፡ ኤልሳዕም፡ጨው፡ጨምራችሁ፡አዲስ፡ሸክላ፡አምጡልኝ፡አላቸው፡እነርሱም፡አመጡለት።

፳፯፡ ኤልሳዕም፡ወደ፡ውኃው፡ምንጭ፡ሒዶ፡ያንን፡ጨው፡በውስጡ፡ጨመረውና፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡እርሱን፡ከመጠጣት፡የተነሣ፡የሚሞት፡እንዳይኖር፡የሚመክንም፡እንዳይኖር፡ይህን፡ውኃ፡ለወጥኩት፡አለ፡አላቸው።

፳፰፡ ከዚያችም፡ቀን፡በኋላ፡ኤልሳዕ፡እንደተናገረ፡እስከ፡አሁን፡ድረስ፡ያ፡ውኃ፡ተለወጠ።

፳፱፡ የዚህ፡የነቢይ፡ኤልሳዕ፡ተአምራቱ፡ብዙ፡ነው፡የሶርያውን፡ሰው፡ንዕማንን፡ከለምጹ፡ያነጻው፡እርሱ፡ነው፡ሁለት፡ሙታንን፡አንዱን፡በሕይወት፡ሳለ፡ሌላውንም፡ከሞተ፡በኋላ፡አስነሥቷል።የትንቢቱንም፡ወራት፡ፈጽሞ፡በሰላም፡አረፈ።

፴፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡በነቢይ፡ኤልሳዕ፡ጸሎት፡ይማረን በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለኤልሳዕ፡ዘአድምዐ፡ስመ።መድኅነ፡ወዐቃቤ፡ዘተተርጕመ።ህየንተ፡ኤልያስ፡ነቢይ፡አመ፡ለእስራኤል፡ቆመ።ፈወሰ፡ወአጥዐመ፡ማየ፡ሕሱመ።ወበቅራፈ፡ዕፅ፡አውጽአ፡ማኅፄ፡ሥጡመ።

* * *

፩፡ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፳ወ፭ለጥቅምት፡በዛቲ፡ዕለት፡

* * *

፩፡ አንድ፡አምላክ፡በሚሆን፡በአብ፡በወልድ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥቅምት፡ሃያ፡

www.ethiopianorthodox.org

መፍቀሬ፡እግዚአብሔር፡ወልዱ፡ለንጉሥ፡
ሰይፈ፡አርዕድ፡ወዓዲ፡ይሰመይ፡ቈስጠን
ጢኖስሃ።
፲፭፡ ወዝንቱ፡ቅዱስ፡ወልደ፡አበው፡መሲሐ
ውያን፡ፈራህያነ፡እግ" አብሔር፡እምል
ሒቃነ፡ሀገረ፡ምስር፡ወሐፀንዎ፡ሠናየ፡
ሕፀንተ፡እንዘ፡ይሜህርዎ፡ትምህርተ፡ቤተ፡
ክርስቲያን፡እስከ፡ደለዎ፡ይሠየም፡መዓርገ፡
ዲቁና።
፲፮፡ ወእምዝ፡ሶበ፡አሠነየ፡ተልእኮተ፡በሢመተ፡
ዲቁና፡ደለዎ፡ይሠየም፡ቀሲስ፡ወተሠይመ፡
ቀሲስ።
፲፯፡ ወኮነ፡ጽሙደ፡በጾም፡ወበጸሎት፡ወበፈሪሀ፡
እግዚአብሔር፡ወመፍቀሬ፡ነዳያን፡ወምስ
ኪናን፡አሜሃ፡ደለዎ፡ሢመተ፡ጵጵስና፡ዘሐ
ዋርያት፡ወበሥምረቱ፡ለእግዚአብሔር፡
ተሠይመ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ውስተ፡ሀገር፡
ቅድስት፡ኢየሩሳሌም፡ወኮነ፡ይሜህሮሙ፡
ለሕዝብ፡በትሕትና፡ወበፈሪሀ፡እግዚአ
ብሔር።
፲፰፡ ወእሙንቱሂ፡ኮኑ፡ዘያፈቅርዎ፡ፈድፋደ፡
በእንተ፡ቅድስናሁ፡ወአርአያሁኒ፡ወመክ
ሥተ፡አፉሁ፡ሠናይ፡ከመ፡መልአከ፡እግዚ
አብሔር።
፲፱፡ ወእምድኅረ፡ነበረ፡ዲበ፡መንበረ፡ሢመቱ፡
ኅዳጣተ፡ዓመታተ፡አምጽአ፡ላዕሌሁ፡
ሰይጣን፡ምክንያተ፡እስከ፡አርኀቆ፡እመ
ንበሩ።
፳፡ ውእቱኬ፡በመዋዕሊሁ፡ለሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእስ
ክንድርያ፡አባ፡ማርቆስ፡እስመ፡ንጉሠ፡
ኢትዮጵያ፡አሕለቆሙ፡ለተንባላት፡እለ፡
ውስተ፡ምኵናኑ፡በእንተ፡ዐሊዎቶሙ፡
በእንተዝ፡አገበሮ፡ንጉሠ፡ምስር፡ለሊቀ፡
ጳጳሳት፡አባ፡ማርቆስ፡ከመ፡ይፈኑ፡መል
እክተ፡ኀበ፡ንጉሠ፡ኢትዮጵያ፡ከመ፡
ኢያሕስም፡ላዕሌሆሙ፡ለተንባላት፡እለ፡
ውስተ፡ምኵናኑ።
፳፩፡ አባ፡ማርቆስኒ፡ተማከረ፡ምስለ፡መኳንንት፡
ወኤጲስቆጳሳት፡ወልሒቃነ፡ሀገር፡በእንተ፡
እለ፡ይፌንዉ፡ኀበ፡ንጉሠ፡ኢትዮጵያ፡ወኀ
ረይዎሙ፡ለእሉ፡አበው፡ከዋክብት፡ብሩ
ሀን፡አባ፡ዮሐንስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘኢየሩ
ሳሌም፡ወአባ፡ሳዊሮስ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘሀገረ፡

ሰይፈ፡አርዕድ፡ደግሞ፡ቈስጠንጢኖስ፡ለሚ
ባል፡ልጁ፡በሆነ፡በንጉሣችን፡በዳዊት፡
ዘመን፡አረፈ።
፲፭፡ ይህም፡ቅዱስ፡ከምስር፡አገር፡ታላላቆች፡እግ
ዚአብሔርን፡የሚፈሩ፡የክርስቲያኖች፡አባ
ቶች፡ልጅ፡ነው። የዲቁና፡መዓርግንም፡
ለመሾም፡እስከ፡ተገባው፡ድረስ፡የቤተ፡ክር
ስቲያንን፡ትምህርት፡እያስተማሩ፡በበጎ፡
አስተዳደግ፡አሳደጉት።
፲፮፡ ከዚህም፡በኋላ፡በዲቁናው፡ሹመት፡አገልግ
ሎቱን፡በአሳመረ፡ጊዜ፡የቅስና፡መዓርግ፡
የሚገባው፡ሁኖ፡ቅስና፡ተሾመ።
፲፯፡ በጾም፡በጸሎት፡እግዚአብሔርንም፡በመፍ
ራት፡የተጠመደ፡ሁኖ፡ድሆችንና፡ችግረ
ኞችን፡የሚወዳቸው፡የሚረዳቸው፡ሆነ፡
ያን፡ጊዜ፡የሐዋርያት፡የሆነች፡የጵጵስና
ሹመት፡የምትገባው፡ሁና፡በከበረች፡አገር፡
በኢየሩሳሌም፡በእግዚአብሔር፡ፈቃድ፡
ሊቀ፡ጵጵስና፡ተሾመ፡ሕዝቡንም፡በፈሪሀ፡
እግዚአብሔርና፡በትሕትና፡የሚያስተምራቸው፡
ሆነ።
፲፰፡ እነርሱም፡ስለ፡ቅድስናው፡እጅግ፡የሚወ
ዱት፡ሆኑ፡መልኩና፡የአንደበቱ፡አገላለጥ፡
እንደ፡እግዚአብሔር፡መልአክ፡ያማረ፡
ነበር።
፲፱፡ በሹመቱም፡ጥቂት፡ዘመናት፡ከኖረ፡በኋላ
ከመንበረ፡ሢመቱ፡እስከ፡አራቀው፡ድረስ፡
በላዩ፡ሰይጣን፡ምክንያትን፡አመጣ።
፳፡ ይህም፡እንዲህ፡ነው፡በእስክንድርያ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡በአባ፡ማርቆስ፡ዘመን፡በግዛቱ፡
ውስጥ፡ያሉ፡እስላሞች፡ስለ፡ዐመፁበት፡
የኢትዮጵያ፡ንጉሥ፡ፈጅቷቸው፡ነበርና፡
ስለዚህ፡በግዛቱ፡ውስጥ፡በሚኖሩ፡እስላ
ሞች፡ላይ፡ክፉ፡እንዳያደርግ፡ለኢትዮጵያ፡
ንጉሥ፡መልእክት፡እንዲልክ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡
ማርቆስን፡የምስር፡ንጉሥ፡አዘዘው።

፳፩፡ አባ፡ማርቆስም፡ወደ፡ኢትዮጵያ፡ንጉሥ፡
ስለሚላኩ፡ሰዎች፡ከመኳንንቱ፡ከኤጲስ
ቆጶሳቱና፡ከሀገር፡ታላላቆች፡ሽማግሌዎች፡
ጋር፡ተማክሮ፡እሊህን፡ብሩሀን፡ከዋክብት፡
የኢየሩሳሌም፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ዮሐንስን፡
የምስር፡ኤጲስቆጶስ፡አባ፡ሳዊሮስን፡በእውቀ

www.ethiopianorthodox.org

ምስር፡በእንተ፡አእምሮቶሙ፡ወለብዎቶሙ፡ ወቅድስናሆሙ ፡ ወአገበርዎሙ ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ኀበ ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ።

፳፪፡ እሙንቱሰ ፡ ተአዚዞሙ ፡ መጽኡ ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወሰሚያ ፡ ንጉሥ ፡ ምጽአቶሙ ፡ ተፈሥሐ ፡ ፈድፋደ ፡ ወፈነወ ፡ ወዐልያኒሁ ፡ ምስለ ፡ አብቅልት ፡ ይትቀበልዎሙ ፡ ለእሉ ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ፡ ወሶበሂ ፡ በጽሑ ፡ ኀቤሁ ፡ ተአምኆሙ ፡ በዐቢይ ፡ፍሥሓ ፡ ወተባረከ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወአክበሮሙ ፡ ክብረ ፡ ዐቢየ ። ወእሙንቱኒ ፡ መጠውዎ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክቱ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡ ውእቱኒ፡አንበባ፡ወከሠተ፡ሎሙ፡ከመ፡ውእቱ፡ ተአዛዚ፡ለቃለ፡ሊቀ፡ጳጳሳት።

፳፫፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ፈቀዱ ፡ ገቢአ ፡ ኀበ ፡ መናብርቲሆሙ ፡ ወሕዝቦሙ ፡ ከልአሙ ፡ እግዚእ ፡ ንጉሥ ፡ ገቢአ ፡ በእንተ ፡ አፍቅሮቱ ፡ ኪያሆሙ፡በይነ፡ቅድስናሆሙ፡ወመዓዛ፡ትምህርቶሙ ፡ እስመ ፡ ኮኑ ፡ እሙንቱ ፡ በኀቤሁ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብሐር ፡ወብሩህ ፡ ገጾሙ፡ከመ፡ፀሐይ።

፳፬፡ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ሶበ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያዕርፎ ፡ እምፃማ ፡ ዝንቱ፡ዓለም፡ፈነወ፡ዲቤሆሙ፡ደዌ፡ንስቲተ፡ ወቦቱ፡አዕረፈ፡በሰላም።

፳፭፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ፡በጸሎቶሙ፡ለቅዱሳን፡አበው፡ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

***

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ፡አመ፡፳ወ፪ለጥቅምት፡በዛቲ፡ዕለት፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ሉቃስ፡ ጠቢብ፡ወማእምር።

፪፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ኮነ ፡ እምኊልቆሙ ፡ ለ፸ወ፪ አርድእት፡ዘዘከሮሙ፡ወንጌል፡ቅዱስ።

፫፡ ወውእቱ ፡ ኮነ ፡ ዘይትለአኮሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ጴጥሮስ፡ወጳውሎስ፡በኵሉ፡ግብር፡በእንተ፡

ታቸው ፡ በአስተዋይነታቸውና ፡ በቅድስናቸው ፡ መረጡአቸው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሥም፡ይሔዱ፡ዘንድ፡ግድ፡አሏቸው።

፳፪፡ እነርሱም ፡ ታዛገሮች ፡ ሁነው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጡ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥም ፡ መምጣታቸውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ እሊህንም ፡ ቅዱሳን ፡ አባቶች ፡ ይቀበሏቸው ፡ ዘንድ ፡ አሽከሮቹን ፡ በቅሎዎችን ፡ አስይዞ ፡ ላከ ፡ በመጡም ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ፡ ሰላምታ ፡ አቀረበላቸው ፡ ከእርሳቸውም ፡ ቡራኬን ፡ ተቀበለ ፡ ታላቅ ፡ ክብርንም ፡ አከበራቸው ። እነርሱም ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ማርቆስን ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጡት ፡ እርሱም ፡ ተቀብሎ ፡ አንብቦ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ቃል ፡ ታዛዥ ፡ መሆኑን፡ገለጠላቸው።

፳፫፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሀገረ ፡ ስብከታቸውና ፡ ወደ፡ሕዝባቸው፡መመለስን፡በአሰቡ፡ጊዜ፡ ስለ ፡ ቅድስናቸውና ፡ ስለ ፡ ትምህርታቸው ፡ ጣዕም፡ስለ፡ወደዳቸው፡የተከበረው፡ንጉሥ፡ መመለስን ፡ ከለከላቸው ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡መላእክት፡ ሁነዋልና ፡ ፊታቸውም ፡ እንደ ፡ ፀሐይ ፡ ያበራል።

፳፬፡ ከጥቂት ፡ ወራትም ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ድካም ፡ ሊአሳርፈው ፡ እግዚአብሔር ፡ በወደደ፡ ጊዜ ፡ በላዩ ፡ ደዌ ፡ ላከበት ፡ በዚያውም፡ ደዌ፡በሰላም፡አረፈ።

፳፭፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በቅዱሳን ፡ አባቶች ፡ ጸሎት ፡ ይማረን፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

***

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥቅምት ፡ ሃያ ፡ ሁለት፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ብልህ ፡ ጥበበኛ ፡ የሆነ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ሉቃስ ፡ በሰማዕትነት ፡ አረፈ።

፪፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ የከበረ ፡ ወንጌል ፡ ከመዘገባቸው፡ ከሰባ ፡ ሁለቱ ፡ አርድእት ፡ ውስጥ ፡ የተቆጠረ፡ነው።

፫፡እርሱም፡ወንጌልን፡ስለማስተማር፡በሥራው፡ ሁሉ ፡ ሐዋርያት ፡ ጴጥሮስንና ፡ ጳውሎስን ፡ የሚአገለግላቸው ፡ ሆነ ፡ ለታአፊላም ፡ ወንጌ

www.ethiopianorthodox.org

ትምህርተ፡ወንጌል፡ወውእቱ፡ዘጸሐፈ፡ለታ
አፊላ፡ወንጌለ፡ወዜናሆሙ፡ለሐዋርያት።

፭፡ ወእምድኅረ፡ቅትለቶሙ፡ለቅዱሳን፡ጴጥሮስ፡ወጳውሎስ፡ኮነ፡ይሰብክ፡ውስተ፡ሀገረ፡ሮሜ፡ወይጽሕፍ፡መልእክተ፡ለመሐይምናን፡ከመ፡ይጽንኡ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ርትዕት፡ወበእንተዝ፡ተሰነዓዉ፡መምለክያነ፡ጣዖት፡ምስለ፡አይሁድ፡ወቆሙ፡ቅድሜሁ፡ለኔሮን፡ንጉሥ፡ወጸርሑ፡በእንተ፡ሉቃስ፡ሐዋርያ፡እንዘ፡ይብሉ፡እስመ፡ዝንቱ፡ሉቃስ፡አብአሙ፡ለብዙኃን፡ሰብእ፡ውስተ፡ትምህርቱ፡በሥራይ፡ወአዘዘ፡ኔሮን፡ንጉሥ፡ከመ፡ያምጽእዎ፡ለሉቃስ፡ውስተ፡ዐውደ፡ምኵናን።

፮፡ ወአእሚሮ፡ሉቃስ፡ሐዋርያ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ከመ፡በጽሐ፡ጸአቱ፡እምዝንቱ፡ዓለም፡ወሖረ፡ኀበ፡ጽንፈ፡ባሕር፡ወበህየ፡ረከቦ፡ለአሐዱ፡ብእሲ፡አረጋዊ፡አሥጋሬ፡ዓሣ፡ወወሀቦ፡መጻሕፍቲሁ፡ወጦማራቲሁ፡ወይቤሎ፡ዕቀብ፡እሎንተ፡መጻሕፍተ፡እስመ፡እማንቱ፡ይበቍዓከ፡ወያበጽሐከ፡ውስተ፡ፍኖተ፡እግዚአብሔር።

፯፡ ወሶበ፡ቀርበ፡ወቆመ፡ቅድመ፡ኔሮን፡ንጉሥ፡ይቤሎ፡ንጉሥ፡እስከ፡ማእዜኑ፡ታስሕቶሙ፡ለሕዝብ፡በሥራይከ፡ወአውሥአ፡ቅዱስ፡ሉቃስ፡ኢኮንኩ፡አንሰ፡መሠርየ፡አላ፡አነ፡ሐዋርያሁ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ሕያው።

፰፡ ወይቤሎ፡ካዕበ፡ኔሮን፡ንጉሥ፡አነ፡እመትራ፡ለባቲ፡እዴከ፡ዘኮነት፡ትጽሕፍ፡መጻሕፍተ፡ወታስሕት፡ሰብአ፡ወዘንተ፡ብሂሎ፡አዘዘ፡ይምትሩ፡እዴሁ፡ዘየማን።ወሶበ፡መተሩ፡እዴሁ፡ይቤሎ፡አ፡ንጉሥ፡አእምር፡ከመ፡ንሕነ፡ኢንፈርህ፡ሞተ፡ዝንቱ፡ዓለም፡ባሕቱ፡አርእየከ፡ኃይሎ፡ለእግዚእየ፡ወአምላኪየ፡ወዘንተ፡ብሂሎ፡ነሥአ፡ለምትርት፡እዴሁ፡ዘየማን፡በጸጋማይ፡እዴሁ፡ወአስተላጸቃ፡ውስተ፡መካና፡ወኮነት፡ድኅንተ፡ከመ፡ቀዳሚ።ወእምዝ፡ፈለጣ፡ወአንከሩ፡እለ፡ነበሩ፡በህየ፡ወአምኑ፡ሊቀ፡ሐራ፡ወብእሲቱ፡ወብዙኃን፡ሰብእ፡በእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት።ወኮነ፡ኍልቆሙ፡

ልንና፡የሐዋርያትን፡ዜና፡የጻፈ፡ይህ፡ሉቃስ፡ነው።

፭፡ ቅዱሳን፡ጴጥሮስና፡ጳውሎስም፡ከተገደሉ፡በኋላ፡በሮሜ፡ሀገር፡የሚያስተምር፡ሆነ፡በቀናች፡ሃይማኖትም፡ይጸኑ፡ዘንድ፡ለምእመናን፡መልእክትን፡ይጽፍ፡ነበር።ስለዚህም፡ጣዖት፡አምላኪዎች፡ከአይሁድ፡ጋር፡በመስማማት፡አንድ፡ግምባር፡ፈጠሩ፡በንጉሥ፡ኔሮን፡ፊት፡ቁመው፡ስለ፡ሐዋርያው፡ሉቃስ፡እንዲህ፡ብለው፡ጮኹ፡ይህ፡ሉቃስ፡ብዙዎች፡ሰዎችን፡በሥራዩ፡ወደ፡ትምህርቱ፡አስገባቸው፡ንጉሥ፡ኔሮንም፡ወደ፡ፍርድ፡አደባባይ፡ሉቃስን፡እንዲአቀርቡት፡አዘዘ።

፮፡ ሐዋርያ፡ሉቃስም፡ከዚህ፡ዓለም፡መውጫው፡እንደ፡ደረሰ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡አውቆ፡ወደ፡ባሕር፡ዳርቻ፡ሔደ፡በዚያም፡ዓሣ፡የሚያጠምድ፡አንድ፡ሽማግሌ፡ሰው፡አገኘ።መጻሕፍቱንና፡ደብዳቤዎቹን፡ሰጠው፡ወደ፡እግዚአብሔር፡መንገድ፡መርተው፡ያደርሱሃልና፡እሊህን፡መጻሕፍት፡ጠብቃቸው፡አለው።

፯፡ በንጉሥ፡ኔሮንም፡ፊት፡ቀርቦ፡በቆመ፡ጊዜ፡ንጉሡ፡በሥራይህ፡ሕዝቡን፡የምታስት፡እስከመቼ፡ነው፡አለው፡ቅዱስ፡ሉቃስም፡እኔ፡ለሕያው፡እግዚአብሔር፡ልጅ፡ለጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሐዋርያው፡ነኝ፡እንጂ፡ሥራየኛ፡አይደለሁም፡ብሎ፡መለሰለት።

፰፡ ንጉሥ፡ኔሮንም፡ሁለተኛ፡እንዲህ፡አለው፡እየጻፈች፡ሰዎችን፡የምታስት፡ይቺን፡እጅህን፡እኔ፡እቆርጣታለሁ፡ይህንንም፡ብሎ፡የቀኝ፡እጁን፡እንዲቆርጡ፡አዘዘ፡በቆረጡትም፡ጊዜ፡ንጉሥ፡ሆይ፡እኛ፡የዚህን፡ዓለም፡ሞት፡እንደማንፈራ፡እወቅ፡ነገር፡ግን፡የጌታዬንና፡የፈጣሪዬን፡ኃይሉን፡ታውቅ፡ዘንድ፡አሳይሃለሁ፡ይህንንም፡ብሎ፡የተቆረጠች፡የቀኝ፡እጁን፡በግራ፡እጁ፡አንሥቶ፡ከተቆረጠችበት፡ቦታዋ፡ላይ፡አገናኝቶ፡እንደ፡ቀድሞዋ፡ደኅነኛ፡አደረጋት።ከዚህም፡በኋላ፡ለያት፡በዚያም፡የነበሩ፡አደነቁ፡የሠራዊት፡አለቃውና፡ሚስቱ፡ብዙዎችም፡ሰዎች፡ክብር፡ይግባውና፡በጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አመኑ፡ቁጥራቸውም፡አራት፡መቶ፡

www.ethiopianorthodox.org

፬፻ወ፸ወ፯ቱ፡ነፍስ፡ወአዘዘ፡ንጉሥ፡ይምትሩ፡
አርእስቲሆሙ፡በሰይፍ፡ምስለ፡ቅዱስ፡ሉቃስ፡
ወመተርዎሙ፡ ወነሥኡ፡ አክሊለ፡ ስምዕ፡
በመንግሥተ፡ሰማያት።
፰፡ ወእምዝ፡ ረሰዩ፡ ሥጋሁ፡ ለቅዱስ፡ ሉቃስ፡
ውስተ፡ ሠቀ፡ ፀጉር፡ ወወገርዎ፡ ውስተ፡
ባሕር፡ ወበሥምረቱ፡ ለእግዚአብሔር፡በጽሐ፡
ኀበ፡ ፩ ደሴት፡ ወረከብዎ፡ መሐይምናን፡
ወነሥእዎ፡ ወገነዝዎ፡ ወአንበርዎ፡ ውስተ፡
መካን፡ሠናይ።
፱፡ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ኪያነኒ፡ ይም
ሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡ሐዋርያ፡ወበረከቱ፡
ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ሰባ፡ሰባት፡ነፍስ፡ሆነ፡ንጉሡም፡ከቅዱስ፡
ሉቃስ፡ ጋር፡ ራሶቻቸውን፡ እንዲቆርጡ፡
አዘዘና፡ቆረጡአቸው፡የምስክርነት፡አክሊ
ልንም፡በመንግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበሉ።
፰፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ የቅዱስ፡ ሉቃስን፡ ሥጋ፡
በማቅ፡ አይበት፡ ውስጥ፡ አድርገው፡ ወደ፡
ባሕር፡ ጣሉት፡ በእግዚአብሔርም፡ፈቃድ፡
ወደ፡አንድ፡ደሴት፡ደረሰ።ምእመናንም፡አግ
ኝተው ወስደው፡ገነዙት፡በአማረ፡ቦታም፡
አኖሩት።
፱፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡
በዚህ፡ሐዋርያ፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከቱም፡
ከእኛ፡ጋራ፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለሉቃስ፡እንተ፡ረትዐ፡ልሳኑ።ወንጌለ፡መለኮት፡ይጽሐፍ፡እምእለ፡ብዙኃን፡ወጠኑ።
ከመ፡ያርኢ፡ኀይለ፡ቅድመ፡ኔሮን፡ወተዐይኑ።አስተላጸቃ፡ወሌለያ፡ለምትርት፡የማኑ።እስመ፡ላዕሌሁ፡
ተሠውጠ፡ለክርስቶስ፡ሥልጣኑ።
ሰላም፡ለክሙ፡ማኅበሩ፡ሉቃስ፡አኃው።አርባዕቱ፡ምእት፡ሰብዓ፡ወሰብዓቱ፡ዕደው።ምቱራን፡
በሰይፍ፡አምሳለ፡ዕፀው።ወለሲላስ፡ሰላም፡አረጋዊ፡ልብው።መጻሕፍቲሁ፡ዘዐቀበ፡እምኵሉ፡ምንስው።

***

፩፡ በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡
አሐዱ፡ አምላክ፡ አመ፡ ፳ወ፫፡ ለጥቅምት፡
በዛቲ፡ ዕለት፡ አዕረፈ፡ አባ፡ ዮሴፍ፡ ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንድርያ፡እምኍልቆሙ፡
ለአበው፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፡፶ወ፪ቱ።
፪፡ ወዝንቱ፡ አብ፡ እምውሉደ፡ ልሒቃነ፡ ሀገረ፡
መኑፍ፡ ወአበዊሁኒ፡ ቦሙ፡ ብዙኀ፡ ንዋይ፡
ወእንዘ፡ ንኡስ፡ ውእቱ፡ አዕረፉ፡ አቡሁ፡
ወእሙ፡ ወኀደግዎ፡ ዕጓለ፡ማውታ፡ ወሐፀኖ፡
፩ብእሲ፡መፍቀሬ፡ እግዚአብሔር።
፫፡ ወሶበ፡ ልሕቀ፡ ወወርዘወ፡ ነሥአ፡ ንዋየ፡
አበዊሁ፡ ኵሎ፡ ወሀበ፡ ለነዳያን፡ ወለምስ
ኪናን፡ወእምዝ፡ዐርገ፡ኀበ፡ገዳመ፡አስቄጥስ፡
ወመንኰሰ፡ኀበ፡፩ አረጋዊ፡ብእሲ፡ጻድቅ፡
ወነበረ፡ እንዘ፡ ይትጋደል፡ በኵሉ፡ ገድል፡
ሠናይ።
፬፡ወሶበ፡ተሠይመ፡አባ፡ማርቆስ፡ዳግማይ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ሰምዐ፡ዜናሁ፡ለዝንቱ፡አባ፡ዮሴፍ፡
ወግዕዘ፡ሠናየ፡ወፈነወ፡ላእካነ፡ወአምጽአ፡
መንገሌሁ፡ ወአንበሮ፡ ምስሌሁ፡ ውስተ፡
ቤቱ።

***

፩፡ አንድ፡ አምላክ፡ በሚሆን፡ በአብ፡ በወልድ፡
በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ ጥቅምት፡ ሃያ፡
ሦስት፡በዚች፡ ቀን፡ ለአባቶች፡ ሊቃነ፡ ጳጳ
ሳት፡ ኀምሳ፡ ሁለተኛ፡ የሆነ፡ የእስክንድርያ፡
ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ዮሴፍ፡አረፈ።
፪፡ ይህም፡ አባት፡ ከመኑፍ፡ አገር፡ ከታላላቆች፡
ተወላጆች፡ ወገን፡ ነው፡ ወላጆቹም፡ ብዙ
ገንዘብ፡ያላቸው፡ነበሩ፡ታናሽም፡ሁኖ፡ሳለ፡
አባትና፡ እናቱ፡ ትተውት፡ ሲሞቱ፡ ድኃ፡
አደግ፡ሆነ፡አንድ፡ እግዚአብሔርንም፡የሚ
ወድ፡ሰው፡አሳደገው።
፫፡ አድጎ፡ በጐለመሰም፡ ጊዜ፡ የወላጆቹን፡ ገን
ዘብ፡ ሁሉንም፡ ወስዶ፡ ለድኆችና፡ ለምስ
ኪኖች፡ መጸወተ፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ ወደ፡
አስቄጥስ፡ ገዳም፡ ወጥቶ፡ ከአንድ፡ ጻድቅ፡
ሽማግሌ፡ ሰው፡ አባት፡ ዘንድ፡ መነኰሰ፡
በበጎ፡ገድል፡ሁሉ፡እየተጋደለ፡ኖረ።
፬፡ ዳግማዊ፡ አባ፡ ማርቆስም፡ ሊቀ፡ ጵጵስና፡
በተሾመ፡ ጊዜ፡ የዚህን፡ አባ፡ ዮሴፍን፡ በጎ፡
ጠባዩንና፡የትሩፋቱን፡ዜና፡ሰምቶ፡መልእክ
ተኞችን፡ልኮ፡ወደርሱ፡አስመጣው፡በቤቱም፡
አኖረው።

፱፡ ወሶበ፡ነበረ፡ዲበ፡መንበረ፡ማርቆስ፡ወንጌላዊ፡
ኮነ፡ዘይሔሊ፡ለአብያተ፡ክርስቲያን፡እስመ፡
ውእቱ፡ይነሥእ፡እምጸባሕተ፡ዚአሁ፡ወይ
ሣየጥ፡ጕልታተ፡ምድር፡ወይጕልቆሙ፡
ለአብያተ፡ክርስቲያን።
፲፡ ወኮነ፡ወትረ፡ይሜህሮሙ፡ለሕዝብ፡ወኢይት
ዔወር፡በምንትኒ፡ለለ፩፩ዱ፡ወባሕቱ፡ኢኀደጎ፡
ሰይጣን፡ዘእንበለ፡ኀዘን፡እስመ፡ቀንአ፡
ላዕሌሁ።
፲፩፡ ውእቱኬ፡እስመ፡ኤጲስቆጶሳት፡፪ቱ፡ዘሀገረ፡
ምስር፡አሕሠሙ፡ላዕለ፡ሕዝብ፡ወአመንደ
ብዎሙ፡በግብር፡ዘኢይደሉ፡ውእቱኒ፡አዘ
ዞሙ፡ለእሉ፡ኤጲስቆጶሳት፡ወሰአሎሙ፡ከመ፡
ይርዓዩ፡መርዔቶሙ፡በምሕረት፡ወበሰላም፡
እሙንቱሰ፡ኢሰምዕዎ፡ወኢተመይጡ፡እምእ
ከዮሙ።
፲፪፡ ወሶበ፡አፈድፈዱ፡ምንዳቤ፡ላዕለ፡ሕዝብ፡
በጽሑ፡ኵሎሙ፡ሕዝብ፡ኀበ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
አባ፡ዮሴፍ፡ወጸርሑ፡በቅድሜሁ።ወይቤልዎ፡
ለእመ፡ኢያንግእኮሙ፡ለእሉ፡ኤጲስቆ
ጶሳት፡ንሕነ፡ንበውዕ፡ውስተ፡ካልዕ፡ሃይ
ማኖት፡ወተጋደለ፡አባ፡ዮሴፍ፡ተጋድሎ፡
ዐቢየ፡ከመ፡ይግበር፡ሰላመ፡ማዕከሎሙ፡
ዳዕሙ፡ኢተክህሎ።
፲፫፡ ወእምዝ፡አስተጋብአሙ፡ለኵሎሙ፡ኤጲስቆ
ጶሳት፡እለ፡ውስተ፡ብሔረ፡ግብጽ፡ወነ
ገሮሙ፡በእንተ፡እሉ፡፪ቱ፡ኤጲስቆጶሳት፡
ለእሉሂ፡አብጽሐሙ፡ኀበ፡ጉባኤ፡ወፈቀደ፡
ይእዜኒ፡ይግበር፡ሰላመ፡ምስለ፡መርዔቶሙ፡
ወእሙንቱሰ፡ኢሰምዑ፡ቃሎ፡ወቃሎሙ፡
ለአበው፡ኤጲስቆጶሳት፡ወበእንተዝ፡መተ
ሮሙ፡እምኅሊመቶሙ፡ውእቱ፡ጉባኤ።

፲፬፡ ወእሙንቱ፡ሖሩ፡ኀበ፡ንጉሠ፡ግብጽ፡ወአስተ
ዋደይዎ፡ለሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ዮሴፍ፡በነገረ፡
ሐሰት፡ወፈነዎ፡ንጉሥ፡ለእኍሁ፡ምስለ፡ሐራ፡
ከመ፡ያምጽኦ፡ለአባ፡ዮሴፍ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡
ወሶበ፡በጽሐ፡እኍሁ፡ለንጉሥ፡ኀበ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ርህጸ፡ወፈቂዶ፡ይቅትሎ፡መልሐ፡
ሰይፎ፡ወዘበጦ፡ለሊቀ፡ጳጳሳት፡ባሕቱ፡ጸነ፡
እዴሁ፡ኀበ፡ካልዕ፡ወአዕረፈ፡ዝብጠት፡
ላዕለ፡ዓምድ፡ወተሰብረ፡ሰይፉ፡ወተቈጥዐ፡
ፋድፋደ፡ወመልሐ፡ካልዓ፡ሰይፈ፡ወዘበጦ፡

፱፡ በወንጌላዊ፡ማርቆስ፡ወንበርም፡በተቀመጠ፡
ጊዜ፡ለአብያተ፡ክርስቲያን፡እጅግ፡የሚያስብ፡
ሆነ፡ለርሱ፡የሆነውን፡የግብሩን፡ገቢ፡ወስዶ፡
ምድሮችን፡በመግዛት፡ለአብያተ፡ክርስቲያን፡
መተዳደሪያ፡ሊሆኑ፡ጕልቶች፡ያደርጋቸው፡
ነበርና።
፲፡ አዘውትሮም፡ሕዝቡን፡የሚያስተምራቸው፡
ሆነ፡በምንም፡በምን፡ለየአንዳንዱ፡ቸለል፡
አይልም፡ነገር፡ግን፡ሰይጣን፡ስለቀናበት፡ያለ፡
ኀዘን፡አልተወውም።
፲፩፡ ይህም፡እንዲህ፡ነው፡በምስር፡አገር፡የተሾሙ፡
ሁለት፡ኤጲስቆጶሳት፡በሕዝቡ፡ላይ፡ክፉ፡
ነገር፡በማድረግ፡በማይገባ፡ሥራ፡አስጨነ
ቋቸው፡እርሱም፡በርኅራኄና፡በፍቅር፡መንጎ
ቻቸውን፡እንዲጠብቁ፡አዘዛቸው፡ለመና
ቸውም፡እነርሱ፡ግን፡ሰምተው፡ከክፋ
ታቸው፡አልተመለሱም።
፲፪፡ በሕዝቡም፡ላይ፡ችግርን፡በአበዙ፡ጊዜ፡ሕዝቡ፡
ሁሉም፡በጠቅላላ፡ወደ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡
ዮሴፍ፡መጡ፡በፊቱም፡እንዲህ፡ብለው፡
ጮኹ፡እሊህን፡ኤጲስቆጶሳት፡ከላያችን፡ካላ
ነሣሃቸው፡እኛ፡ወደሌላ፡ሃይማኖት፡እንገ
ባለን፡አባ፡ዮሴፍም፡በመካከላቸው፡ሰላምን፡
ለማድረግ፡ብዙ፡ትግልን፡ታገለ፡ግን፡አልተ
ቻለውም።
፲፫፡ ከዚህም፡በኋላ፡በግብጽ፡አገር፡ያሉትን፡ኤጲስ
ቆጶሳት፡ለጉባኤ፡ሰበሰባቸውና፡ስለ፡እሊህ፡
ሁለት፡ኤጲስቆጶሳት፡ነገራቸው፡አሁንም፡
ከመንጋዎቻቸው፡ጋር፡ሊአስታርቅ፡ሽቶ፡
እሊህን፡ኤጲስቆጶሳት፡ወደ፡ጉባኤው፡አስቀ
ረባቸው፡እነርሱ፡ግን፡የጉባኤውንም፡የእር
ሱንም፡ቃል፡አልተቀበሉም፡ስለዚህም፡ያ፡
ጉባኤ፡ከሹመታቸው፡ሻራቸው።
፲፬፡ እነርሱም፡ወደ፡ግብጽ፡ንጉሥ፡ሒደው፡
በሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ዮሴፍ፡ላይ፡በሐሰት፡
ነገር፡ሠሩበት፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ዮሴፍንም፡
ያመጡት፡ዘንድ፡ንጉሡ፡ወንድሙን፡
ከጭፍራ፡ጋር፡ላከው።የንጉሡም፡ወንድም፡
ወደ፡ሊቀ፡ጳጳሳቱ፡በደረሰ፡ጊዜ፡ተበሳጨ፡
ሊገለውም፡ወዶ፡ሰይፉን፡መዞ፡ሊቀ፡
ጳጳሳቱን፡ሊመታው፡ሰነዘረበት፡ግን፡እጁ፡
ወደሌላ፡አዘንብሎ፡ምሰሶ፡መትቶ፡ሰይፉ፡
ተሰበረ፡እጅግም፡ተቆጥቶ፡ሌላ፡ሰይፍን፡

www.ethiopianorthodox.org

በኵሉ ፡ ኃይሉ ፡ አሚሃኒ ፡ ተመይጦ ፡ ሰይፍ ፡ እምክሣዱ ፡ መንገለ ፡ ገቦሁ ፡ ወበተከ ፡ አልባሲሁ ፡ ወቅናቶ ፡ ባሕቲቶ ፡ ወሐለየ ፡ እኁሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ከመ ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ እምእከይ፡ወበእንተዝ፡ተዐቅቦ፡ኃይል፡አምላካዊት፡ወለበወ።

፲፫፡ ወአብጽሖ፡ኀበ፡ንጉሥ፡በክብር፡ወአይድዖ፡ ለንጉሥ ፡ እኁሁ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ንጉሥኒ፡ፈርሀ፡ወአክበሮ፡ወእምዝ፡ተሰአሎ፡ · በእንተ፡እሉ፡፪ቱ፡ኤጲስቆጶሳት፡እለ፡አስተዋደይዎ፡ውእቱኒ፡አጠየቆ፡ለንጉሥ፡ጽድቀ፡ ከመ፡እሙንቱ፡ተመትሩ፡በጉባኤ፡በእንተ፡ እከየ፡ምግባሮሙ፡ወሶቤሃ፡አእመረ፡ንጉሥ፡ ከመ ፡ ሐሳውያን ፡ እሙንቱ ፡ ወአዘዘ ፡ ይቅትልዎሙ።

፲፬፡ ወአስተብቍዖ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ዮሴፍ ፡ ለንጉሥ፡ወይቤሎ፡አ፡ንጉሥ፡መሐሮሙ፡ ወኢትቅትሎሙ ፡ ለእሉ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር፡እስመ፡ለነ፡አዘዘነ፡እግዚእነ፡ከመ፡ ንግበር ፡ ሠናየ ፡ ህየንተ ፡ እኪት ፡ ወአንከረ ፡ ንጉሥ ፡ እምየውሀቱ ፡ ወተወክፈ ፡ ስእለቶ ፡ ወመሐሮሙ፡ሎቱ።

፲፭፡ ወእምዝ ፡ ጸሐፈ ፡ሎቱ ፡ ጦማረ ፡ ወወሀቦ ፡ መባሕተ፡ላዕለ፡ኵሎሙ፡ሥዩማን፡ወላዕለ፡ ኵሎሙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዘፈቀደ ፡ እመሂ ፡ ይፈቅድ ፡ ይሢም ፡ ወእመሂ፡ይሥዓር፡ወአልቦ፡ዘይትቃወሞ።

፲፮፡ ወበመዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ፈነወ ፡ መልእክተ፡ንጉሠ፡ኢትዮጵያ፡ኀበ፡ዝንቱ፡ አብ ፡ አባ ፡ ዮሴፍ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዘ ፡ ይብል፡እኤምኅ፡ለመንበረ፡ማርቆስ፡ወንጌላዊ ፡ ወለዘደለዎ ፡ ይንበር ፡ዲቤሁ ፡ ቅድስናከ ፡ ወእስእል ፡ ከመ ፡ ትሣሃል ፡ ላዕሌየ፡ ወላዕለ ፡ መንግሥትየ ፡ ወላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብየ፡ሰብአ፡ኢትዮጵያ፡ወትፈንዎ፡ለነ፡ ለአቡነ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ጳጳስ ፡ እስመ ፡ እምሰብአ፡ሀገርነ፡እለ፡ስሕቱ፡እምፍኖተ፡ ጽድቅ ፡ ሰደድዎ ፡ ለአባ ፡ ዮሐንስ፡ ጳጳስነ ፡ እንዘ ፡ ኢ.ሀሎኩ፡ ወኢየአምር ፡ አነ ፡ ወበእንተዝ ፡ ኮነ ፡ ውስተ ፡ ሀገርነ፡ ብድብድ ፡ ወኃጢአ፡ዝናም፡ወኀልቁ፡ብዙኃን፡እምሰብእ፡ወእንስሳ።

መገዙ፡በመላ፡ኃይሉ፡መታው፡ያን፡ጊዜም፡ ሰይፉ ፡ ከአንገቱ ፡ ወደ ፡ ወገቡ ፡ ተመልሶ ፡ ልብሱንና፡ቅናቱን፡ብቻ፡ቆረጠ፡የንጉሡም፡ ወንድም ፡ ከክፋት ፡ ንጹሕ ፡ እንደሆነ ፡ ስለዚህም፡አምላካዊት፡ኃይል፡እንደምትጠብቀው፡አሰበ፡አስተዋለም።

፲፫፡ወደ፡ንጉሡም፡በክብር፡አደረሰው፡ወንድሙ፡ ለሆነ፡ንጉሥም፡በእርሱ፡በሊቀ፡ጳጳሳቱ፡ላይ፡ የሆነውን፡ሁሉ፡ነገረው፡ንጉሡም፡ፈራው፡ አከበረውም፡ከዚህም፡በኋላ፡ስለከሰሱት፡ስለ፡ ሁለቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ጠየቀው፡ እርሱም ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራቸው ፡ በጉባኤ ፡ እንደተሻሩ ፡ እውነቱን፡ለንጉሡ፡አስረዳው፡ያን፡ጊዜም፡ ሐሰተኞች፡እንደሆኑ፡ንጉሥ፡አወቀ፡ይገድሏቸውም፡ዘንድ፡አዘዘ።

፲፬፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ዮሴፍም ፡ ንጉሡን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ማለደው ፡ ጌታችን ፡ በክፉ ፡ ፈንታ፡በጎ፡እንድናደርግ፡እኛን፡አዞናልና፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ እሊህን ፡ ማራቸው፡እንጂ፡አትግደላቸው፡ንጉሡም፡ስለ፡ የዋህነቱ፡አደነቀ፡ልመናውንም፡ተቀብሎ፡ ማረለት።

፲፭፡ከዚህም፡ በኋላ፡ በሹማምንቱና፡ በኤጲስቆጶሳቱ፡ሁሉ ላይ፡የፈለገውን፡ያደረግ፡ ዘንድ ፡ ቢፈልግ ፡ እንዲሾም ፡ ወይም ፡ እንዲሽር ፡ የሚቃወመው ፡ እንዳይኖር ፡ ደብዳቤ ፡ በመጻፍ፡ሥልጣንን፡ሰጠው፡፡

፲፮፡በዚህም፡አባት፡ዘመን፡የኢትዮጵያ፡ንጉሥ፡ ወደዚህ ፡ አባት ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ዮሴፍ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መልእክትን ፡ ላከ ፡ ለወንጌላዊ ፡ ማርቆስ ፡ መንበርና ፡ በላዩ ፡ ለመቀመጥ ፡ ለተገባው ፡ ቅድስናህ ፡ እጅ ፡ እነሣለሁ ፡ በእኔና ፡ በመንግሥቴ ፡ ላይ ፡ በመላው፡ ወገኖቼ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ላይ፡ይቅርታ፡እንድታደርግና፡አባታችንን፡ አባ ፡ ዮሐንስን ፡ እንድትልክልን ፡ እለምንሃለሁ ፡ ከሀገራችን ፡ ሰዎች ፡ ከእውነት ፡ መንገድ፡የወጡና፡የሳቱ፡ጳጳሳችንን፡አባ፡ ዮሐንስን፡እኔ፡ሳልኖርና፡ሳላውቅ፡አባረውታልና ፡ ስለዚህም ፡ በሀገራችን ፡ ቸነፈርና ፡ ድርቅ ፡ ሁኖ ፡ ከሰዎቹም ፡ ከእንስሶችም ፡ ብዙዎች፡አለቁ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፡ ወይእዜኒ፡ተማኅፅል፡ኦ፡አቡነ፡ላዕለ፡እበድነ፡ ወፈንዎ፡ለአቡነ፡አባ፡ዮሐንስ፡ጳጳስ፡ከመ፡ ይጸሊ ፡ ለነ ፡ ወያስተብቍዕ ፡ ኀበ ፡ እግዚአ ብሔር፡መሐሪ፡ወመስተማህል፡ከመ፡ንድ ኃን፡እምዝንቱ፡ምንዳቤ፡በጸሎቱ፡ቅድስት።

፳፡ ኦ፡አቡየ፡አነ፡አጤይቀከ፡ምክንያተ፡ስደቱ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ወልድከ ፡ ተባረኩ ፡ እምነ ፡ አቡየ፡አባ፡ዮሐንስ፡ጳጳስ፡ወውእቱ፡አስተ ፋነወኒ፡ በሰላም ፡ ምስለ ፡ ሠራዊትየ ፡ ወሖ ርኩ፡ውስተ፡ጸብእ፡ወሶበ፡ገባእኩ፡እምጸ ብእ፡ኃጣእክዎ፡ለአቡየ፡አባ፡ዮሐንስ፡ጳጳስ፡ ወሶበ ፡ ተሰአልኩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ነገሩኒ ፡ ከመ፡ ብእሲትየ ፡ ንግሥት ፡ ሰደደቶ ፡ ሶበ ፡ አምከርዋ፡ሰብእ፡እኩያን፡በከመ፡ሰደደቶ፡ አውዶክስያ ፡ ንግሥት ፡ ለዮሕንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ፡በቀዳሚ፡መዋዕል፡ወሚሙ፡ካልዓ፡ ጳጳሰ ፡ በፈቃዶሙ ፡ በተዓድዎ ፡ ትእዛዘ ፡ ቀኖና።

፳፩፡ ውእቱሰ ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ሶበ ፡ ሰደድዎ ፡ እምብሔረ፡ኢትዮጵያ፡ሖረ፡ኀበ፡ገዳመ፡ አስቄጥስ፡ኀበ፡ደብረ፡አባ፡ሙሴ፡ጸሊም፡ ዘመንኰሰ፡ባቲ፡ወበህየ፡ነበረ።

፳፪፡ ወሶበ ፡ በጽሐት ፡ መልእክቱ ፡ ለንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ፡ኀበ፡አባ፡ዮሴፍ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ አንበባ፡ወተፈሥሐ፡ፈድፋደ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ ሃይማኖቱ፡ለንጉሠ፡ኢትዮጵያ፡ወፍጡነ፡ ፈነወ ፡ ላእካነ ፡ ኀበ ፡ ገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ ወአብጽሖ፡ለአባ፡ዮሐንስ፡ኀቤሁ፡ወናዘዞ፡ ወአጽንዖ ፡ ወፈነዎ ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ምስለ፡ኄራን፡ሰብእ።

፳፫፡ ወሶበ፡በጽሐ፡ብሔረ፡ኢትዮጵያ፡አባ ፡ዮሐንስ፡ ተአተተ ፡ ብድብድ ፡ ወወረደ ፡ ዝናም ፡ እምሰማይ፡ወተፈሥሑ፡ንጉሥ፡ወኵሎሙ፡ ሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአ ብሔር።

፳፬፡ ወኮነ፡ዝንቱ፡አብ፡ዮሴፍ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘይ ጌሥጾሙ፡ለዓላውያን፡ወይሜህሮሙ፡ለሕ ዝቡ፡ከመ፡ይጽንዑ፡ውስተ፡ሃይማኖት፡ ርትዕት ፡ ዘተመጠውዋ ፡ እምአበዊሆሙ ፡ ወይከሥት ፡ ሎሙ ፡ ዘውስተ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት፡ዘኮነ፡ኀቡአ፡እምኔሆሙ፡ወይፌ

፲፱፡ አሁንም፡አባቴ፡ሆይ፡ስንፍናችንን፡ይቅር፡ በል፡መሐሪና፡ይቅር፡ባይ፡ወደ፡ሆነ፡እግዚ አብሔር ፡ ፈጽሞ ፡ ይማልድልን ፡ ዘንድ ፡ በከበረች፡ጸሎቱም፡ከዚህ፡መከራ፡እንድን፡ ዘንድ፡አባታችንን፡አባ፡ዮሐንስን፡ላክልን።

፳፡ አባቴ፡ሆይ፡የተባረረበትን፡ምክንያት፡እኔ፡ አስረዳሃለሁ፡እኔ፡ልጅህ፡ከአባቴ፡ከጳጳስ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ ቡራኬ ፡ ተቀብዬ ፡ እርሱ ፡ ከሠራዊቴ፡ጋር፡በፍቅር፡አሰናብቶኝ፡ወደ፡ ጦር፡ሜዳ፡ሔድሁ፡ከጦር፡ሜዳም፡በተመ ለስኩ፡ጊዜ፡አባቴን፡አባ፡ዮሐንስ፡ጳጳሱን፡ አጣሁት ፡ ስለርሱም ፣ በጠየቅሁ ፡ ጊዜ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅን ፡ ንግሥት፡አውዶክስያ፡እንደሳደደችው፡በክ ፉዎች፡ሰዎች፡ምክር፡ንግሥቲቱ፡ሚስቴ፡ ማሰደዷን ፡ የቀኖናውንም ፡ ትእዛዝ፡ በመተ ላለፍ፡በፈቃዳቸው፡ሌላ፡ጳጳስ፡እንደሾሙ፡ ነገሩኝ።

፳፩፡ እርሱ፡አባ፡ዮሐንስም፡ከኢትዮጵያ፡በአሳ ደዱት፡ጊዜ፡ወደ፡አስቄጥስ፡በመሔድ፡ አስቀድሞ ፡ በመነኰሰባት ፡ በአባ ፡ ሙሴ ፡ ጸሊም፡ገዳም፡በዚያ፡ተቀመጠ።

፳፪፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መልእክትም ፡ ወደ ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡አባ፡ዮሴፍ፡በደረሰች፡ጊዜ፡ አነበባት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ የሃይ ማኖት ፡ ጽናት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ፈጥ ኖም፡ ወደ ፡ አስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ መልእክተ ኞችን ፡ ልኮ ፡ አባ ፡ ዮሐንስን ፡ ወደርሱ ፡ አስመጥቶ፡አረጋጋው፡አጽናናው፡ከዚያም፡ በኋላ ፡ ከደጋጎች ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ፡አገር፡ላከው።

፳፫፡ አባ ፡ ዮሐንስም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አገር ፡ በደረሰ፡ጊዜ፡ቸነፈር፡ተወገደ፡ዝናብም፡ ዘነበ ፡ ንጉሡና ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑት።

፳፬፡ ይህም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ዮሴፍ ፡ መናፍ ቃንን ፡ የሚገሥጻቸው ፡ ሆነ ፡ ሕዝቡንም ፡ ከአባቶቻቸው፡በተቀበሏት፡በቀናች፡ሃይማ ኖት፡እንዲጸኑ፡አስተማራቸው፡ከቅዱሳት፡ መጻሕፍትም ፡ ለእነርሱም ፡ ሥውር ፡ የሆነ ውን ፡ ተርጉሞ ፡ ያስረዳቸዋል ፡ ያስገነዝባቸ

www.ethiopianorthodox.org

ዘአፍአ ፡ ዘኢኮነ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ወተንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እስክንድርያ ፡ ወቦአ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ቦቱ ፡ ኵሎሙ ፡ መምህራን ፡ ወተምህረ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ ብዙኃተ ፡ ትምህርታተ ። ወይእተ ፡ አሚረ ፡ ተሀውከ ፡ ወገብአ ፡ ከመ ፡ ይትመሀር ፡ ትምህርተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአንበበ ፡ ብዙኃተ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይፌክር ፡ ሎቱ ፡ ወያሌብዎ ፡ አባ ፡ እለእስክንድሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ።

፬ ፡ ወእምዝ ፡ አምነ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወተጠምቀ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወእምዝ ፡ መንኰሰ ፡ ወተጸምደ ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ምንኵስና ፡ ወተጋደለ ፡ ገድለ ፡ ጽኑዐ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስ ፡ ወነበረ ፡ ኀቤሁ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ እንዘ ፡ ይትሜሀር ፡ ኵሎ ፡ ምግባረ ፡ ጽድቅ ፡ መንፈሳዌ ።

፭ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ከመ ፡ አበዊሁ ፡ ሞቱ ፡ ሖረ ፡ ወነሥአ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮሙ ፡ ዘኀደጉ ፡ ሎቱ ፡ ወወሀበ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ፡ ወእምዝ ፡ ቦአ ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ ደብር ፡ እምአድባራተ ፡ ሶርያ ፡ ወተጋደለ ፡ በህየ ፡ ፍጹመ ፡ ገድለ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ወበሰጊድ ፡ ወበትጋህ ፡ እስከ ፡ ኮነ ፡ ይሴሰይ ፡ በበ፯ቱ ፡ ዕለት ፡ ወሲሳዩኒ ፡ ማዕረ ፡ ገዳም ።

፮ ፡ ወወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ትንቢት ፡ ወበርሀ ፡ ልቡ ፡ ወገብረ ፡ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ ወውእቱ ፡ ዘአመንኰሶ ፡ ለኤጲፋንዮስ ፡ ወተነበየ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይከውን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ላዕለ ፡ ደሴተ ፡ ቆጵሮስ ።

፯ ፡ ወኮነ ፡ ኵሉ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ፹ ፡ ዓመት ፡ እምቅድመ ፡ ክርስትናሁ ፡ ወምንኵስናሁ ፡ ነበረ ፡ ፲ወ፯ተ ፡ ዓመተ ፡ ወበምንኵስናሁ ፡ ፷ወ፫ተ ፡ ዓመተ ፡ ወእምድኅረ ፡ አሥመሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ አዕረፈ ፡ በሰላም ፡ ወወደሶ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ወካዕበ ፡ ወደሶ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ በመጻሕፍቲሁ ።

፰ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ አብ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

የሆነ ፡ ጥበብን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መማርን ፡ ወዶ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ሀገር ፡ ሔደ ፡ መምህራንም ፡ ሁሉ ፡ ከሚኖሩበት ፡ ቦታ ፡ ገብቶ ፡ ከእሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ትምህርትን ፡ ተማረ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ትምህርት ፡ ለመማር ፡ ተነሣሥቶ ፡ ቸኰለ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ መጻሕፍት ፡ ብዙዎቹን ፡ አነበበ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ እለእስክንድሮስም ፡ ይተረጕም ለትና ፡ ያስረዳው ፡ ነበር ።

፬ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ በጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ አምኖ ፡ የክርስትናን ፡ ጥምቀት ፡ ተጠመቀ ፡ ከዚያም ፡ መንኵሶ ፡ በምንኵስና ፡ ሕግ ፡ ጸንቶ ፡ ገድልን ፡ ተጋደለ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ እንጦንዮስም ፡ ሔዶ ፡ መንፈሳዊ ፡ የሆነ ፡ የትሩፋትን ፡ ሥራ ፡ እየተማረ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ኖረ ።

፭ ፡ ወላጆቹም ፡ እንደሞቱ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሒዶ ፡ የተዉለትን ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሁሉንም ፡ ወስዶ ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ መጸወተ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከሶርያ ፡ ገዳማት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ገዳም ፡ ገባ ፡ በዚያም ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በስግደት ፡ በመትጋት ፡ ፍጹም ፡ ገድልን ፡ ተጋድሎ ፡ በየሰባት ፡ ቀን ፡ እስቲመገብ ፡ ድረስ ፡ ምግቡም ፡ የዱር ፡ ማር ፡ ነበር ።

፮ ፡ እግዚአብሔርም ሀብተ ፡ ትንቢትን ፡ ሰጥቶት ፡ ልቡናው ፡ ብሩህ ፡ ሆነ ፡ ድንቆች ፡ ተአምራትንም ፡ የሚያደርግ ፡ ሆነ ፡ ኤጲፋንዮስንም ፡ ያመነኰሰውና ፡ ለደሴተ ፡ ቆጵሮስም ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ እንደሚሆን ፡ ትንቢት ፡ የተናገረለት ፡ እርሱ ፡ ነው ።

፯ ፡ የዚህም ፡ አባት ፡ መላ ፡ ዕድሜው ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ ከክርስትናውና ፡ ከምንኵስናው ፡ በፊት ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በምንኵስናም ፡ ስልሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነው ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ እግዚአብሔርንም ካገለገለ ፡ በኋላ ፡ በሰላም ፡ አረፈ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ አመስግኖታል ፡ ሁለተኛም ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ በመጻሕፍቱ ፡ አመስግኖታል ።

፰ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በዚህ ፡ አባት ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ለአብላርዮስ ፡ ለከርሡ ፡ ዘሠርዐ ። ማየ ፡ ባሕር ፡ ስቴ ፡ ወማዕረ ፡ ገዳም ፡ መብልዐ ። በዕለተ ፡ አዕረፈ ፡ ዮም ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እኅድዓ ። ኢትፍርሂ ፡ ነፍስየ ፡ እምነ ፡ ሥጋ ፡ ወጺአ ። እስመ ፡ ተቀነይኩ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዓመታተ ፡ ሰብዓ ።

፱፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተገዘከርሙ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳውሎስ ፡ ቢጹ ፡ ለለንጊኖስ ፡ ሰማዕት ፡ ወዘይና ፡ ወአውስያ ፡ ወጸበለ ፡ ማርያም ፡ ተሐራሚት ፡ ወቈስጠንጢኖስ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡፡

፱፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ለሰማዕት ፡ ለንጊኖስ ፡ ባልንጀራው ፡ የሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳውሎስ ፡ የዘይና ፡ የአውስያ ፡ የጸበለ ፡ ማርያም ፡ ተሐራሚት ፡ የቈስጠንጢኖስም ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለጳውሎስ ፡ ወለለንጊኖስ ፡ ቢጹ ። እምፍኖተ ፡ ስምዕ ፡ ዘኢገገጹ ። ወለዘይና ፡ ሰማዕት ፡ ፈጻሚተ ፡ ገድል ፡ ዘበበገጹ ። እምእለ ፡ መከሩ ፡ መከየድየ ፡ ያዕቅጹ ። ለዓቂቦትየ ፡ እምሰማይ ፡ ይቅንጹ ።

ሰላም ፡ ለኪ ፡ ጸበለ ፡ ማርያም ፡ ተሐራሚት ። እምወይነ ፡ መዓዛ ፡ ወእክለ ፡ ወራዙት ። ተውላጠ ፡ ሕማምኪ ፡ ዘመጠነ ፡ ኃምሳ ፡ ዓመት ። በገነተ ፡ ጽጌ ፡ ኀበ ፡ ተነጽፈ ፡ ዕረፍት ። ከመ ፡ ንባእ ፡ አኃውኪ ፡ አስተብቍዒ ፡ እኅት ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፫ ፡ ለጥቅምት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ዐቢይ ፡ ወክቡር ፡ ወመስተጋድል ፡ አባ ፡ ቡላ ፡ ዘተሰምየ ፡ አቢብ ።

፪፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ አብርሃም ፡ ወስማ ፡ ለእሙ ፡ ሐሪክ ፡ ወእሙንቱ ፡ ውስተ ፡ በሐውርተ ፡ ሮሜ ፡ እምአድያመ ፡ ሉፊ ፡ ወበመዋዕሊሆሙ ፡ ኮነ ፡ ስደት ፡ ሶበ ፡ አንሥአ ፡ ምንዳቤ ፡ መክስምያኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ዐላዊ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወእሙንቱ ፡ ነበሩ ፡ ውስተ ፡ ስደት ፡ ብዙኀ ፡ አዝማነ ።

፫፡ ወሶበ ፡ ኃጥኡ ፡ ወልደ ፡ ሰአሉ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ፡ ከመ ፡ የሀቦሙ ፡ ወልደ ፡ ቡሩከ ፡ ወአስተርአዮሙ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕልም ፡ ወመጠዎሙ ፡ አስካለ ፡ ምሉዐ ፡ ፍሬ ።

፬፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ተፀንሰ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ በቈለ ፡ በጥቃ ፡ ቤቶሙ ፡ ዐቢይ ፡ ያም ፡ ወጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ቈጽሉ ፡ በልሳነ ፡ ሮማይስጥ ፡ ዘይብል ፡ ቡላ ፡ ገብሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወቅዱሱ ፡ ለአምላክ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘየኃድር ፡ ውስተ ፡ ጽዮን ።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥቅምት ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ታላቅና ፡ ክቡር ፡ የሆነ ፡ አቢብ ፡ የተባለ ፡ መስተጋድል ፡ አባ ፡ ቡላ ፡ አረፈ ።

፪፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ አብርሃም ፡ የእናቱም ፡ ስም ፡ ሐሪክ ፡ ነው ፡ እነርሱም ፡ ከሮሜ ፡ አገር ፡ ሉፊ ፡ ከሚባል ፡ አውራጃ ፡ ናቸው ፡ በዘመናቸውም ፡ ከሀዲው ፡ ንጉሥ ፡ መክስምያኖስ ፡ በክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ አመጣ ፡ ስደት ፡ ሁኖ ፡ ነበርና ፡ እነርሱም ፡ በስደት ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ኖሩ ።

፫፡ ልጅንም ፡ በአጡ ፡ ጊዜ ፡ የተባረከ ፡ ልጅን ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ ተወስነው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመኑ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በሕልም ፡ ተገለጠላቸውና ፡ ፍሬ ፡ የመላበትን ፡ ዘለላ ፡ ሰጣቸው ።

፬፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ በተፀነሰ ፡ ጊዜ ፡ በቤታቸው ፡ አጠገብ ፡ ታላቅ ፡ ዛፍ ፡ በቀለ ፡ በቅጠሉም ፡ ላይ ፡ በሮማይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ቡላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ በጽዮንም ፡ አድሮ ፡ የሚኖር ፡ የያዕቆብ ፡ ፈጣሪ ፡ ያከበረው ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ነበረበት ።

www.ethiopianorthodox.org

፱፡ ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ካልዕ ፡ መኰንን ፡ ወጸረፈ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወላዕለ ፡ አማልክቲሁ ፡ ርኩሳን ፡ ወተምዐ ፡ መኰንን ፡ ወመተረ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ፡ አመ ፡ ፲ወ፫ ለወርኀ ፡ ሚያዝያ ፡ ወወረደ፡ካዕበ፡ቅዱስ፡ሚካኤል፡እምሰማይ፡ ወአንሥአ ፡ እሙታን ፡ ወወሰዶ ፡ ውስተ ፡ ፩ ደብር ፡ ወአልበሶ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና ፡ ወአስኬማ፡በአርአያ፡ትእምርተ፡መስቀል፡ ወይቤሎ ፡ አዘዘከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትኩን ፡ ሱታፌሆሙ፡ለቅዱሳን፡ጻድቃን።

፲፡ ወሶበ፡ሃ፡ ሀገረ፡ቅዱስ፡አባ፡ቡላ፡ወልዕልተ፡ ደብር ፡ ይቡስ ፡ ወነበረ ፡ ውስቴታ ፡ እንዘ ፡ ይትጋደል፡ዘእንበለ፡አጽርዖ።

፲፩፡ ወሶበ፡ይዜከር፡ስቅለቶ፡ወሕማማቲሁ፡ ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የዐርግ፡ላዕለ፡ ዕፅ፡ነዊኅ፡ወይዌሩ፡ርእሶ፡ታሕተ፡ኵሎ፡ አሚረ።

፲፪፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ሶበ ፡ ተወርወ ፡ ጸንዐ ፡ ሰይጣን፡ ለቀቲሎቱ ፡ ወሞተ ፡ ወሶቤሃ ፡ መድኃኒነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ አንሥአ ፡ እሙታን፡ወይቤሎ፡እምይእዜሰ፡ኢይኩን፡ ስምከ፡ቡላ፡አላ፡ይኩን፡አቢብሃ፡እስመ፡ አበ፡ብዙኃን፡ትከውን።

፲፫፡ ወውእቱ ፡ ወሰከ ፡ አፍቅሮቶ ፡ ለክርስቶስ ፡ ጥቀ ፡ ወነበረ ፡ እንዘ ፡ ይጸፍዕ ፡ ገጾ ፡ ወይመትር፡ሥጋሁ፡በበግማድ፡ወይቀሥፍ፡ዘባኖ፡ ፫፻ተ፡ጊዜያተ፡ወእግዚእነ፡ይፌውሶ፡ወለለ እሑድ፡ያስተርእዮ፡ዘከመ፡ተወልደ፡እምቅ ድስት፡ድንግል፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ወበካ ልአት፡ዕለታት፡ተእኅዞ፡ወሕማማቲሁ፡ እምአይሁድ።

፲፬፡ ወበእንተዝ ፡ ነበረ ፡ እንዘ ፡ ኢይበልዕ ፡ ወኢይሰቲ ፡ ፵ወ፪ተ፡ዓመተ ፡ወዓዲ ፡ተተክለ ፡ በርእሱ ፡ ፲ወ፪ተ ፡ አውራኀ ፡ እስከ ፡ ሐልቀ ናላሁ።

፲፭፡ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ሶበ ፡ ሐለየ ፡ ሕማሞ፡ ለእግዚእነ፡ተከለ፡ሰይፎ፡በመንጸሩ፡ወዐርገ፡ዲበ፡ ዕፅ፡ወወድቀ፡ዲቤሁ፡ወሞተ፡ወመጽአት፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም፡ ምስለ፡መላእክት፡አእላፍ፡ወትቤሎ፡ሰላም፡

፱፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መኰንን ፡ ሒዶ፡ እርሱንና ፡ የረከሱ ፡ ጣዖቶቹን ፡ ረገመ ፡ መኰንኑም ፡ ተቆጥቶ ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ ቆረጠው ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልም ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ አስነሣው ፡ ወደ ፡ አንድ፡ገዳምም፡ወስዶ፡የምንኵስና፡ልብስ ንና፡አስኬማን፡በመስቀልም፡ምልክት፡አለ በሰው ። እንዲህም ፡ አለው ፡ ከቅዱሳን ፡ ጻድ ቃን ፡ አንድነት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ ብሔር፡አዝዞሃል።

፲፡ ያን፡ጊዜም፡ቅዱስ፡አባ፡ቡላ፡ከደረቅ፡ተራራ፡ ላይ፡ወጣ፡ያለ፡ማቋረጥም፡በውስጧ፡እየተ ጋደለ፡ኖረ።

፲፩፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መከራ ውንና ፡ ስቅለቱን ፡ በአሰበ ፡ ጊዜ ፡ ከረጅም ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ በመውጣት ፡ ራሱን ፡ ወደ ታች፡ሁል፡ጊዜ፡ይወረውር፡ነበር።

፲፪፡ በአንዲትም፡ቀን፡ከዛፍ፡ላይ፡በተወረወረ፡ ጊዜ፡ሰይጣን፡ሊገድለው፡ስለ፡በረታበት፡ ሞተ፡ያን፡ጊዜም፡ክብር፡ይግባውና፡መድ ኃኒታችን ፡ ከሞት ፡ አነሣውና ፡ እንዲህ ፡ አለው፡ከእንግዲህ፡ስምህ፡ቡላ፡አይሁን፡ አቢብ፡ይባል፡እንጂ፡የብዙዎች፡አባት፡ ትሆናለህና።

፲፫፡ እርሱም ፡ የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ እጅግ ፡ ጨመረ ፡ ፊቱንም ፡ እየጸፋ ፡ ሥጋውን ፡ በየጥቂቱ፡እየቆረጠ፡ጀርባውንም፡ሰባት፡ መቶ፡ ጊዜ ፡ እየገረፈ ፡ ኖረ ፡ ጌታችንም ፡ ይፈውሰው ፡ ነበር ፡ በየእሑድም ፡ ቀን ፡ ከቅድስት፡ድንግል፡እመቤታችን፡ማርያም፡ እንደተወለደ፡በሌሎች፡ቀኖችም፡እንደተ ያዘና፡ከአይሁድ፡መከራ፡እንደ፡ተቀበለ፡ ሁኖ፡ይገለጽለት፡ነበር።

፲፬፡ ስለዚህም፡ሳይበላ፡ሳይጠጣ፡አርባ፡ሁለት፡ ዓመት፡ኖረ፡ዳግመኛም፡ናላው፡ፈስሶ፡እስ ኪአልቅ ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ በራሱ ተተክሎ፡ኖረ።

፲፭፡ በአንዲትም ፡ ቀን ፡ የጌታችንን ፡ መከራ ፡ በአሰበ ፡ ጊዜ ፡ ሰይፉን ፡ በአንጻሩ ፡ ተከለ ፡ ከዕንጨት ፡ ላይም ፡ ወጥቶ ፡ በላዩ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችን ፡ ማርያምም ፡ ከአእላፍ ፡ መላእክት ፡ ጋር ፡

www.ethiopianorthodox.org

ለከ፡ኦ፡ፍቁርየ፡ወፍቁረ፡ወልድየ፡ወወጽአ፡ ቃል፡እምነ፡በድኑ፡ወይቤላ፡ሰላም፡ለኪ፡ ኦ፡እግዝእትየ፡ንግሥተ፡ሰማይ፡ወምድር፡ ወይእቲ፡ገሠሠቶ፡በእደዊሃ፡ወአንሥአቶ፡ እሞት።

፲፮፡ ወሶበ፡ፈጸመ፡መዋዕሊሁ፡ወበጽሐ፡ፍል ሰቱ፡እምዝንቱ፡ዓለም፡አስተርአዮ፡እግዚ እነ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡እንዘ፡ውስተ፡ እዴሁ፡አክሊላት፡ዘአዕናቍ፡ብዑዳት፡ወአል ባሳት፡ብሩሃት፡ወይቤሎ፡ነዓ፡ፍቁርየ፡ አቢብ፡ከመ፡አስተፍሥሕከ፡በፍሥሓ፡ዘኢ የኀልቅ፡ወመሐልኩ፡ለከ፡በርእስየ፡ከመ፡ ለኵሉ፡ዘይጼውዕ፡ስመከ፡ወይገብር፡ ተዝካረከ፡አነ፡እሰሪ፡ኃጢአቶ፡አው፡ ዘያለብስ፡ዕሩቀ፡ወያጸግብ፡ርኁበ፡ወያሰቲ፡ ጽሙዐ፡አው፡ዘየሐንፅ፡መርጡለከ፡ ወይጽሕፍ፡መጽሐፈ፡ገድልከ፡አው፡ ዘያነብቦ፡ወይሰምዖ፡ወለዘሂ፡ይትአመኑ፡ በጸሎትከ፡እምሕሮሙ፡እስከ፡፲ቱ፡ትው ልድ፡ወዘንተ፡ብሂሎ፡ሰዓሞ፡አፉሁ፡ወፆሮ፡ በእንግድዓሁ፡ወአዕረጎ፡ውስተ፡አየር፡ ወሶበ፡ሰምዓት፡ስብሐተ፡መላእክት፡ተፈል ጠት፡ነፍሱ፡እምሥጋሁ፡ወቦአት፡ውስተ፡ ኢየሩሳሌም፡ሰማያዊት።

፲፯፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐ ረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡መስተጋድል፡አብ፡ ክቡር፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

መጥታ፡የእኔና፡የልጄ፡ወዳጅ፡ሰላምታ፡ ይድረስህ፡አለችው። ከበድኑም፡ቃል፡ ወጥቶ፡የሰማይና፡የምድር፡ንግሥት፡ እመቤቴ፡ሰላምታ፡ይገባሻል፡አላት፡ እርሷም፡በከበሩ፡እጆቿ፡ዳሥሣ፡ከሞት፡ አስነሣቸው።

፲፮፡ ዕድሜውንም፡ፈጽሞ፡ከዚህ፡ዓለም፡የሚወ ጣበት፡ጊዜ፡ሲደርስ፡ክብር፡ይግባውና፡ ጌታችን፡ክርስቶስ፡በእጁ፡ልዩ፡የሆኑ፡አክሊ ሎችን፡የሚያበሩ፡ልብሶችንም፡ይዞ፡ተገለ ጠለት፡ወዳጄ፡አቢብ፡ሆይ፡በማያልቅ፡ ተድላ፡ደስታ፡ደስ፡አሰኝህ፡ዘንድ፡ወደእኔ፡ ና፡ስምህን፡ለሚጠራ፡መታሰቢያህን፡ለሚያ ደርግ፡እኔ፡ኃጢአቱን፡አስተሠርይለት፡ ዘንድ፡በራሴ፡ማልኩልህ፡ወይም፡ ለተራቆተ፡የሚያለብሰውን፡ለተራበም፡ የሚያጠግበውን፡ለተጠማ፡የሚያጠጣውን፡ የገድልህን፡መጽሐፍም፡የሚጽፈውን፡ ወይም፡የሚያነበውንና፡የሚሰማውን፡በጸ ሎትህም፡የሚታመኑትን፡ሁሉ፡እስከ፡ ዐሥር፡ትውልድ፡እምራቸዋለሁ፡ይህንም፡ ብሎ፡አፉን፡ሳመው፡በደረቱም፡ላይ፡ አድርጎ፡ወደአየር፡አወጣው፡የመላእክ ትንም፡ምስጋና፡በሰማች፡ጊዜ፡ነፍሱ፡ ከሥጋው፡ተለየች፡ወደ፡ሰማያዊት፡ኢየሩ ሳሌም፡ገባች።

፲፯፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡ እኛንም፡በዚህ፡በቅዱስ፡አባት፡ጸሎት፡ ይማረን፡በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለአቢብ፡ዘአስተጋብአ፡አሐተኔ።ምግባረ፡ጻድቃን፡ዘገዳም፡ወምግባረ፡ሰማዕት፡በኵርጓኔ። እስከ፡ይቤሎ፡አምላክ፡ቃለ፡አኰቴት፡ማኅዘኔ። ረሰይከኑ፡ለባሕቲትከ፡ኵነኔ። ዘመጠነዝ፡ታፃሙ፡ ነፍሰከ፡በቅኔ።

ተዘኪረከ፡ክርስቶስ፡ሥቃያተ፡አቢብ፡ብዙኀ። ወሩጸተ፡ነፍሱ፡ፍሉሐ። ኢታጽንዕ፡ብየ፡ልበከ፡ ርኁሩኀ።እስከ፡እትመየጥ፡መንገሌከ፡ጽንሐኒ፡ጸኒሐ።እስመ፡ድኅረ፡ሞቱ፡ለሰብእ፡አልቦቱ፡ንስሓ።

ሰላም፡እብል፡ዐሠርተ፡ወክልኤተ፡አምአተ። ወአርብዓ፡ወሠለስተ፡ተባዕተ። ወሠለስተ፡ምእተ፡ ወሰብዓተ፡አንስተ። ሶበ፡ርእዩ፡ውስተ፡ዓውድ፡ዘአቢብ፡ጥብዓተ።እለ፡ተጋደሉ፡ወኮኑ፡ሰማዕተ።

፲፰፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ካዕበ፡አዕረፈ፡አባ፡ እብሎይ፡አምሳለ፡መላእክት፡ዘእምሀገረ፡ አክሚም።

፲፰፡ በዚችም፡ቀን፡ደግሞ፡አክሚም፡ከሚባል፡ አገር፡የመላእክት፡አምሳል፡የሆነ፡አባ፡ እብሎይ፡አረፈ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፱፡ ወለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ ስመ ፡ አቡሁ ፡ አሞኒ ፡ ወስማ ፡ ለእሙ ፡ ሙሲያ ፡ ወክልኤሆሙ ፡ ጻድቃን ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወየሐውሩ፡ውስተ፡ፍኖቱ፡ወያፈቅርዎሙ፡ ለፈላስያን፡ወለነዳያን።

፳፡ ወባሕቱ ፡ ኢኮነ ፡ ሎሙ ፡ ወልድ ፡ ወርእየት ፡ ራእየ ፡ ሙስያ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ብርሃናዊ ፡ ወምስሌሁ ፡ ዕፅ፡ ወተከሎ ፡ ውስተ ፡ ቤታ ፡ ወበጊዜሃ፡ሠረፀ፡ወጸገየ፡ወፈረየ።ወይቤላ፡ ውእቱ ፡ ብርሃናዊ ፡ ኵሉ ፡ ዘይበልዕ፡ እምዝንቱ፡ፍሬ፡የሐዩ፡ለዓለም።ወይእቲ፡ እንዘ ፡ ትነሥእ ፡ ወትበልዕ ፡ ወይከውን፡ ውስተ፡አፉሃ፡ጥዑመ፡ወትብል፡በልባ፡ይከ ውነኒ፡ሊተ፡ፍሬ።

፳፩፡ወሶበ፡ነቅሐት፡እምንዋማ፡ነገረቶ፡ለምታ፡ ዘከመ፡ርእየት ፡ ውእቱኒ ፡ አይድዓ ፡ ዘከመ ፡ ርእየ፡ በከመ ፡ ርእየት ፡ ይእቲ ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብዙኀ ፡ ወወሰኩ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ወተጋድሎ ፡ ወይጸውሙ ፡ በበ፪ቱ ፡ መዓልት፡ወሲሳዮሙ፡ኀብስት፡ወጼው።

፳፪፡ ወሶበ ፡ ፀንሰቶ ፡ ለቅዱስ ፡ እብሎይ ፡ ኮነት ፡ እሙ ፡ ዘትጼሊ ፡ ጸሎታተ ፡ ብዙኀተ ፡ እስከ፡ ትመውዖሙ፡ለዕደው፡ለለኵሎን፡ለያልይ፡ ትሰግድ ፡ ፲፻ተ፡ ስግደታተ ፡ በመዓልትሰ ፡ ፫፻ተ፡ ስግደታተ ፡ መጠነ ፡ ፱ቱ ፡ አውራኅ ፡ እስከ፡ወለደቶ፡ለሕፃን።

፳፫፡ ወሶበ፡ወለድዎ፡ሰመይዎ፡ስሞ፡እብሎይሃ፡ ወሶበ፡ ወርዘወ ፡ ፈተወ ፡ ይልበስ ፡ አልባሰ ፡ ምንኵስና፡ወነበረ፡ከመዝ፡እስከ፡ይረክብ፡ ምክንያተ ፡ ወኮነ ፡ ሎቱ ፡ ዐርክ ፡ ዘስሙ ፡ አቢብ፡ውእቱኒ፡ነሥአ፡ምስሌሁ፡ወወሰዶ፡ በሌሊት፡ወመንኰሰ፡ውስተ፡፩ዱ፡ደብር፡ እምአድባራት፡ዘላዕላይ፡ግብጽ፡ወተጸምደ፡ በገድል፡ወተጋደለ፡ገድለ፡ዐቢየ።

፳፬፡ወእምድኅረ፡ኀዳጥ፡መዋዕል፡አዕረፈ፡አባ፡ አቢብ፡ አመ ፡ ፳ወ፫ ለወርኀ ፡ ጥቅምት ፡ አሚሃ ፡ ሖረ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ እብሎይ ፡ ኀበ ፡ ደብረ፡አብሎግ፡ወተጋብኡ፡ኀቤሁ፡ሰብእ፡ ብዙኃን፡ወኮነ፡ውእቱ፡ይሜህሮሙ፡ፈሪሀ፡ እግዚአብሔር፡በአምልኮ፡ሠናይ።

፲፱፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ አሞኒ፡ የእናቱ፡ ስም ፡ ሙሲያ ፡ ነው ፡ ሁለቱም ፡ በእግ ዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቃን ፡ የሆኑ ፡ በሕጉ ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ ድኆችንና ፡ መጻተ ኞችን፡የሚወዱ፡የሚረዱ፡ናቸው።

፳፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ አልነበራቸውም ፡ ሙስያም፡ ዕንጨት ፡ የያዘ ፡ ብርሃናዊ ፡ ሰው ፡ በቤቷ ፡ ውስጥ ፡ ሲተክለውና ፡ ወዲያውኑ ፡ ለምልሞ፡ አብቦ ፡ ሲያፈራ ፡ ያ ፡ ብርሃናዊው ፡ ሰውም፡ ከዚህ፡ ፍሬ ፡ የሚበላ ፡ ሁሉ ፡ ለዘላለም ፡ ይኖራል ፡ ሲላት ፡ እርሷም ፡ ከፍሬው ፡ ወስዳ፡ ስትበላና ፡ በአፏ ፡ ውስጥ ፡ ጣፋጭ ፡ ሲሆንላት፡ በልቧም ፡ ፍሬ ፡ ይሆንልኝ ፡ ይሆን ፡ ስትል፡ ራእይን፡አየች።

፳፩፡ ከእንቅልፏም ፡ በነቃች ፡ ጊዜ ፡ ራእይን ፡ እንዳየች፡ ለባሏ ፡ ነገረችው ፡ እርሱም ፡ እርሷ፡ እንዳየችው ፡ ያለ ፡ ማየቱን ፡ ነገራት ፡ እግዚአ ብሔርንም ፡ አብዝተው ፡ አመሰገኑት ፡ ትሩፋ ትንና ፡ ተጋድሎን ፡ በመጨመር ፡ በየሁለት፡ ቀን ፡ የሚጾሙ ፡ ሆኑ ፡ ምግባቸውም ፡ እን ጀራና፡ጨው፡ነው።

፳፪፡ ይህን፡ቅዱስ፡እብሎይን፡በፀነሰችው፡ጊዜ፡ እናቱ፡በገድል፡ወንዶችን፡እስከምታሸንፍ፡ ድረስ ፡ በየሌሊቱ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሺህ፡ ስግደትን ፡ እየሰገደች ፡ ብዙ ፡ ጸሎቶችን ፡ ትጸልይ፡ነበር።በቀን፡ግን፡አምስት፡መቶ፡ ስግደትን ፡ ትሰግዳለች ፡ ሕፃኑን ፡ እስከ ፡ ወለደችው ፡ ድረስ ፡ ዘጠኝ፡ ወር ፡ ያህል ፡ እንዲህ፡ስትጋደል፡ኖረች።

፳፫፡ በወለዱትም ፡ ጊዜ ፡ እብሎይ ፡ ብለው ፡ ሰየሙት፡በጐለመሰም፡ጊዜ፡የምንኵስናን፡ ልብስ፡ሊለብስ፡ወደደ፡ምክንያትም፡እስቲ ያገኝ ፡ እንዲህ ፡ ኖረ ፡ አቢብ ፡ የሚባል ፡ ወዳጅ፡ ነበረውና፡እርሱ፡በሌሊት፡ወስደው፡ ከላዕላይ፡ግብጽ፡በሚገኙ፡ገዳማት፡በአንዱ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ መነኰሰ ፡ በገድልም፡ በመጠ መድ፡ታላቅ፡ተጋድሎን፡ተጋደለ።

፳፬፡ከጥቂት ወራትም፡በኋላ፡በጥቅምት፡ወር፡ሃያ፡ አምስት፡ቀን፡አባ፡አቢብ፡አረፈ፡ያን፡ጊዜ፡ አባ፡እብሎይ፡አብሎግ፡ወደሚባል፡ገዳም፡ ሔደ፡ ወደርሱም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ፡ እርሱም ፡ በበጎ ፡ አምልኮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራትን፡የሚያስተምራቸው፡ሆነ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፫፡ ወበዕለተ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለቅዱስ ፡ አባ ፡ አቢብ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ተዝካሮ ፡ ይቤሎሙ ፡ ዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ እብሎይ ፡ ኦ ፡ አኃው ፡ ዘይጼሊ ፡ ጸሎተ ፡ ዮም፡ በስሙ ፡ ለአባ ፡ አቢብ ፡ይሰሪ ፡ ሎቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ኃጢአቶ ፡ እስመ ፡ ተካየዶ ፡ እንዘ፡ ይብል ፡ ኦ ፡ ኅሩይየ ፡ አቢብ ፡ ለኵሉ ፡ዘይጼሊ ፡ በዕለተ ፡ ተዝካርከ ፡ አሐተ ፡ ጸሎተ ፡ ወይብል ፡ አምላኩ ፡ ለአባ ፡ አቢብ ፡ ስረይ ፡ ኵሎ ፡ ኃጢአትየ ፡ አነ ፡ አኃድግ ፡ ኃጢአቶ ፡ ኵሎ።

፳፬፡ ወበይእቲ ፡ ሰዓት ፡ አዕረፈ ፡ አሐዱ ፡ እምአኃው ፡ ወእሙንቱ ፡ ይቀውሙ ፡ በህየ ፡ ከመ ፡ ይግንዝዎ ፡ ወናፈቀ ፡ አሐዱ ፡ እመነ ኰሳት ፡ በእንተ ፡ ዘይቤ ፡ አባ ፡ እብሎይ ፡ ወሶቤሃ ፡ ተንሥአ ፡ውእቱ ፡ ምውት ፡ ወአኀዘ ፡ ይትናገር ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለምንት ፡ ትናፍቁ ፡ በእንተ ፡ ቃሉ ፡ ለአባ ፡ እብሎይ ፡ እስመ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ተካየዶ ፡ ለአቡነ ፡ አቢብ፡ በዝንቱ ፡ ኪዳን ፡ በዕለተ ፡ ተዝካሩ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ፡ ተመይጠ ፡ ወአዕረፈ ፡ ወአንከሩ ፡ አኃው ፡ ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስቡሕ።

፳፭፡ ወሐይወ ፡ ዝንቱ ፡ አባ ፡ እብሎይ ፡ ብዙኀ ፡ አዝማነ፡ ወበዝኀ ፡ ውሉዱ ፡ መነኰሳት ፡ ወኮኑ ፡ሎቱ ፡ብዙኃት ፡ ገዳማት።

፳፮፡ ወመዋዕሊሁኒ ፡ ኮነ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለአባ ፡ መቃርስ ፡ ዘየዐቢ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ዜና ፡ ምግባሩ ፡ ለአባ ፡ እብሎይ ፡ ተፈሥሐ ፡ ቦቱ ፡ ፈድፋደ ፡ ወጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ መልእክተ ፡እንዘ ፡ ይናዝዞ ፡ ወያጸንዖ ፡ ሎቱ ፡ ወለውሉዱ ፡ መነኰሳት ፡ ከመ፡ ያጽንዖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ውስተ ፡ ገቢረ ፡ ሥምረቱ።

፳፯፡ ወእንዘ ፡ ዘንተ ፡ ይጽሕፍ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ በገዳመ ፡ አስቄጥስ ፡ አእመረ ፡ አባ ፡ እብሎይ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በላዕላይ ፡ ግብጽ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለመነኰሳት ፡ እለ ፡ የዓውድዎ ፡ ናሁ ፡ ጸሐፈ ፡ ለነ ፡ መልእክተ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ እንተ ፡ ምልዕት ፡ ኑዛዜ ፡ ወእምዝ ፡ ወጽኡ ፡ ወተቀበልዎሙ ፡ ለመን ኰሳት ፡ ፍንዋን ፡ እምኀበ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ወአብእዎሙ ፡ በፍሥሓ ፡ ወአንበቡ ፡ መልእክቶ ፡ በቅድመ ፡ ኵሎሙ ፡ መነኰሳት ፡ ወተፈሥሑ ፡ ዐቢየ ፡ ፍሥሓ።

፳፫፡ ቅዱስ፡ አቢብም ፡በአረፈበት ፡ ቀን ፡ መታሰቢ ያውን ፡ ሲያደርጉ ፡ ይህ ፡ ቅዱስ ፡ አባ ፡ እብሎይ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ በአባ ፡ አቢብ ፡ስም ፡ ዛሬ ፡ ጸሎትን ፡ የሚጸልየውን ፡ ኃጢአቱን ፡ እግዚአ ብሔር ፡ያስተሰርይለታል፡ በዕረፍትህ ፡ መታ ሰቢያ ፡ ቀን ፡ የአባ ፡ አቢብ ፡ ፈጣሪ ፡ ሆይ ፡ ኃጢአቴን ፡ ሁሉ ፡ ተውልኝ ፡ ብሎ ፡ አንዲት ፡ ጸሎትን ፡ የሚጸልየውን ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ ኃጢአ ቱን ፡ እተውለታለሁ ፡ ሲል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሰጥ ቶታልና ፡ አላቸው።

፳፬፡ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ከመነኰሳት ፡ አንዱ ፡ አረፈ፡ እነርሱም ፡ ሊገንዙት ፡ በዚያ ፡ ቁመው፡ ሳሉ ፡ አባ፡ እብሎይ ፡ ስለ ፡ ተናገረው፡ ቃል ፡ ከመነ ኰሳት ፡ አንዱ ፡ ተጠራጠረ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ፡ ያ፡ የሞተው ፡ ተነሥቶ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ጀመረ፡ አባ፡ እብሎይ ፡ ስለተናገረው ፡ ቃል ፡ ለምን ፡ ትጠራጠራላችሁ ፡ ለአባታችን ፡ አቢብ በመ ታሰቢያው ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እግዚአ ብሔር ፡ሰጥቶናልና ፡ አላቸው ። ይህንንም ፡ ብሎ ፡ ተመልሶ ፡ አረፈ ፡ መነኰሳቱም ፡ አደ ነቁ ፡ ምስጉን ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰ ገኑት።

፳፭፡ ይህ ፡ አባ ፡ እብሎይም ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ ኖረ፡ ልጆቹ፡ መነኰሳትም ፡ በዙ ፡ ብዙ ፡ ገዳማትም፡ ተሠሩለት።

፳፮፡ የኖረበትም ፡ ዘመኑ ፡ በታላቁ ፡ አባ ፡ መቃርስ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ የአባ ፡ እብሎይንም ፡ የትሩፋቱን፡ ዜና ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስ፡ ተሰኘበት ፡ እርሱን ፡ እያጽናና ፡ እያረጋጋ፡ መነ ኰሳት ፡ ልጆቹንም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወ ደውን ፡ በመሥራት ፡ ያጸናቸው ፡ ዘንድ ፡ መልእ ክትን ፡ ጻፈለት።

፳፯፡ ይህንንም ፡ በአስቄጥስ ፡ ገዳም ፡ ሁኖ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ሲጽፍ ፡ አባ ፡ እብሎይ ፡ በላዕላይ ፡ ግብጽ፡ ሳለ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አውቆ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ መነኰሳት ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ። እነሆ ፡ ማጽናናትን ፡ የተመላች ፡ መልእክትን ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ ጻፈልን ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከአባ ፡ መቃርስ ፡ ዘንድ ፡ የተላ ኩትን ፡ መነኰሳት ፡ ሁሉ ፡ ወጥተው ፡ በደስታ፡ ተቀብለው ፡ አስገቧቸው፡ መልእክቱንም ፡ በመነኰሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ አነበቡ ፡ በታላቅ፡ ደስታም ፡ ደስ ፡ አላቸው።

www.ethiopianorthodox.org

፴፡ ወዝንቱ ፡ አባ ፡ እብሎይ ፡ ዘሖረ ፡ ኀበ ፡ አባ ፡
አሞንዮስ ፡ ወርእያ ፡ ለቅድስት ፡ ብእሲት ፡
እንተ፡ስማ፡የዋሂት፡ዘትነብር፡በኀቤሁ።

፴፩፡ ወእምዝ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ያዕርፎ ፡ እምፃማ ፡
ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወአዕረፈ ፡ አመ ፡ ፳ ለወርኀ ፡
የካቲት ፡ ንሕነሰ ፡ ጸሐፍነ ፡ ዜናሁ ፡ ለአባ ፡
እብሎይ፡ምስለ፡ዐርኩ፡አባ፡አቢብ።

፴፪፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም
ሐረነ፡በጸሎቶሙ፡ለቅዱሳን፡አበዊነ፡ወበረ
ከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ ዓለም
አሜን።

፴፫፡ወበዛቲ፡ዕለት፡ካዕበ፡ኮነ፡ቅዳሴ፡ቤተ፡ክርስ
ቲያኑ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮልዮስ ፡ ሰማዕት ፡ ዘእም
ሀገረ፡አቅፋሐስ።

፴፬፡ወዝንቱ፡ቅዱስ፡ዮልዮስ፡ሶበ፡ኮነ፡ሰማዕተ፡
በሀገረ ፡ ጥዋ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ በገድሉ ፡
ውእቱኬ፡እምድኅረ፡ጥፍአቱ፡ለዲዮቅልጥ
ያኖስ፡ወነግሠ፡ሎሙ፡ብእሲ፡ጻድቅ፡ቈስጠ
ንጢኖስ፡እምቅድመ፡ይጠመቅ፡ጥምቀተ፡
ክርስትና ፡ ወበኀዳጥ፡ መዋዕል ፡ ሶበ ፡ ተጠ
ምቀ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ተለዓለ ፡ ቀርና ፡
ለቤተ፡ክርስቲያን፡ወተሐንፃ፡አብያተ፡ክር
ስቲያናት ፡ በስሞሙ ፡ ለሰማዕት፡ ንጹሐን ፡
እለ፡ቀተልዎሙ፡ነገሥት፡ከሀድያን።

፴፭፡ ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡
ዜናሁ፡ ለቅዱስ ፡ ዮልዮስ ፡ ከመ ፡ አቀሞ ፡
ወዐቀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ የሐሊ ፡
በእንተ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ ቅዱሳን፡
ይግንዞሙ ፡ ወይፀውሮሙ ፡ ኀበ ፡ ሀገሮሙ ፡
ምስለ፡አግብርቲሁ፡ወይጽሐፍ፡ገድሎሙ፡
ወእምድኅረዝ፡ዘከመ፡እፎ፡ኮነ፡ሰማዕተ፡
ለሊሁ ፡ ወወደሶ ፡ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡
ለቅዱስ፡ዮልዮስ፡በእንተ፡ሠናይ፡ገድሉ።

፴፮፡ ወበእንተዝ ፡ ፈነወ ፡ ንጉሥ ፡ ኀበ ፡ ብሔረ ፡
ግብጽ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ይሕ
ንፁ ፡ ሎቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠናይተ ፡
ወያንብሩ ፡ ሥጋሁ ፡ ውስቴታ ። ወይእተ ፡
አሚረ፡ሐነፁ፡ሎቱ፡በከመ፡አዘዘ፡ንጉሥ፡
ወአፍለሱ፡ሥጋሁ፡ለቅዱስ፡ዮልዮስ፡ወአን
በርዎ፡ውስቴታ፡ወቀደሳ፡አባ፡እለእስክን

፴፡ ይህም ፡ አባ ፡ እብሎይ ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አሞን
ዮስ፡ የሔደ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድም ፡ የምትኖ
ረውን፡ ስሟ ፡ የዋሂት ፡ የተባለችውን ፡ የተቀ
ደሰች፡ሴት፡ያየ፡ነው።

፴፩፡ክብር፡ይግባውና፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስ
ቶስም፡ከዚህ፡ዓለም፡ድካም፡ሊአሳርፈው፡
ወዶ፡በየካቲት፡ወር፡በአምስተኛው፡ቀን፡
አረፈ ፡ እኛ ፡ ግን ፡ የአባ ፡ እብሎይን ፡ ዜና
ከወዳጁ፡ከአባ፡አቢብ፡ጋር፡ጻፍን።

፴፪፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ
ንም፡ በቅዱሳን ፡ አባቶቻችን ፡ ጸሎት ፡ ይማ
ረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡
ለዘላለሙ፡አሜን።

፴፫፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ዳግመኛ ፡ አቅፋሐስ ፡ ከሚ
ባል ፡ አገር ፡ ሰማዕት ፡ ለሆነ ፡ ለቅዱስ ፡
ዮልዮስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የከበረችበት ፡
ነው።

፴፬፡ይህም፡ቅዱስ፡ዮልዮስ፡በሀገረ፡ጥዋ፡በሰማዕ
ትነት፡በአረፈ፡ጊዜ፡በገድሉ፡እንደተጻፈ፡
ዲዮቅልጥያኖስ፡ከጠፋ፡በኋላ፡ጻድቅ፡ሰው፡
ቈስጠንጢኖስ ፡ ሳይጠመቅ ፡ ነገሠላቸው ፡
በጥቂት፡ወራትም፡የክርስትና፡ጥምቀትን፡
ተጠመቀ፡የቤተ፡ክርስቲያንም፡ሥልጣን፡
ከፍ፡ከፍ፡አለ፡ከሀድያን፡ነገሥታት፡ለገደ
ሏቸው፡ ንጹሐን ፡ ሰማዕታት ፡ በስማቸው ፡
አብያተ፡ክርስቲያናት፡ታነፁ።

፴፭፡ስለ፡ቅዱሳን፡ሰማዕታትም፡ስለ፡ሥጋቸው፡
እንዲአስብ ፡ ገንዞ ፡ በመሸከም ፡ ወደ ፡ አገ
ራቸው፡እንዲአደርሳቸው፡ከአገልጋዮቹም፡
ጋር፡ገድላቸውን፡እንዲጽፍ፡እግዚአብሔር፡
እንደአቆመውና፡እንደጠበቀው፡ከዚህም፡
እርሱ፡ራሱ፡በሰማዕትነት፡እንዴት፡እንደ
ሞተ፡የቅዱስ፡ዮልዮስን፡ዜና፡ንጉሥ፡ቈስ
ጠንጢኖስ፡በሰማ፡ጊዜ፡ስለበጎ፡ተጋድሎው፡
ንጉሥ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡ ቅዱስ፡ ዮልዮስን ፡
አመሰገነው።

፴፮፡ስለዚህም፡ለቅዱስ፡ዮልዮስ፡ያማረች፡ቤተ፡
ክርስቲያን ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሠርተው ፡
ሥጋውን፡በውስጧ፡ያኖሩ፡ዘንድ፡ንጉሡ፡
ወደ ፡ ግብጽ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ላከ ፡
በዚያንም ፡ ጊዜ፡ ንጉሡ ፡ እንዳዘዘ ፡ አነፁ
ለት። የቅዱስ፡ ዮልዮስንም ፡ ሥጋ ፡ አፍል
ሰው፡በውስጧ፡አኖሩት፡ሊቀ ጳጳሳት፡አባ፡

www.ethiopianorthodox.org

ድሮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ምስለ፡ኤጲስቆጶሳቲሁ፡ ወገብረ፡ባቲ፡በዓለ፡ዐቢየ፡በከመ፡ዛቲ፡ዕለት፡ ወኮና፡እምሥጋሁ፡ለቅዱስ፡ዮልዮስ፡ተአ ምራት፡ወመንክራት፡ዐበይት።

፴፯፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይም ሐረነ፡በጸሎቱ፡ወበረከቱ፡ተሀሉ፡ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

እለእስክንድሮስም፡ከኤጲስቆጶሳቱ፡ጋር፡ አከበራት፡እንደዛሬዪቱም፡ቀን፡በዓል፡አከ በረባት፡ከሥጋውም፡ታላላቅ፡የሆኑ፡ድን ቆች፡ተአምራት፡ተገለጡ።

፴፯፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛ ንም፡በጸሎቱ፡ይማረን፡በረከቱም፡ከእኛ፡ ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

<u>አርኬ</u>

ሰላም፡ለቅዳሴ፡ቤትከ፡በጉባኤ፡ሕዝብ፡ክቡድ። ወለተአምሪከ፡ዓዲ፡ዘኍላቌሁ፡ፍድፋድ። አመ፡ አገትዎ፡ዐሩ፡አምሳለ፡ማዕድ። በከመ፡መጠቆ፡ለቈስጠንጢኖስ፡እምባዕድ። መንገለ፡ጥበብ፡ምጥቀኒ፡ ዮልዮስ፡ለአብድ።

* * *

፩፡ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ፡አመ፡ ፳ወ፮፡ ለጥቅምት በዛቲ፡ ዕለት፡ኮነ፡ሰማዕተ፡ቅዱስ፡ጢሞና፡ሐዋርያ፡ ፩ዱ፡እም፸ወ፪ቱ፡አርድእት፡ዘኀረዮሙ፡ እግዚእነ፡ወወሀቦሙ፡ሥልጣነ፡ከመ፡ይፈ ወሱ፡ኵሎ፡ዱያነ፡ወያውጽኡ፡አጋንንተ።

፪፡ ወዝንቱ፡ቅዱስ፡ጢሞና፡ነሥአ፡ሀብተ፡ሰማ ያዊተ፡ወኃይለ፡መለኮታዊተ፡ወባቲ፡ፈወ ሶሙ፡ለድውያን፡ወገረሩ፡ሎቱ፡አጋንንት፡ወተ ልእኮ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ ስብሐት፡እንዘ፡ሀሎ፡በሥጋ፡ዲበ፡ምድር፡ ወድኅረኒ፡ዐርገ፡እግዚእነ፡ውስተ፡ሰማይ፡ ተልእኮሙ፡ለሐዋርያት፡ወነሥአ፡ምስሌ ሆሙ፡ጸጋ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ጰራቅሊጦስ፡ ሶበ፡ወረደ፡ላዕሌሆሙ፡በበዓለ፡፶ሳ።

፫፡ ወእምድኅረዝ፡ሤምዎ፡ሐዋርያት፡ውስተ፡ ኍልቆሙ፡ለሰብዓቱ፡ዲያቆናት፡ዘኮነ፡ ስምዐ፡መጽሐፈ፡ግብረ፡ሐዋርያት፡በእንቲ አሆሙ፡ከመ፡እሙንቱ፡ምሉዐነ፡መንፈስ ቅዱስ፡ወጥበብ።

፬፡ ወእምድኅረ፡ተልእኮ፡በመልእክተ፡ዲቁና፡ ኅዳጠ፡መዋዕለ፡ሤምዎ፡ኤጲስቆጶሰ፡ላዕለ፡ ሀገረ፡ስብራ፡ዘምዕራብ፡ብሔረ፡ብልቃ፡ ወሰበከ፡ውስቴታ፡ሃይማኖተ፡እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡ወአጥ መቆሙ፡ለብዙኃን፡እምዮናናውያን፡ወአ ይሁድ።

፭፡ ወሶበ፡ሰምዐ፡ዘንተ፡መኰንነ፡ይእቲ፡ሀገር፡

፩፡ አንድ፡አምላክ፡በሚሆን፡በአብ፡በወልድ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ጥቅምት፡ሃያ፡ ስድስት፡በዚች፡ቀን፡ጌታችን፡ከመረጣ ቸውና፡በሽተኞችን፡ሁሉ፡ይፈውሱ፡ዘንድ አጋንንትንም፡ያወጡ፡ዘንድ፡ሥልጣንን፡ ከሰጣቸው፡ከሰባ፡ሁለቱ፡አርድእት፡አንዱ፡ ቅዱስ፡ሐዋርያ፡ጢሞና፡በሰማዕትነት፡ አረፈ።

፪፡ ይህም፡ቅዱስ፡ጢሞና፡ሰማያዊ፡ሀብትን፡መለ ኮታዊ፡ኃይልን፡ገንዘብ፡አድርጎ፡በሽተኞ ችን፡ፈወሳቸው፡አጋንንትም፡ተገዙለት፡ ክብር፡ይግባውና፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ በሥጋ፡በምድር፡ሳለ፡አገለገለው። ወደ፡ ሰማይም፡ከዐረገ፡በኋላ፡ሐዋርያትን፡አገለገ ላቸው፡በሃምሳኛው፡ቀንም፡ጰራቅሊጦስ፡ በወረደ፡ጊዜ፡የአጽናኝ፡መንፈስ፡ቅዱስን፡ ጸጋ፡ከእርሳቸው፡ጋር፡ተቀበለ።

፫፡ ከዚህም፡በኋላ፡ሰባት፡ሁነው፡ከተቆጠሩት፡ ዲያቆናት፡ጋር፡ሐዋርያት፡ሾሙት፡እነርሱ፡ መንፈስ፡ቅዱስን፡ዕውቀትንም፡የተመሉ፡ እንደሆኑ፡የሐዋርያት፡ሥራ፡መጽሐፍ፡ ምስክር፡ሁኖአል።

፬፡ በዲቁና፡አገልግሎትም፡ጥቂት፡ከአገለገለ፡ በኋላ፡ብልቃ፡ከሚባል፡አገር፡በስተም ዕራብ፡በሆነ፡ስብራ፡በሚባል፡አገር፡ላይ፡ ኤጲስቆጶስነት፡ሾሙት፡በውስጧም፡ክብር፡ ይግባውና፡የጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ ሃይማኖት፡አስተማረ፡ከዮናውያንና፡ከአይ ሁድም፡ብዙዎችን፡አጠመቃቸው።

፭፡ የዚያች፡አገር፡ገገርም፡ይህን፡በሰማ፡ጊዜ፡

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ ወካልዕተ፡ጊዜ፡ርእዮ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት፡ እንዘ፡ ይነብር፡ ዲበ፡ምሥዋዕ፡ወመላእክት፡ያቄርቡ፡ሎቱ፡ ምግባራቲሆሙ፡ ለኵሎሙ፡ ሰብእ፡ ለለ ፩ ፩ ዱ፡ ወሶቤሃ፡ሰምዐ፡ቃለ፡ዘይብል፡ኦ፡ኤጲስ ቆጶስ፡ለምንት፡ትትዔወር፡እምሕዝብ፡ወኢ ትጌሥጾሙኑ፡ወኢትሜህሮሙኑ፡ውእቱኒ፡ አውሥአ፡ወይቤ፡እግዚኦ፡እሙንቱ፡ኢተ ወክፉ፡ቃልየ፡ወይቤሎ፡ካዕበ፡ይደልዎ፡ለኤ ጲስቆጶስ፡ይምሀሮሙ፡ለሕዝቡ፡ወለእመሰ፡ ኢተወክፉ፡ቃሎ፡ደሞሙ፡ላዕለ፡ርእሶሙ።

፮፡ ወእምዝ፡ጸውዕዎ፡ከመ፡ይሑር፡ምስለ፡አባ፡ ዲዮስቆሮስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ኀበ፡ጉባኤ፡ዘአስ ተጋብአ፡መርቅያኖስ፡ዕልው፡ንጉሥ፡እሉሂ ጉባኤ፡ዘረሰይዎ፡ለዋሕድ፡ክርስቶስ፡፪ተ፡ ጠባይዓተ፡ወበጺሖ፡ከልእዎ፡በዊአ፡ውስተ፡ ጽርሐ፡ንጉሥ፡በእንተ፡አልባሲሁ፡ርሱሐት፡ ወነገሮሙ፡አባ፡ዲዮስቆሮስ፡ከመ፡ውእቱ፡ ጳጳስ፡ወያብእዎ፡ምስሌሁ።

፯፡ ወሶበ፡ ቦኡ፡ ሰምዑ፡ አሚኖቶሙ፡ ከመ፡ ረሰይዎ፡ለአሐዱ፡ክርስቶስ፡፪ተ፡ጠባይዓተ፡ ወፈለጥዎ፡ ለትስብእቱ፡ እመለኮቱ፡ ወበእ ንተዝ፡አውገዝዎሙ፡ለንጉሥ፡ወለማኀበር፡ እስመ፡ እሉ፡ አበዊነ፡ አባ፡ ዲዮስቆሮስ፡ ወአባ፡ መቃርስ፡መጠዉ፡ነፍሶሙ፡ለሞት፡ በእንተ፡ሃይማኖቶሙ፡ርትዕት፡ወሰደዶሙ፡ ንጉሥ፡ውስተ፡ደሴተ፡ጋግራ።

፰፡ ወእምህየ፡ ፈነዎ፡ አባ፡ ዲዮስቆሮስ፡ ኀበ፡ ሀገረ፡ እስክንድርያ፡ ምስለ፡ ብእሲ፡ ነጋዲ፡ መሐይምን፡እስመ፡ውእቱ፡ተነበየ፡ሎቱ፡ ለአባ፡መቃርስ፡ወይቤሎ፡አንተሰ፡ሀለወከ፡ ትንሣእ፡ አክሊለ፡ ስምዕ፡ በሀገረ፡ እስክን ድርያ።

፱፡ ወሶበ፡ በጽሐ፡ ሀገረ፡ እስክንድርያ፡ አባ፡ መቃርስ፡በውእቱ፡ጊዜ፡በጽሐ፡መልእክቱ፡ ለንጉሥ፡መርቅያን፡ዐላዊ፡ዘጽሑፍ፡ውስቴቱ፡ ሃይማኖቱ፡ እኪት፡ ወአ፲፱፡ ለላእኩ፡ እንዘ፡ ይብል፡ ዘጸሐፊ፡ ቀዳሚ፡ ውስተ፡ ዝንቱ፡ መጽሐፍ፡ ወአምነ፡ በሃይማኖተ፡ ዚአነ፡ ይኩን፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ላዕለ፡ ሀገረ፡ እስክን

፭፡ ሁለተኛ፡ጊዜም፡ክብር፡ይግባውና፡ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በመሠዊያው፡ላይ፡ተቀ ምጦ፡ የየአንዳንዱን፡ የሰውን፡ ሥራ፡ መላ እክት፡ ሲያቀርቡለት፡ አየው፡ በዚያንም፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ የሚል፡ ቃል፡ ሰማ፡ ኤጲስ ቆጶስ፡ሆይ፡ለምን፡ቸለል፡ትላለህ፡ሕዝቡን፡ አትገሥጻቸውምን፡አታስተምራቸውምን፡እር ሱም፡ አቤቱ፡ እነርሱ፡ ትምርቴን፡ አይቀ በሉም፡ ብሎ፡ መለሰ። ሁለተኛም፡ እንዲህ፡ አለው፡ ለኤጲስቆጶስ፡ ሕዝቡን፡ ማስተማር፡ ይገባዋል፡ትምርቱን፡ካልተቀበሉ፡ግን፡ደማ ቸው፡በራሳቸው፡ይሆናል።

፮፡ከዚህም፡በኋላ፡መናፍቁ፡ንጉሥ፡መርቅያኖስ፡ ወደ፡ሰበሰበው፡ጉባኤ፡ከሊቀ፡ጳጳሳቱ፡ዲዮስ ቆሮስ፡ጋር፡ይሔድ፡ዘንድ፡ጠሩት፡የተሰበሰ ቡትም፡አንዱን፡ክርስቶስ፡ሁለት፡ባሕርይ፡ የሚሉ፡ናቸው፡በደረሰም፡ጊዜ፡ስለ፡ልብሱ፡ አዳፋነት፡ወደ፡ንጉሥ፡አዳራሽ፡መግባትን፡ ከለከሉት፡አባ፡ዲዮስቆሮስም፡ከእርሱ፡ጋር፡ እንዲአስገቡት፡ጳጳስ፡መሆኑን፡ነገራቸው።

፯፡ በገቡም፡ ጊዜ፡ አንዱን ክርስቶስን፡ ሁለት፡ ባሕርይ፡አድርገው፡ትስብእቱን፡ከመለኮቱ፡ እንደለዩት፡እምነታቸውን፡ሰሙ፡ስለዚህም፡ ንጉሡንና፡ጉባኤውን፡አወገዙአቸው፡እሊህ፡ አባቶቻችን፡ አባ፡ ዲዮስቆሮስና፡ አባ፡ መቃርስ፡ስለ፡ቀናች፡ሃይማኖታቸው፡ነፍሳ ቸውን፡ለሞት፡አሳልፎ፡ለመስጠት፡ቆርጠ ዋልና፡ ንጉሡም፡ ወደ፡ ደሴተ፡ ጋግራ፡ አጋዛቸው።

፰፡ከዚያም፡ከምእመን፡ነጋዴ፡ጋር፡ወደ፡እስክን ድርያ፡አባ፡ዲዮስቆሮስን፡ሰደደው፡እርሱ፡ ለአባ፡ መቃርስ፡ ትንቢት፡ ተናግሮለት፡ ነበርና፡እንዲህ፡ብሎ፡አንተ፡ግን፡በእስክን ድርያ፡አገር፡የሰማዕትነት፡አክሊል፡ትቀበል፡ ዘንድ፡አለህ።

፱፡ አባ፡መቃርስም፡ወደ፡እስክንድርያ፡ሲደርስ፡ በዚያን፡ጊዜ፡የመናፍቁ፡የንጉሥ፡መርቅያን፡ በውስጡ፡ የከፋች፡ ሃይማኖቱ፡ የተጻፈበት፡ የመልእክት፡ ደብዳቤ፡ ደረሰ፡ መልእክተኛ ውንም፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ አዞታል፡ በእኛ፡ ሃይማኖት፡አምኖ፡በዚህ፡መዝገብ፡ውስጥ፡ መጀመሪያ፡ የጻፈ፡ በእስክንድርያ፡ ሊቀ፡ ጳጳሳት፡ ይሁን፡ የሚል፡ ነው፡ አብሮታራ፡

www.ethiopianorthodox.org

ጳጳሳት ፡ ዘቍስጥንጥንያ ። ውእቱኬ ፡ እስመ ፡ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ካልዕ ፡ አርዮሳዊ ፡ ሶበ፡ ተቃረኖ ፡ ለአባ ፡ ጳውሎስ ፡ ሰደዶ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ አርማንያ ፡ ወበህየ ፡ ረሰየ ፡ ከመ ፡ ይሕንቅዎ ፡ በኀቡእ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ወይቅትልዎ ፡ እሙንቱሰ ፡ ቅዱሳን ፡ መርት ያኖስ፡ወመርቄሬዎስ፡ጸሐፋ፡ዕለተ፡ዕረፍቱ፡ ወዜናሁ ፡ ለአባ ፡ ጳውሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወረገምዎ፡ለንጉሥ፡አርዮሳዊ።

፫፡ ወሖረ ፡ አሐዱ ፡ ብእሲ ፡ እኩይ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወአስተዋደዮሙ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ረገምዎ ፡ ወንጉሥ ፡ አሚሃ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ መካን ፡ እምአዕፃዳት ፡ ወፈነወ ፡ ሐራ ፡ ወአብ ጽሐሙ ፡ ኀቤሁ ፡ ወአዘዘ ፡ ይቅትልዎሙ ፡ በሰይፍ፡ወቀተልዎሙ፡ወቀበርዎሙ፡በኀበ፡ ቀተልዎሙ ፡ በህየ ፡ ወኮኑ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ እስከ ፡ አመ ፡ መዋዕለ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ፡ወውእቱ፡ሶበ፡ሰምዐ፡ዜናሆሙ፡ፈነወ፡ ላዕካነ ፡ ወአብጽሐ ፡ ሥጋሆሙ ፡ በክብር ፡ ውስተ፡ሀገረ፡ቍስጥንጥንያ፡ወሐነፀ፡ሎሙ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠናይተ ፡ ወአንበረ ፡ ሥጋሆሙ፡ውስቴታ፡ወገብረ፡ሎሙ፡በዓለ፡ በዛቲ፡ዕለት።

፬፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐ ረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ለአባ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ናቸው ፡ ይህም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ አርዮሳዊ ፡ የሆነው ፡ ሁለተኛው፡ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ አባ ፡ ጳውሎስን፡በተጣላው፡ጊዜ፡ወደ፡አርማንያ፡ አጋዘውና ፡ በዚያም ፡ በሥውር ፡ በእሥር ፡ ቤት፡ ውስጥ ፡ አንቀው ፡ እንዲገድሉት ፡ አደረገ፡ እሊህ ፡ ቅዱሳን ፡ መርትያኖስና ፡ መር ቈሬዎስ ፡ ግን ፡ የዕረፍቱን ፡ ቀን ፡ ገድሉንም ፡ ጻፉ፡አርዮሳዊውንም፡ንጉሥ፡ረገሙት።

፫፡ አንድ ፡ ክፉ ፡ ሰውም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ሒዶ ፡ እነርሱ፡እንደረገሙት፡ወነጀላቸው፡ንጉሡም፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከአታክልት ፡ ቦታዎች ፡ በአንዲቱ ፡ ቦታ፡ተቀምጦ፡ሳለ፡ወታደሮች፡ልኮ፡ወደርሱ፡ አስቀረባቸው ፡ በሰይፍም ፡ እንዲገድሏቸው ፡ አዘዞ ፡ ገደሏቸው ፡ በዚያም ፡ በገደሏቸው ፡ ቦታ ፡ ቀበሩአቸው ፡ እስከ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ዘመንም ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ኖሩ ፡ እርሱም ፡ ዜናቸውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ መልእክተኞችን ፡ ልኮ ፡ ሥጋቸውን ፡ ወደቍስጥንጥንያ ፡ በክብር፡ አስመጣ ፡ ያመረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ ሠርቶላቸው ፡ ሥጋቸውን ፡ በውስጧ ፡ አኖረ፡ በዚችም፡ቀን፡በዓልን፡አደረገላቸው።

፬፡ ለእግዚአብሔርም፡ምስጋና፡ይሁን፡እኛንም፡ በቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለመርትያኖስ ፡ ዘተጋደለ ፡ በጽንዐ ። ወለመርቄሬዎስ ፡ ስንዐ ። ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳውሎስ፡ እስመ፡ እሙንቱ ፡ አርዳኢ ። እለ ፡ ሠለጡ ፡ ገድሎሙ ፡ ወዐስበ ፡ ስብሐቶሙ ፡ ነሥኡ ። ድኅረ ፡ መምህሮሙ ፡ ፈጸማ፡ለስምዑ።

፩፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለአባ ፡ መቅብዩ ፡ ወአባ ፡ ይምዓታ ፡ ፩እም፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ወያፌት ፡ ዘባረከ ፡ ኖኅ ፡ አቡሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ለያርህብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደውሎ ፡ ለያፌት ፡ ወተዝካሮሙ ፡ ለአበዊነ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ፡ ወያዕቆብ ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፩፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የአባ ፡ መቅብዩ ፡ ከዘጠኙ ፡ ቅዱሳን ፡ የአንዱ ፡ የአባ ፡ ይምዓታ ፡ ዳግመ ኛም፡ አባቱ ፡ ኖኅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያያፌትን ፡ አገር ፡ ያስፋለት ፡ ብሎ ፡ የመረቀው ፡ ያፌት ፡ የአባቶቻችንም ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕ ቆብ ፡ መታሰቢያቸው ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## አርኬ

ሰላም ፡ ሰላም ፡ ለአባ ፡ ይምዓታ ፡ ዘተሳተፈ ፡ አዕሩገ ። እለ ፡ ኃሠሡ ፡ ሥርዓተ ፡ ወእለ ፡ ዐቀቡ ፡ ሕገ ። በሥምረተ ፡ አምላክ ፡ ከሃሊ ፡ እንተ ፡ ሠጠቀ ፡ አፍላገ ። በድነ ፡ ሥጋሁሰ ፡ አመ ፡ መልዕልተ ፡ ደብር ፡ ዐርገ ። ዐሠረ፡ግንዘተ፡በኰነኰሕ፡ለትእምርት፡ተኀድገ።

ሰላም ፡ ለአብርሃም ፡ ዘተፈልጠ ፡ እምሕዝቡ ። ሊያዕቆብሂ ፡ ወልደ ፡ ይስሐቅ ፡ አቡ ። እለ ፡ ተደለዉ ፡ ርእየ፡እግዚአብሔርሃ ፡ ዲበ ፡ ኪሩቡ ። በአዕይንቲሆሙ ፡ አምኃ ፡ ጽጌ ፡ ተዘግቡ ። ወበገነቶሙ ፡ እንኰታት ፡ መዐዛ፡ወሀቡ።

* * *

፩፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ አመ ፡ ፳ወ፱ ፡ ለጥቅምት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተዘከረ ፡ በዓለ ፡ ልደቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምእግዝእትነ ፡ ቀድስት፡ድንግል፡ማርያም። ወሎቱ፡ስብሐት፡ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ኄር ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥቅምት ፡ ሃያ ፡ ዘጠኝ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ የጌታችን ፡የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከእመቤታችን ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የተወለደበት ፡ የልደቱ ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ ነው። ለእርሱም ፡ ከቸር ፡ አባቱ ፡ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ከሆነ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋር ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም ፡ ለልደትከ ፡ በበትረ ፡ አሮን ፡ ዘተርእየ ። አመ ፡ ጸገየት ፡ ወፈረየት ፡ እንበለ ፡ ይስቅይዋ ፡ ማየ ። ኢየሱስ፡ክርስቶስ መድኃኔ፡ገጽየ።ከመ፡ትምሐረኒ፡ሥመር፡ኪያየ።ከመ፡አንተ፡ትቤ፡መሐሩ፡ነዳየ።

፯፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ለመክስምያኖስ ፡ ንጉሥ፡ከሀዲ።

፰፡ ወዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ እምሀገረ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ወተምህረ ፡ ትምህርተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት፡ወጽንዐ፡ኮነ፡በሃይማኖት፡ርትዕት፡ ወይሜሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወይሰብክ ፡ ሎሙ ፡ ሃይማኖተ ፡እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ፡ስብሐት፡ወሚጠሙ፡ለብዙኃን፡እምስ ህተት።

፱፡ ወበእንተዝ ፡ አስተዋደይዎ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ከሀዲ፡ ወአዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ያምጽእዎ፡ ኀቤሁ ፡ ወሀሎ ፡ በኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ፩ ብእሲ ፡ ጽኑዕ፡ በሥጋሁ፡ወግዙፍ፡ወስፉሕ፡በዐፅሙ፡ወዘይ መስሎሙ፡ለኵሎሙ፡ሰብእ፡ይመውዕ፡ኵሎ፡ ወሎቱ፡አልቦ፡ዘይመውዖ፡ንጉሥኒ፡ያፈቅሮ፡ ወይትሜካህ ፡ ቦቱ ፡ ወይብል ፡ እሁቦ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ፡ለዘይመውዖ፡ለውእቱ፡ብእሲ፡ዘግዙፍ፡ አካሉ።

፯፡ በዚችም፡ቀን፡ በከሀዲው፡ንጉሥ፡በመክስምያኖስ ፡ ዘመን ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ በሰማዕትነት፡አረፈ።

፰፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ ከተሰሎንቄ ፡ ሀገር ፡ ነው ፡ የከበረች፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ ትምርት ፡ ተምሮ፡በቀናች፡ሃይማኖት፡ጸና፡ሕዝቡንም፡ የሚያስተምር፡ሆነ፡ክብር፡ይግባውና፡የጌታ ችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ በመ ስበክ፡ብዙዎችን፡ከስሕተት፡መለሳቸው።

፱፡ ስለዚህም ፡ በከሀዲው ፡ ንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ወነጀ ሉት ፡ ንጉሡም ፡ ወደርሱ ፡ እንዲአመጡት ፡ አዘዘ ፡ በንጉሡም ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሥጋው ፡ የደነደነ ፡ የጸና ፡ ዐጥንቱ ፡ የሰፋ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ለሰዎችም ፡ ሁሉ ፡ እሱ ፡ ሁሉን ፡ የሚያሸንፍ ፡ እሱን ፡ የሚያሸንፈው ፡ የሌለ ፡ ይመስላቸው ፡ ነበር ፡ ንጉሡም ፡ ይወደዋል ፡ ይመካበታል ፡ እንዲህም ፡ ይል ፡ ነበር ፡ ይህን ፡ አካሉ ፡ ግዙፍ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለሚያሸንፍ ፡ እኔ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ እሰጠዋለሁ።

www.ethiopianorthodox.org

፭፡ ወውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ተንሥአ ፡ ፩ ብእሲ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ዘስሙ ፡ በስጥዮስ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ወሰአሎ ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይእተብ ፡ ዲበ ፡ ሥጋሁ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ መዋዒ ፡ ውእቱኒ ፡ ጸለየ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአተበ ፡ ዲበ ፡ ኵሉ ፡ ሥጋሁ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ። ወእምዝ ፡ ቦአ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወሰአሎ ፡ ከመ ፡ ያስተቃልሶ ፡ ምስለ ፡ ውእቱ ፡ ግዙፈ ፡ ሥጋ ፡ ንጉሥኒ ፡ አብሖ ፡ ወሶበሂ ፡ ተቃለሱ ፡ አውደቆ ፡ ወሞዖ ፡ ለውእቱ ፡ ግዙፈ ፡ ሥጋ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ወኀዘነ ፡ ንጉሥ ፡ ወአንከረ ፡ ወነፍረ ፡ በተመውዖቱ ፡ ለግዙፈ ፡ ሥጋ ፡ እስመ ፡ ይትሜካህ ፡ ቦቱ ።

፮፡ ወተሰአለ ፡ ንጉሥ ፡ ሐራሁ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ እሙንቱኒ ፡ ነገርዎ ፡ ከመ ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ጸለየ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአተበ ፡ ዲበ ፡ ሥጋሁ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ።

፯፡ ወሰሚዖ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንተ ፡ ተምዕ ፡ ፈድፋደ ፡ ላዕለ ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ይቅሥፍዎ ፡ እስከ ፡ ይወግር ፡ ዕጣነ ፡ ለአማልክት ፡ ወገብሩ ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ወሶበ ፡ ኢሰምዐ ፡ ትእዛዞ ፡ ለንጉሥ ፡ አዘዘ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይርግዝዎ ፡ በኵያንው ፡ እስከ ፡ ይመውት ።

፰፡ ወነገርዎ ፡ ሐራ ፡ ዘንተ ፡ ፍትሐ ፡ ለቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ እስመ ፡ መሰሎሙ ፡ ዘየኀድግ ፡ ሃይማኖቶ ፡ ወይሰግድ ፡ ለአማልክት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ግበሩ ፡ ዘትፈቅዱ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ኢይፈቅድ ፡ እስግድ ፡ ለአማልክት ፡ ርኵሳን ፡ ወኢ ፡ ወጊረ ፡ ዕጣን ፡ ዘእንበለ ፡ ለእግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ።

፱፡ ወሶቤሃ ፡ ረገዝዎ ፡ በኵናት ፡ እስከ ፡ መጠወ ፡ ነፍሶ ፡ ንጹሕተ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወሶበ ፡ ወገሩ ፡ ሥጋሁ ፡ ነሥእዎ ፡ መሐይምናን ፡ ኀቢሆሙ ፡ ወረሰይዎ ፡ ውስተ ፡ ግዑን ፡ ወአንበርዎ ፡ ኀቡአ ፡ ውስተ ፡ ቤቶሙ ፡ እስከ ፡ የኀልፍ ፡ መዋዕለ ፡ ስደት ።

፲፡ ወእምድኅረ ፡ ኀለፈ ፡ መዋዕለ ፡ ስደት ፡ ከሠቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአውጽእዎ ፡ እምህየ ፡ ወሐነፁ ፡ ሎቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠናይተ ፡ በሀገረ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ወአንበሩ ፡ ሥጋሁ ፡ ውስቴታ ፡

፭፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ስሙ ፡ በስጥዮስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ሔደ ፡ እንዲጸልይለትና ፡ በሥጋውም ፡ ሁሉ ፡ አሸናፊ ፡ በሆነ ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ እንዲአማትብበት ፡ ለመነው ። እርሱም ፡ በላዩ ፡ ጸለየለት ፡ በሥጋውም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በመስቀል ፡ አማተበበት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ገብቶ ፡ ከዚያ ፡ ሥጋው ፡ ግዙፍ ፡ ከሆነው ፡ ጋር ፡ ያታግለው ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ፡ ንጉሡም ፡ ፈቀደለት ፡ በታገሉም ፡ ጊዜ ፡ ሥጋው ፡ የደነደነውን ፡ ያ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ሰው ፡ አሸንፎ ፡ ጣለው ፡ ንጉሡም ፡ አዘነ ፡ አደነቀም ፡ ሥጋው ፡ የደነደነውም ፡ በመሸነፉ ፡ አፈረ ፡ ተመክቶበት ፡ ነበርና ።

፮፡ ንጉሡም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ወታደሮቹን ፡ ጠየቀ ፡ እነርሱም ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ በላዩ ፡ እንደጸለየለትና ፡ በሥጋውም ፡ ላይ ፡ በመስቀል ፡ ምልክት ፡ እንዳማተበበት ፡ ነገሩት ።

፯፡ ንጉሡም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በቅዱስ ፡ ድሜጥሮስ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቆጣ ፡ ለአማልክትም ፡ ዕጣን ፡ እስከሚአሳርግ ፡ ድረስ ፡ እንዲገርፉት ፡ አዘዘ ፡ ንጉሡም ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉበት ፡ የንጉሡንም ፡ ትእዛዝ ፡ ባልሰማ ፡ ጊዜ ፡ እስከሚሞት ፡ በጦሮች ፡ እንዲወጉት ፡ ሁለተኛ ፡ አዘዘ ።

፰፡ ለቅዱስ ፡ ድሜጥሮስም ፡ ይህን ፡ ፍርድ ፡ ነገሩት ፡ ሃይማኖቱን ፡ ትቶ ፡ ለአማልክት ፡ የሚሰግድ ፡ መስሏቸው ፡ ነበርና ፡ ቅዱስ ፡ ድሜጥሮስም ፡ እኔ ፡ ከዕውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ከሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቀር ፡ ለረከሱ ፡ አማልክት ፡ እሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ዕጣን ፡ ማሳረግም ፡ አልፈቅድም ፡ የወደዳችሁትን ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ።

፱፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ንጽሕት ፡ ነፍሱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ እስከ ሚሰጥ ፡ በጦር ፡ ወጉት ፡ ሥጋውንም ፡ በጣሉት ፡ ጊዜ ፡ ምእመናን ፡ ወደ ፡ ርሳቸው ፡ ወሰዱት ፡ የስደቱም ፡ ወራት ፡ እስከ ሚያልፍ ፡ በግጥን ፡ አድርገው ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ሠውረው ፡ አኖሩት ።

፲፡ የስደቱም ፡ ወራት ፡ ከአለፈ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገለጠውና ፡ ከዚያ ፡ አወጡት ፡ ያማረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ በተሰሎንቄ ፡ አገር ፡ ሠሩለት ፡ ሥጋውንም ፡ በውስጧ ፡ አኖሩ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ወሀሎ፡እስከ፡ይእዜ፡እንዘ፡ይገብር፡ተአምረ፡ ወመንክረ፡ዐቢየ፡እስመ፡ይውኅዝ፡እምኔሁ፡ ቅብዐ፡ዕፍረት፡ዘምዑዝ፡ጼናሁ፡ፈድፋደ፡ ወይፌውሶሙ፡ለኵሎሙ፡ዱያን፡እለ፡ይትቀብዑ፡በአሚን፡ወፈድፋደሰ፡በዕለተ፡ተዝካረ፡ ዕረፍቱ ፡ ይውኅዝ ፡ ብዙኀ ፡ እምካልአን ፡ ዕለታት ፡ ወእምኵሉ ፡ አድያም ፡ ይመጽኡ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ ወይነሥኡ ፡ እምውእቱ ፡ ቅብዕ፡ወይወድይዎ፡በገማዕዊሆሙ፡ወካህናት፡ጻድቃን፡ኮኑ፡ሰማዕተ፡ከመ፡ዛቲ፡ትእምርት፡ ትሄሉ ፡ ወትትረከብ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ፡ዓለም።

፲፩፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ሰማዕት ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ድንቅ ፡ የሆነ ፡ ታላቅ ፡ ተአምርን ፡ እያደረገ ፡ እስከ ፡ ካሬ ፡ አለ። ሽታው፡ እጅግ ፡ ጣፋጭ፡ የሆነ፡ የሽቱ ፡ ቅባት ፡ ከእርሱ ፡ ይፈሳልና ፡ በእምነት፡የሚቀቡትን፡በሽተኞች፡ሁሉንም፡ ያድናቸዋል። ይልቁንም ፡ በዕረፍቱ ፡ መታሰቢያ፡ ቀን ፡ ከሌሎቹ ፡ ዕለታት ፡ ተለይቶ ፡ በብዛት ፡ ይፈሳል ፡ ከአውራጃው ፡ ሁሉ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎችም ፡ ይመጣሉ ፡ ከዚህም ፡ ቅባት፡ወስደው፡በማሰሮቻቸው፡ያደርጋሉ፡ ይቺ ፡ ምልክትም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ በመኖር ፡ እንደምትገኝ ፡ ደጋጎች ፡ ካህናት ፡ ምስክሮች፡ሆኑ።

፲፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም፡በዚህ፡ሰማዕት፡ጸሎት፡ይማረን፡በረከቱም፡ከእኛ፡ጋር፡ትኑር፡ለዘላለሙ፡አሜን።

## አርኬ

ሰላም፡ለከ፡ድሜጥሮስ፤ሰማዕት። ርጉዘ፡ገቦ፡በኵናት። እስእለከ፡ኀፀረኒ፡በጽጌ፡ቅድሳት። ኢያማዕርር፡ጕርዔየ፡ጸቃውዐ፡ዘማ፡ኀስርት። ፈዳዬ፡መጥባሕት፡ስሑል፡ወመሪር፡ሞት።

፲፪፡ ወበዛቲ፡ዕለት፡ተገብረ፡ዕረፍቱ፡ለቅዱስ፡ ስቅጣር፡ሰማዕት፡ፍቁረ፡ድሜጥሮስ፡እግዚአብሔር ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቱ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም፡አሜን።

፲፫፡ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ ጸቃውዐ፡ድንግል፡መምህር፡ዘደብረ፡ዘሽኝ።

፲፬፡ ወለዝንቱ፡ ቅዱስ ፡ አቡሁ ፡ ካህን ፡ ወሐፀኖ ፡ በጥበብ ፡ ወበተግሣጽ ፡ ሠናይ ፡ ወመሀሮ ፡ ኵሎ፡ ትምህርተ ፡ መለኮታዊተ ፡ ወሶበ ፡ ልሕቀ ፡ ወኮኖ ፡ ፵ዓመተ ፡ መንኰሰ ፡ አቡሁ ፡ ውስተ ፡ ፩፡ ደብር ፡ ወተኀርየ ፡ ለምህሮ ፡ ወተሠይመ ፡ ላዕለ፡ መንበሩ ፡ ለአባ ፡ ገብረ ፡ ማርያም።

፲፭፡ ወሶቤሃ፡ አልበሶ፡ ለወልዱ፡ አልባሰ፡ ምንኩስና፡ ወሰመዮ፡ ስሞ፡ ጸቃውዐ፡ ድንግል፡ ወእምአሜሃ፡ ወጠነ፡ ተጋድሎ፡ ዐቢየ፡ በጾም፡ ወበጸሎት ፡ ወበሰጊድ ፡ ብዙኀ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽርዓት።

፲፮፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ አዕረፈ ፡ አቡሁ ፡ ተሠይመ ፡ ህየንቴሁ፡ ወረዓዮሙ፡ ለመርዔቱ፡ በሠናይ፡ ተዐቅቦ፡ በከመ፡ ሥርዓተ፡ ሐዋርያት።

፲፪፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ የድሜጥሮስ ፡ ወዳጅ ፡ የሰማዕት፡ ስቅጣር፡የዕረፍቱ፡ መታሰቢያ፡ ነው፡ እግዚአብሔርም፡ በጸሎቱ፡ ይማረን፡ ለዘላለሙ፡አሜን።

፲፫፡ በዚችም፡ቀን፡የተመሰገነና፡የከበረ፡የደብረ ዘሽኝ፡መምህር፡ጸቃውዐ፡ድንግል፡አረፈ።

፲፬፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ አባቱ ፡ ካህን ፡ ነው ፡ በጥበብና ፡ በበጎ ፡ ተግሣጽም ፡ አሳደገው ፡ መለኮታዊ ፡ ትምህርትን ፡ ሁሉ ፡ አስተማረው ፡ አድጎ፡ አርባ ፡ ዓመትም ፡ በሆነው ፡ ጊዜ ፡ አባቱ ፡ ከአንድ ፡ ገዳም ፡ ውስጥ ፡ መነኰሰ ፡ ለመምህርነትም ፡ ተመርጦ ፡ በአባ፡ ገብረ ፡ ማርያም፡ወንበር፡ላይ፡ተሾመ።

፲፭፡ በዚያንም፡ጊዜ፡አባቱ፡ለልጁ፡የምንኵስና፡ ልብስ ፡ አለበሰው ፡ ስሙንም ፡ ጸቃውዐ ፡ ድንግል ፡ ብሎ፡ ሰየመው፡ ከዚያችም፡ ጊዜ፡ ጀምሮ፡ያለ፡ማቋረጥ፡በጾም፡በጸሎት፡ብዙ፡ በመስገድም፡ ታላቅ፡ ተጋድሎን፡ ተጋደለ።

፲፮፡ ከዚህም፡ በኋላ፡ አባቱ፡ በአረፈ፡ ጊዜ፡ በአባቱ፡ ፈንታ ፡ ተሾመ ፡ መንጋዎቹንም ፡ እንደሐዋርያት ፡ ሥርዓት ፡ በመልካም ፡ አጠባበቅ ፡ ጠበቃቸው።

www.ethiopianorthodox.org

፲፯፡ ወኮነ ፡ በኵሉ ፡ ሌሊት ፡ ይቀውም ፡ ውስተ ፡ ባሕር፡ወወጺአ፡እምባሕር፡ያወትር፡ሰጊደ፡ እስከ ፡ ያንጸፈጽፍ ፡ ሐፉ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡ ወሲሳዩ፡ይቡስ፡ኅብስት፡ወኢይሰቲ፡ሜሰ፡ ወኢ ፡ ምዝረ ፡ ወአርአየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዲበ፡እደዊሁ፡ተአምረ፡ወእንዘ፡የሐውር፡ በውስተ፡ፍኖት፡ረከበ፡መፃጕዐ፡ዘኢሖረ፡ እምንእሱ፡ወነገሮ፡ላዕሌሁ፡ማየ፡ጸሎት፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ወአተቦ፡በትእምርተ፡ መስቀል፡ወሐይወ፡ሶቢሃ።

፲፰፡ ወሶበ፡በጽሐ፡ፍልሰቱ፡እምዝንቱ፡ዓለም፡ ደወየ፡ንስቲተ፡ወአዕረፈ፡በሰላም።

፲፱፡ ወስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነኒ፡ይምሐረነ፡በጸሎቱ፡ለዝንቱ፡ጻድቅ፡ወበረከቱ፡ ተሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

* * *

፩፡ በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩ አምላክ ፡ አመ ፡ ፴ሁ፡ ለጥቅምት ፡ በዛቲ ፡ ዕለት፡አዕረፈ፡አብ፡ቅዱስ፡ወጽሙድ፡ወመ ስተጋድል፡አብርሃም፡ባሕታዊ፡እምሀገረ፡ መኑፍ።

፪፡ ወለዝንቱ፡ቅዱስ፡አበዊሁ፡ፈራህያነ፡እግዚአ ብሔር፡ወያመልክዎ፡ለክርስቶስ፡ወብዑላን፡ ፈድፋደ፡በንዋየ፡ዝንቱ፡ዓለም።

፫፡ ወሶበ፡ልሕቀ፡ዝንቱ፡ቅዱስ፡ፈተወ፡ይልበስ፡ አልባሰ፡ምንኵስና፡ወዐርገ፡ሐመረ፡ወሖረ፡ ኀበ፡ሀገረ፡አክሚም፡ዘላዕላይ፡ግብጽ፡ወበ ጽሐ፡ኀበ፡አባ፡ጳኵሚስ፡ውእቱኒ፡አልበሶ፡ አልባሰ፡ምንኵስና፡ወአፃመወ፡ሥጋሁ፡በተ ጸምዶተ፡ገድል፡ወነበረ፡ዘኀበ፡አባ፡ጳኵ ሚስ፡ውስተ፡ማኅበረ፡ዚአሁ፡መጠነ፡፳ወ፫ ዓመት።

፬፡ ወእምድኅረዝ፡ሰአሎ፡ለቅዱስ፡አባ፡ጳኵሚስ፡ ከመ ፡ ይኅድጎ ፡ ይንበር ፡ ባሕቲቶ ፡ ውስተ ፡ በአት ፡ ውእቱኒ ፡ አብሐ ፡ ወኮነ ፡ ዘይገብር ፡ በእደዊሁ፡መርበብተ፡ዘያሠግሩ፡ቦቱ፡ዓሣ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብ ሐት ፡ አምጽአ ፡ ሎቱ ፡ አሐደ ፡ ብእሴ፡ ወውእቱ፡ ይሠይጥ ፡ ሎቱ ፡ ወሲሳዮሰ ፡ ይሣየጥ፡ ሎቱ ፡ አተረ ፡ ይቡሰ ፡ ወዘተርፈ ፡ ይሁብ ፡ ለነዳያን ፡ ወመጠነ ፡ ሲሳዩኒ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ አሐቲ ፡ ሕፍን ፡ በጊዜ ፡ ምሴት ፡ ዘርሑስ፡በማይ፡ዘምስለ፡ፄው።

፲፯፡ በሌሊቱም ፡ ሁሉ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ቆሞ ፡ ያድራል፡ከባሕሩም፡ሲወጣ፡ወዙ፡በምድር፡ ላይ ፡ እስከሚንጠፈጠፍ ፡ ስግደትን፡ ያዘወ ትራል፡ምግቡም፡ደረቅ፡እንጀራ፡ነው፡ጠጅ፡ ወይም፡ጠላ፡አይጠጣም፡እግዚአብሔርም፡ በእጆቹ ፡ ላይ፡ ተአምራትን ፡ አደረገ ፡ በጐዳናም፡ሲጓዝ፡ከታናሽነቱ፡ጀምሮ፡ሒዶ፡ የማያውቅ፡መፃጉዕን፡አገኘ፡በስመ፡አብ፡ ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ብሎ፡የተጸለየ በትን ፡ ውኃ ፡ በላዩ ፡ ረጨ ፡ በመስቀልም ፡ ምልክት፡አማተበው፡በዚያንም፡ጊዜ፡ዳነ።

፲፰፡ ከዚህም፡ዓለም፡የሚለይበት፡ሰዓት፡በደረሰ፡ ጊዜ፡ጥቂት፡ታሞ፡በሰላም፡አረፈ።

፲፱፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛ ንም ፡ በዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ጸሎት ፡ ይማረን ፡ ለዘላለሙ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር፡ አሜን።

* * *

፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ጥቅምት ፡ ሠላሳ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ መኑፍ ፡ ከሚባል ፡ አገር ፡ በገ ድል ፡ የተጸመደ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ ባሕታዊ ፡ አብርሃም፡አረፈ።

፪፡ የዚህም ፡ ቅዱስ ፡ ወላጆቹ ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚፈሩና፡የሚያመልኩ፡ናቸው፡በዚህም፡ ዓለም፡ገንዘብ፡እጅግ፡ባለጸጎች፡ነበሩ።

፫፡ ይህም ፡ ቅዱስ ፡ በአደገ ፡ ጊዜ ፡ የምንኵስናን ፡ ልብስ ፡ ሊለብስ ፡ ሽቶ ፡ በላዕላይ ፡ ግብጽ ወደሚገኝ፡ወደ፡ ሀገረ፡አክሚም፡በመርከብ፡ ተጭኖ፡ሔደ፡ወደ፡አባ፡ጳኵሚስም፡ደረሰ፡ እርሱም ፡ የምንኵስና ፡ ልብስን ፡ አለበሰው ፡ በገድልም፡በመጸመድ፡ሥጋውን፡አደከመ፡ በአባ፡ ጳኵሚስም ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ሃያ፡ሦስት፡ዓመት፡ያህል፡በማገልገል፡ኖረ።

፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ብቻውን ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንዲአሰናብተው ፡ አባ ፡ ጳኵሚስን፡ ለመነው ፡ እርሱም ፡ ፈቀደለት ፡ ዓሣ ፡ የሚያሠግሩበትን ፡ መረብ ፡ የሚሠራ ፡ ሆነ ፡ ክብር፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም፡አንድ፡ሰውን፡አመጣለት፡ያም፡ ሰው ፡ መረቡን ፡ ሽጦ ፡ ምግቡን ፡ አተር ፡ ይገዛ ለታል ፡ የተረፈውንም ፡ ለድኆች ፡ ይሰጣል ፡ የምግቡም ፡ መጠን ፡ ሁልጊዜ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ አንዲት፡እፍኝ፡ከጨው፡ጋር፡በውኃ፡የራሰ፡ አተር፡ነው።

www.ethiopianorthodox.org

